## ምክንያተ ፡ መልእክተ ፡ ጳውሎስ ፡ ካልእ ፡ ኀበ ፡ ሰብአ ፡ ቆሮንቶስ ።

እስመ ፡ ሰብአ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ኮኑ ፡ ሶበ ፡ ተወከፍዋ ፡ ለመልእክቱ ፡ ቀዳሚት ፡ ተከዙ ፡ ጥቀ ፡ እንዘ ፡ ይኔስሑ ፡ እምኀጢአቶሙ ፡ ለእለ ፡ ነሥኡ ፡ ማዕርገ ፡ ሢመቶሙ ፡ ለመምህራን ፡ ወኀዘኑ ፡ በእንተ ፡ ዘተሐየዩ ፡ ወኢገብሩ ፡ ንስሐ ፡ በእንተ ፡ ዝቲ ፡ ኃጢአት ።

ወዓዲ ፡ ተባየጽዎሙ ፡ ለቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ እለ ፡ ያመጽኡ ፡ ምክንያተ ኃዕዝ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ያከብርዋ ፡ ለመጽሐፈ ፡ ኦሪት ፡ ወይመንንዋ ፡ ለሥርዓተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወይሬስይዋ ፡ ከመ ፡ ወኢምንት ።

ወእጽንኡ ፡ ልቦሙ ፡ ለብዙኃን ፡ ኀበ ፡ ዝንቱ ፡ ግብር ፡ በተእዝዞቶሙ ፡ ለእሉ ፡ እምድኅረ ፡ እስተሐመሙ ፡ ፀሠናይ ፡ ጸሕቅ ፡ በእንተ ፡ እምኃ ፡ ዘይፌንውዎ ፡ ለቅዱሳን ፡ ኀበ ፡ ኢየሩሳሌም ።

ወነገረ ፡ ዘንተ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ረድኡ ፡ እመ ፡ ገብአ ፡ ኀቤሁ ፡ እምኀቤሆሙ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ በፊልጵስዩስ ፡ ዘመቄዶንያ ።

ወፈነዎ ፡ ለቲቶ ፡ ረድኡ ፡ ዘእንበለ ፡ መጽሐፍ ፡ ከመ ፡ ይገሥጾሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ በቃሉ ፡ ከመ ፡ ኢይትወከፍዎሙ ፡ ለእሉ ፡ ሐዋርያተ ፡ ሐሰት ።

ወሶበ ፡ በጽሐ ፡ ኀቤሆሙ ፡ ቲቶ ፡ ተወከፍዎ ፡ ኵሎሙ ፡ ወመሀርሙ ፡ ከመ ፡ ኢይትወከፍዎሙ ፡ እስከ ፡ ዐበይዎሙ ፡ ወገብኡ ፡ ኀበ ፡ ጸሕቆሙ ፡ ዘቀዳሚ ።

ወተእዘዙ ፡ ሎቱ ፡ በፍርሃት ፡ ወበረዓድ ። ወእምዝ ፡ ሖረ ፡ ቲቶ ፡ እምኀቤሆሙ ፡ እንዘ ፡ የአኵትዎ ፡ ወይትዌከፍ ፡ ሥላጤሆሙ ።

ወነገሮ ፡ ለጳውሎስ ፡ ሐዋርያ ፡ ዘከመ ፡ ተእዘዙ ፡ ሎቱ ፡ ወአፈድፈዱ ፡ ጸሕቀ ፡ እምቀዳሚ ፡ በእንተ ፡ እምኃ ፡ ዘይፌንውዎ ፡ ኀበ ፡ ቅዱሳን ።

ወሶበ ፡ ሰምዐ ፡ ዘንተ ፡ ሐዋርያ ፡ ጸሐፈ ፡ ሎሙ ፡ ዳግመ ፡ መልእክተ ፡ እንዘ ፡ ያቀድም ፡ ወድሶቶሙ ፡ ለእሉ ፡ እለ ፡ ሰደድዎ ፡ ለዝኩ ፡ ዘተዐደወ ፡ ሥርዓተ ፡ ትእዛዝ ፡

## ጳውሎስ ፡ ኹለተኛ ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ የጻፈው ፡ ክታብ ፡ ምክንያት ።

የቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ የፊተኛይቱን ፡ ክታቡን ፡ በተቀበሏት ፡ ጊዜ ፡ የመምህርቻቸውን ፡ ሹመት ፡ የተሾሙትን ፡ ሰዎች ፡ ስለዚች ፡ ኃጢአታቸው ፡ ንስሐ ፡ አድርገው ፡ ሳይለዩዋቸው ፡ በመቅረታቸው ፡ ቸል ፡ በማለታቸው ፡ እየተጠጡ ፡ እጅግ ፡ አርገው ፡ አዝነው ፡ ተከዘው ፡ ነበረ ።

ዳግመኛም ፡ የክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ ወንጌልን ፡ እንደ ፡ ኢምንት ፡ አድርገው ፡ ንቀው ፡ አቃለው ፡ ኦሪትን ፡ ያከብሯት ፡ ዘንድ ፡ ወንጌል ፡ እንበለ ፡ ኦሪት ፡ ጥምቀት ፡ እንበለ ፡ ግዝረት ፡ አትረባም ፡ አትጠቅምም ፡ እያሉ ፡ ጠብ ፡ ክርክርን ፡ የሚፈጥሩ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያንን ፡ ጓደኞች ፡ አድርገዋቸው ፡ ነበርና ።

በኢየሩሳሌም ፡ ላሉ ፡ ምእመናን ፡ የሚሰዱትን ፡ እስተዋፅኦውን ፡ ለማወጣጣት ፡ ፀበን ፡ ሐሳብ ፡ በፍጹም ፡ ትጋት ፡ ከደከሙ ፡ በኋላ ፡ ብዙዎች ፡ ሰዎች ፡ ለነዚህ ፡ በመታዘዛቸው ፡ ልቡናቸውን ፡ ወደዚህ ፡ ግብር ፡ አዘንብለው ፡ ነበርና ።

ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ እነሱን ፡ ጠይቆ ፡ ወደርሱ ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ የመቄዶንያ ፡ ክፍል ፡ በምትኾን ፡ በፊልጵስዩስ ፡ ላለ ፡ ይህን ፡ ነገረው ።

ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ቲቶን ፡ እኒህን ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያንን ፡ እንዳይቀበሏቸው ፡ በቃል ፡ ይመክራቸው ፡ ያስተምራቸው ፡ ዘንድ ፡ ክታብ ፡ ሳይጽፍ ፡ በቃል ፡ ላከው ።

ቲቶም ፡ ከነሱ ፡ ዘንድ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ኹሉም ፡ አክብረው ፡ ተቀበሉት ፡ እሱም ፡ ወደቀደመ ፡ ትሩፋታቸው ፡ ተመልሰው ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያንን ፡ እንቀበላችሁም ፡ እስኪሏቸው ፡ ድረስ ፡ መላልሶ ፡ አስተማራቸው ።

ፈርተው ፡ ተንቀጥቅጠው ፡ ታዘዙለት ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቲቶ ፡ ግዳጅ ፡ መፈጸማቸውን ፡ አይቶ ፡ እያመሰገናቸው ፡ ከነሱ ፡ ዘንድ ፡ ተመለሰ ።

ለጳውሎስም ፡ ለርሱ ፡ መታዘዛቸውን ፡ ለምእመናን ፡ ስለሚልኩት ፡ እስተዋፅኦ ፡ ማወጣጣትም ፡ ከቀደመው ፡ ይልቅ ፡ አብልጠው ፡ መትጋታቸውን ፡ ነገረው ።

ሐዋርያ ፡ ጳውሎስም ፡ ይህን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ የመምህሩን ፡ ሹመት ፡ የተሾመውን ፡ ያባቱን ፡ ሚስት ፡ የነሣውን ፡ ንስሐ ፡ ሠርተው ፡ በመለየታቸው ፡ እነሱን ፡ እያመሰገነ ፡ ይህን ፡ ኹለተኛውን ፡ ክታብ ፡ ጻፈላቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

ወእርእዮሙ ፡ ካዕበ ፡ በጪስቴታ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ሐዋርያ ፡ ዘይሰብክ ፡ በጽድቅ ፡ እንዘ ፡ የሐምም ፡ በብዙኀ ፡ መከራ ፡ ወውእቶሙ ፡ ሐዋርያት ፡ ሐሳውያን ።

ወእምዝ ፡ ሰአሎሙ ፡ ወአስተብቍዖሙ ፡ ከመ ፡ ይትወከፍዎ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ እመ ፡ ነስሐ ።

ወፈነወ ፡ ዘንተ ፡ መልእክተ ፡ በእደ ፡ ቲቶ ፡ ወሉቃስ ፡ እንዘ ፡ ሀሎ ፡ በፊልጵስዩስ ፡ ዘመቄዶንያ ።

ዳግመኛም ፡ በዚች ፡ ክታብ ፡ ውስጥ ፡ ይህ ፡ ሐዋርያ ፡ መከራ ፡ እየተቀበለ ፡ የሚያስተምር ፡ እውነተኛ ፡ መምህር ፡ እንደኾነ ፡ እነዚያ ፡ ግን ፡ ሐሰተኞች ፡ መምህራን ፡ እንደኾኑ ፡ ገለጠላቸው ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ያሰው ፡ ቢመለስ ፡ ይቀበሉት ፡ ዘንድ ፡ እንዲቀበሉት ፡ ለመናቸው ፡ ማለዳቸው ።

ይህን ፡ ክታብ ፡ የመቄዶንያ ፡ ክፍል ፡ በምትኾን ፡ በፊልጵስዩስ ፡ ሳለ ፡ ጽፎ ፡ በቲቶና ፡ በሉቃስ ፡ እጅ ፡ ላከላቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

ቀዳማዊ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ካልእት ፡ አለ ፡ (ታሪክ ፡ ) ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ በፊልጵስዩስ ፡ ኾኖ ፡ ቷቶን ፡ ጢዮቀኖቸው ፡ ና ፡ ብሎ ፡ ሰዶታል ፡ ቢ ሔድ ፡ ለአስተዋፅኦ ፡ ሲተጉ ፤ ለምግባር ፡ ለቸሩፋት ፡ ሲፎካከሩ ፡ ያባቱን ፡ ሚስት ፡ የነግው ። የመምህሩን ፡ ሹመት ፡ የተቃወሙትን ፡ ለይተው ፤ እኔ ፡ ዘጳውሎስ ፡ ወእኔ ፡ ዘአጵሎስ ፡ ሐኔ ፡ ዘኬፋ ፤ ማለትን ፡ ትተው ፡ እኔ ፡ ዘክርስቶስ ፡ ሲሉ ፡ አግኝቷቸዋል ። ነገር ፡ ግን ፡ ክዕው ፡ ጽንተ ፡ አይታጣምና ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ በመና ፡ በደመና ፡ ሲመኩ ፡ ሰምተው ፡ ወደአሪት ፡ እንመለስ ፡ ብለዋል ፡ ሐጅ ፡ ይህን ፡ ነግሮታል ፡ ይህን ፡ ሰምቶ ፡ ለዚህ ፡ ይጽፋል ።

ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አቡሃ ፡ ለምሕረት ፡ ወአምላካ ፡ ለኵሉ ፡ ትፍሥሕት ፡ ዘእስተፍሥሐነ ፡ እምኵሉ ፡ ሕማምነ ፡ ከመ ፡ ንክሀል ፡ አስተፍሥሖቶሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ሕሙማን ፡ በውእቱ ፡ ፍሥሓነ ፡ ዘእስተፍሥሐነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይላል ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፫-፩ ።)

እስመ ፡ ይደሉ ፡ ይኩን ፡ ነገርክሙ ፡ አሙኒ ፡ እወ ፡ እወ ፡ ወአሙኒ ፡ አልቦ ፡ አልቦ ። ጻድቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወኢኮነ ፡ ሐሰተ ፡ ቃልነ ፡ ወኢተቶስሐ ፡ እወ ፡ ወአልቦ ። እስመ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘንሕነ ፡ ሰበክነ ፡ ለክሙ ፡ አነ ፡ ጳውሎስ ፡ ወስልዋኖስ ፡ ወጢሞቴዎስ ፡ ኢኮነ ፡ እወ ፡ ወእልቦ ። ዳዕሙ ፡ እወ ፡ ኮነ ፡ በእንቲአሁ ፡ ይላል ። ( ምዕራፍ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ፡ እስከ ፡ ፳ ።)

ወበጺሕየ ፡ ጢሮአዳ ፡ ውስተ ፡ ትምህርቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ ተከሥተ ፡ ሊተ ፡ ፍኖተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይላል ፡ (ምዕ ፡ ፪ ፡ ፲፪ ።)

ወብነ ፡ ዝንቱ ፡ መዝገብ ፡ ውስተ ፡ ንዋየ ፡ ልሕኵት ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ዕበየ ፡ ኃይል ፡ ዘእምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይላል ። (ምዕ ፡ ፬ ፡ ፯ ።)

እፉን ፡ ክሡተ ፡ ለክሙ ፡ አ ፡ ሰብአ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ወርኅብ ፡ ልብነ ፡ ይላል ። (ምዕ ፡ ፮ ፡ ፲፪ ።)

ከዚያም ፡ ወእንግረክሙ ፡ አንቲነ ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘተውህበ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘመቄዶንያ ፡ ይላል ። (ምዕ ፡ ፰ ፡ ፩ ።)

ወይእዜሰ ፡ ግበሩኒ ፡ ወፈጽሙኒ ፡ ይላል ።( ፰ ፡ ፲፩ ።)

እመሰ ፡ ይኤድመክሙ ፡ እጽምእቶሙ ፡ ለአብዳን ፡ አንዘ ፡ ጠቢባን ፡ ወነባብያን ፡ አንትሙ ፡ ይላል ፡ (ምዕ ፡ ፲፩ ፡ ፲፱ ።)

ክዚህ ፡ በኋላ ፡ እሱ ፡ እያጸናው ፡ በተቀበለው ፡ መከራ ፡ ሲመካ ፡ አልምቶ ፡ አስፍቶ ፡ ይጽፋል ። ወእመሰ ፡ ይደሉ ፡ ተመክሖ ፡ አነሂ ፡ እትሜካሕ ፡ ይላል ። (ምዕ ፡ ፲፩ ፡ ፴ ።)

ወናሁ ፡ ይረትዕ ፡ ሊተ ፡ ተመክሖ ፡ ወባሕቱ ፡ ኢኮነ ፡ ሠናየ ፡ ብሎ ፡ ንግባዕ ፡ ካዕበ ፡ ወንዘክር ፡ ራእየ ። ዘከሠተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይላል ። (ምዕ ፡ ፲፪ ፡ ፩ ።)

የጻፈበት ፡ ሀገር ፡ ፊልጵስዩስ ፡ ክታብ ፡ ወሳጅ ፡ ቲቶና ፡ ሉቃስ ።

## ምዕራፍ ፡ ፩ ።

## ክፍል ፡ ፩ ።

፩ ፡ እምጳውሎስ ፡ ሐዋርያሁ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ።

በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸንቼ ፡ ብገኝ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ክሾመኝ ።

እንድም ፡ በፈቃደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ አጸና ፡ ዘንድ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ነገር ፡ ክማስቀምር ፡ ከኔ ፡ ከጳውሎስ ፡ የተላከች ፡ መልእክት ።

ወጢሞቴዎስ ፡ እኁነ ።

ክወንድማችን ፡ ከጢሞቴዎስ ፡ የተላከች ፡ መልእክት ፡ (ሐተታ) ፡ በጽሕፈትም ፡ በድርሰትም ፡ እግዞት ፡ አይደለም ፡ ስለትሕትና ፡ ያነግዋል ።

ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘማኅበረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘሀገረ ፡ ቆሮንቶስ ።

ማኅበረ ፡ ጳውሎስ ፡ ማኅበረ ፡ አጵሎስ ፡ ማኅበረ ፡ ኬፋ ፡ ሳይደሉ ፡ ማኅበረ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሚባሉ ፡ በቆሮንቶስ ፡ ላሉ ፡ ምእመናን ፡ ትድረስ ፡ (ሐተታ) ፡ አንድቀዳማዊ ፡ ቆሮንቶስ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፪ ።)

ወለኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ፡ እለ ፡ ሀገረ ፡ ካይያ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፳ ።)

በአካይያ ፡ አውራጃ ፡ ላሉትም ፡ ኹሉ ፡ ትድረስ ።

www.ethiopianorthodox.org

፪ ፡ ሰላም ፡ ለክሙ ።
ቸር ፡ እላችሁን ።

ወጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡነ ፡ ወእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፯) ።
የእግዚአብሔር ፡ አብና ፡ የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋው ፡ ይደርባችሁ ፡ ቸርነቱ ፡ ይደረግላችሁ ።

፫ ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የባሕርይ ፡ አባቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

አቡሃ ፡ ለምሕረት ።
የምሕረት ፡ መገኛ ፡ (ሐተታ) ፡ ልጁ ፡ ከአባቱ ፡ እንዲገኝ ፡ ምሕረትም ፡ ከርሱ ፡ ትገኛለችና ።

ወአምላክ ፡ ለኵሉ ፡ ትፍሥሕት ፡ (ሮሜ ፡ ፲፭ ፡ ፭) ።
የፍጹም ፡ ተስፋ ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

፬ ፡ ዘአስተፍሥሐነ ፡ እምኵሉ ፡ ሕማምነ ፡ ከመ ፡ ንክሀል ፡ አስተፍሥሖቶሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ሕሙማን ፡ በውእቱ ፡ ፍሥሓ ፡ ዘአሥተፍሥሐነ ፡ እግዚአብሔር ።

እኛን ፡ ደስ ፡ ባሰኘበት ፡ ደስታ ፡ ኀዙናንን ፡ ደስ ፡ ያሰኘናቸው ፡ ዘንድ ፡ በመከራው ፡ ኹሉ ፡ ደስ ፡ ያሰኘን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ፡ (ሐተታ) ፡ ባደባባይ ፡ ገፈው ፡ ገርፈው ፡ ሲያሰወጧቸው ፡ እንደተኾሙ ፡ እንደተሸሸሙ ፡ ደስ ፡ እያላቸው ፡ ይሔዱሉና ፤ ወፅኡ ፡ እምዐውድ ፡ እንዘ ፡ ይትፌሥሑ ፡ እስመ ፡ ከረሉሙ ፡ ጸጋ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከመ ፡ ያኅሥርዎሙ ፡ በእንተ ፡ ስሙ ፡ እንዲል ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፭ ፡ ፵፩) ።

እንድም ፡ እኛን ፡ ወደመከራው ፡ አግብቶ ፡ ከመከራው ፡ አውጥቶ ፡ ጸጋውን ፡ ሰጥቶ ፡ ደስ ፡ ባሰኘበት ፡ ደስታ ፤ ኀዙናንን ፡ ወደመከራው ፡ አግብተን ፡ ከመከራው ፡ አውጥተን ፡ ጸጋውን ፡ አሰጥተን ፡ ደስ ፡ እናሰኛቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደመከራው ፡ አግብቶ ፡ ከመከራው ፡ አውጥቶ ፡ ጸጋውን ፡ ሰጥቶ ፡ ደስ ፡ ያሰኘን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

፭ ፡ ወበከመ ፡ በዝኀ ፡ ሕማሙ ፡ ለክርስቶስ ፡ ላዕሌነ ፡ ከማሁ ፡ ይፈደፍድ ፡ ፍሥሓነ ፡ በክርስቶስ ፡ (መዝ ፡ ፺፫ ፡ ፲፱ ፡ ፲፱) ።
የክርስቶስ ፡ መከራ ፡ በኛ ፡ እንደበዛ ፡ መጠን ፡ እንድም ፡ (ብዙኀ ፡ ሕማሙ ፡ ) እንጂ ፡ ክርስቶስ ፡ መከራ ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ በክርስቶስ ፡ ደስታ ፡ ይበዛልና ።

፮ ፡ ወእመኒ ፡ ሐመምነ ፡ ከመ ፡ አንትሙ ፡ ትድኅኑ ፡ (ም ፡ ፬ ፡ ፲፭ ፡ ፲፯) ።
መከራም ፡ ብንቀበል ፡ እናንተ ፡ ከመከራ ፡ ነፍሱ ፡ ትድኑ ፡ ዘንድ ፡ ነው ። ወትትፌሥሑ ።
እናንተን ፡ ደስ ፡ ይላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ወእመኒ ፡ ተፈግሕነ ፡ ንሕነ ፡ ከመ ፡ አንትሙ ፡ ትትፌሥሑ ።
እኛም ፡ በመከራው ፡ ደስ ፡ ቢለን ፡ እናንተንም ፡ ደስ ፡ ይላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።
እንድም ፡ እኛ ፡ ወደመከራው ፡ ገብተን ፡ ከመከራው ፡ ወጥተን ፡ ጸጋውን ፡ አግኝተን ፡ ደስ ፡ ቢለንም ፡ እናንተም ፡ ወደመከራው ፡ ገብታችሁ ፡ ከመከራው ፡ ወጥታችሁ ፡ ጸጋውን ፡ አግኝታችሁ ፡ ደስ ፡ ይላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

ወትጸንዑ ፡ በትዕግሥቱ ፡ ለውእቱ ፡ ሕማም ፡ ዘቦቱ ፡ ነሐምም ፡ ንሕነኒ ።
መከራውን ፡ በመታገሥ ፡ ብንጸናም ፡ እናንተ ፡ እኛ ፡ ታግሠን ፡ የተቀበልነውን ፡ መከራ ፡ በመታገሥ ፡ ትጸኑ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

፯ ፡ ወትውክልትነኒ ፡ ጽኑዕ ፡ በእንቲአክሙ ።
እናንተን ፡ ስለማስተምር ፡ ስለናንት ፡ ተስፋችን ፡ (ፍጹም) ፡ የተረዳ ፡ ነው ። ጽኑሕ ፡ ይላል ፡ ዋጋችን ፡ ይቆየናል ።

ወበከመ ፡ ዓረይክሙ ፡ ሕማመነ ፡ ከማሁ ፡ ተኀብሩ ፡ በፍሥሓነኒ ።
በመከራም ፡ እንደመሰላችሁን ፡ በክብርም ፡ ትመስሉናላችሁ ።

፰ ፡ ወእፈቅድ ፡ ታእምሩ ፡ አኃዊነ ፡ በከመ ፡ ሐመምነ ፡ በዕስያ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፱ ፡ ፳፫) ።
ሐመምነ ፡ ሐመምነ ፡ ትላለህ ፡ እንጂ ፡ ማን ፡ ያውቅልሃል ፡ ትለኝ ፡ እንደኾነ ፤
ወንድሞቻችን ፤ በእስያም ፡ መከራ ፡ እንደተቀበልን ፡ ልታውቁ ፡ እወዳለሁ ፡ ይህስ ፤ ያንዱን ፡ ላንዱ ፡ እያመጣም ፡ ብሎ ፡ በእስያ ፡ በተቀበልነው ፡ መከራ ፡ እንደመሰላችሁን ፡ በክብርም ፡ እንድትመስሉን ፡ ልታውቁ ፡ እወዳለሁ ።

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ፡ ፈድፋደ ፡ እምእምጣነ ፡ ኃይልነ ፡ አመንደቡን  እስከ ፡ ቀበጽናት ፡ ለሕይወትነ ፡ ወአጥባዕነ ፡ ለሞት ።
ለሕይወት ፡ እንኖራለን ፡ ማለትን ፡ ትተን ፡ እንሞታለን ፡ በማለት ፡ እስክንጸና ፡ ድረስ ፡ ደርሰን ፡ ከመከራችን ፡ የወጣ ፡ ብዙ ፡ መከራ ፡ አጽንተውብናልና ።

ከመ ፡ ኢንትአመን ፡ በርእስነ ፡ ዘእንበለ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘያሐይዎሙ ፡ ለምውታን ።
ሙታን ፡ ሕሊናን ፡ ትንሣኤ ፡ ሕሊና ፤ ሙታን ፡ ሥጋን ፤ ትንሣኤ ፡ ሥጋ ፡ በሚያስነሣቸው ። በእግዚአብሔር ፡ እንጂ ፡ በራሳችን ፡ እንዳንተማመን ፡ (ሐተታ) ፤ ፍጡር ፡ የእድሜውን ፡ ልክ ፡ ዐውቃለሁ ፡ ማለት ፡ እሞታለሁም ፡ እለማለት ፡ በራስ ፡ መተማመን ፡ ነውና ።

፲ ፡ ዘአድኃነነ ፡ እመጠነዝ ፡ ሞት ።
ከዚህን ፡ ያህል ፡ መከራ ፡ ባዳነን ።

ወዓዲ ፡ ኪያሁ ፡ ንትአመን ፡ ከመ ፡ ያድኅነነ ። (ጢሞ ፡ ፩ ፡ ፲፰ ።)
እንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ከሚመጣው ፡ መከራ ፡ እንዲያድነን ፡ እናምናለን ።

እንዘ ፡ ትረድኡነ ፡ አንትሙኒ ፡ በጸሎትክሙ ።
በምትጸልዩት ፡ ጸሎት ፡ እናንተ ፡ እያዘናችሁልን ፡

፲፩ ፡ ከመ ፡ ንርከብ ፡ ሞገሰ ፡ በጸሎተ ፡ ብዙኃን ።
ባንድነት ፡ ማኅበር ፡ በምትጸልዩት ፡ ጸሎት ፡ ድኅነትን ፡ እናገኝ ፡ ዘንድ ፡ እንዘ ፡ ትረድኡነ ፡ በጸሎትክሙ ፡ ላለው ፡ (ሐተታ) ፡ ፍጹም ፡ ስለትሕትና ፡ ወጣንያኑን ፡ ትረድኡነ ፡ አለ ፡ አስተብቍዖ ፡ ለማስተማር ፡ ለማለበም ፡ ጸሎተ ፡ ማኅበር ፡ ይጠቅማልና ።

ወአንትሙኒ ፡ ትትአኰቱ ፡ በኀበ ፡ ኵሉ ።
እናንተም ፡ በሰው ፡ ኹሉ ፡ ዘንድ ፡ ለመመስገን ፡ የቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ ለራሳቸው ፡ ተጠቅመው ፡ መምህሮቻቸውን ፡ ይጠቅማሉ ፡ ተብላችሁ ።

፲፪ ፡ እስመ ፡ ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ትምክህትነ ።
መመኪያችን ፡ ይህች ፡ ናትና ።

ወስምዓ ፡ ግእዛንነ ፡ (ዕብ ፡ ፲፫ ፡ ፲፰ ፡ ማቴ ፡ ፲ ፡ ፲፮ ።)
የነጻነታችንም ፡ ምስክር ፡ ይህች ፡ ናትና ፤ እንድም ፡ ትምክህትነ ፡ ስምዓ ፡ ግዕዛንነ ፡ የነጻነታችን ፡ ምስክር ፡ የምትኾን ፡ መመኪያችን ፡ ይህች ፡ ናትና ፡ ፡ አለ ፡ ሃይማኖት ፡ ናትና ፡ ዓዲ ፡ ንትአመን ።

በምሕረቱ ፡ ወበተመይጦቱ ።
በቸርነቱ ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ በመመለሱ ። እንድም ፡ በቸርነቱ ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ በመመለሱ ፡ የነፃነታችን ፡ ምስክር ፡ የምትኾን ፡ መመኪያችን ፡ ይህች ፡ ናትና ፡ አለ ፡ ጸሎት ፡ ናትና ፡ ንርከብ ፡ ሞገሰ ፡ በጸሎተ ፡ ብዙኃን ፡ ላለው ፡ ወበጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንሶሰውነ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ማንሻ ።

ወበጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንሶሰውነ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ወኢኮነ ፡ በትምህርቲ ፡ ሥጋ ።
በቸርነቱ ፡ ከመዓት ፡ ወደ ፡ ምሕረት ፡ በመመለሱ ፡ የነጻነታችን ፡ ምስክር ፡ የምትኾን ፡ መመኪያችን ይህች ፡ ናትና ፡ አለ ፡ ወንጌል ፡ ናትና ፡ አንሶሰውነ ። እንድም ፡ ሥጋዊ ፡ ደማዊ ፡ ትምህርት ፡ አሪትን ፡ ያይደለ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ወንጌልን ፡ በማስተማር ፡ ኖርን ።

ወፈድፋደሰ ፡ በኀቤክሙ ።
ይልቁንም ፡ በናንተ ፡ ዘንድ ፡ አለ ፡ ወነበረ ፡ ጳውሎስ ፡ በቆሮንቶስ ፡ ዓመተ ፡ ወስድስተ ፡ አውራኀ ፡ እንዲል ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፰ ፡ ፲፩ ።)
ዓመት ፡ ከመንፈቅ ፡ ኑሩዋልና ። አንድም ፡ ኹለት ፡ ከታብ ፡ ጽፏልና ።

እስመ ፡ ዛቲ ፡ ይእቲ ፡ ትምክህትነ ።
በቸርነቱ ፡ ከመዓት ፡ ወደምሕረት ፡ በመመለሱ ፡ መመኪያችን ፡ የነፃነታችን ፡ ምስክር ፡ ይህች ፡ ናትና ፡ አለ ፡ ማስተማር ፡ ዋጋ ፡ አለመብላት ፡ ናትና ።

ወበጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንሶሰውነ ፡ ውስተ ፡ ዓለም ፡ ወኢኮነ ፡ በትምህርተ ፡ ሥጋ ።
እንበላበት ፡ እንጠጣበት ፡ ብለን ፡ ያይደለ ፤ በጸጋ ፡ ዘነሣእክሙ ፡ በጸጋ ፡ ሀቡ ፡ በከንቱ ፡ ዘነሣእክሙ ፡ በከንቱ ፡ ሀቡ ፡ ባለው ፤ ዋጋ ፡ ባለመብላት ፡ ኖርን ።

ወፈድፋደሰ ፡ በኀቤክሙ ።
ይልቁንም ፡ በናንተ ፡ ዘንድ  ፡ አለ ፡  ከሌላ ፡ የመጣለትን ፡ እየበላ ፡ አስተምሩዋቸዋልና ። ወባዕደሰ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቀሠጥኩ ፡ ወነሣእኩ ፡ ስሲሳይየ ፡ ከመ ፡ እትለአክሙ ፡ ወአመኒ ፡ ሀሎኩ ፡ ኀቤክሙ ፡ ኢተሰቈቊ ፡ ንዋየክሙ ፡ ወኢተአጽወተኒ ፡ ዛቲ ፡ ፍሥሓየ ፡ በደወለ ፡ አካይያ ፡ ብሎ ፡ አሁን ፡ እንዲያ መጣው ፡ (፲፩ ፡ ፳ ፡ ፲፩ ።)

www.ethiopianorthodox.org

፲፫ ፡ እስመ ፡ አልቦ ፡ ዘንጽሕፍ ፡ ኀቤክሙ ።
የማታውቁትን ፡ የማትረዱትን ፡ የምንጽፍላችሁ ፡ አይደለምና ።
ዘእንበለ ፡ ዘታነብቡ ፡ ወዘተአምሩ ፡ ወዘይትዓወቀክሙ ።
የምትመለከቱትን ፡ የምታውቁትን ፡ የሚረዳችሁን ፡ ነው ፡ እንጂ ።
እስመ ፡ አልቦ ፡ ዘንጽሕፍ ፡ ኀቤክሙ ።
እንድም ፡ ይህን ፡ አድርጉልን ፡ ብለን ፡ የምንጽፍላችሁ ፡ የለምና ።
ዘእንበለ ፡ ዘታነብቡ ፡ ወዘተአምሩ ፡ ወዘይትዓወቀክሙ ።
የምትመለከቱትን ፡ የምታውቁትን ፡ የምትረዱትን ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ወእትአመን ፡ ከመ ፡ ለዝሉፉ ፡ ተአምርዎ ፡ ለዝንቱ ።
ይህንም ፡ ፈጽሞ ፡ እንድታውቁ ፡ እምናለሁ ።

፲፬ ፡ በከመ ፡ አእመርክሙኒ ፡ እምእሐዱ ፡ ገጽ ።
ከቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ኾናችሁ ፡ እንዳወቃችሁን ፡ መጠን ፡ መመኪያችሁ ፡ እንደኾነ ፡ ዘንድ ፤ እንድም ፡ ከቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ኾነን ፡ መመኪያችሁ ፡ እንደኾነ ፡ መጠን ፡ እንዳወቃችሁን ፡ ዘንድ ፡ ፈጽሞ ፡ እንድታውቁት ፡ እምናለሁ ፡ ወከማሁ ፡ ማንሻ ።
ወከማሁ ፡ እንትሙኒ ፡ ምክህነ ፡ በዕለተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፲፪ ።)
ከቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ኾናችሁ ፡ እንዳወቃችሁን ፡ መጠን ፡ እኛ ፡ መመኪያችሁ ፡ እንደኾነ ፡ እናንተም ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሚመጣበት ፡ በዕለተ ፡ ምጽአት ፡ መመኪያችን ፡ ናችሁ ፡ እኮኑ ፡ ሐምስ ፡ መካልየ ፡ ወሀብክኒ ፡ ወናሁ ፡ ኀምስ ፡ መካልይ ፡ ዲቤሆን ፡ ዘረባሕኩ ፡ ብለን ፡ ሰናበረ ክታችሁ ። (ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፳-፳፱ ።)

፲፭ ፡ ወበዝንቱ ፡ ፍሥሓ ፡ ተእሚንየ ፡ መከርኩ ፡ እምጻእ ፡ ኀቤክሙ ።
በዚህም ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ ደስ ፡ እንዲለኝ ፡ አውቄ ፡ ወደናንት ፡ ልመጣ ፡ ወደድሁ ።
በቀዳሚ ፡ ከመ ፡ ትርከቡ ፡ ጸጋ ፡ ምክዕቢተ ።
(በቀዳሚን ፡ አቆይ) ፡ እጽፍ ፡ ክብር ፡ ታገኙ ፡ ዘንድ ፡ እለ ፡ ኹለት ፡ ክታብ ፡ መጻፍ ፡ ማስተማር ፡ ዋጋ ፡ አለመብላት ።

፲፮ ፡ ወእሑር ፡ መቄዶንያ ።
(በቀዳሚ ፡ እሑር ፡ መቄዶንያ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ) ፡ በመጀመሪያ ፡ ወደ ፡ መቄዶንያ ፡ እሔድ ፡ ዘንድ ።
ወእምህየ ፡ እሠወጥ ፡ ኀቤክሙ ።
ከዚያም ፡ ወደናንት ፡ እመለስ ፡ ዘንድ ።
ወአንትሙ ፡ ትፈንዉኒ ፡ ለምድረ ፡ ይሁዳ ።
እናንተም ፡ ወደምድረ ፡ ይሁዳ ፡ ሸኝታችሁ ፡ ትሰዱኝ ፡ ዘንድ ።

፲፯ ፡ ዘንተ ፡ እንከ ፡ ዘመከርኩ ፡ ቦኑ ፡ እንጋ ፡ ከመ ፡ እብድ ፡ ዘገበርኩ ።
ይህን ፡ የመከርሁ ፡ በውኑ ፡ ያላዋቂ ፡ ሥራ ፡ ሠራሁን ። እንድም ፡ እንደ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ ኾንኩን ።
ወቦኑ ፡ ዘእመክር ፡ ሕገ ፡ ሰብእ ፡ እመክር ።
ባስተምርስ ፡ የሰው ፡ ሥርዓት ፡ አስተምራለሁን ፡፡ እንድም ፡ እንደቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ አስተምራለሁን ።
እስመ ፡ ይደሉ ፡ ይኩን ፡ ነገርክሙ ፡ እመኒ ፡ እወ ፡ እወ ፡ ወእመኒ ፡ አልቦ ፡ አልቦ ፡
ነገራችሁ ፡ እውነት ፡ ቢኾን ፡ እውነት ፡ ሐሰት ፡ ቢኾን ፡ ሐሰት ፡ ሊኾን ፡ ይገባል ፡ እኮን ፡ (አለ) ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ትሉት ፡ እንደኾነ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ትሉትም ፡ እንደኾነ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ልትሉት ፡ ይገባል ፡ እኮን ።

፲፰ ፡ ጻድቅ ፡ እግዚአብሔር ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፱ ።)
ልጄን ፡ በሥጋ ፡ ወስኜ ፡ እሰዳለሁ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እውነተኛ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ።
ወኢኮነ ፡ ሐሰተ ፡ ቃልነ ።
የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ብለን ፡ የምናስተምረውም ፡ ትምህርት ፡ ሐሰት ፡ አይደለም ።
ወኢተቶስሐ ፡ እወ ፡ ወአልቦ ።
አንድ ፡ ጊዜ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ማለት ፡ አልተቀላቀለበትም ።

፲፱ ፡ እስመ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘንሕነ ፡ ሰበክነ ፡ ለክሙ ፡ አነ ፡ ጳውሎስ ፡ ወስ ልዋኖስ ፡ ወጢሞቴዎስ ፤ ኢኮነ ፡ እወ ፡ ወአልቦ ።
(ዘንሕነ ፡ ጳውሎስ ፤ ወስልዋኖስ ፡ ወጢሞቴዎስ ፡ ) ፡ እኔ ፡ ጳውሎስ ፤ ስልዋኖስ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ያስተ

www.ethiopianorthodox.org

ያገናኘችው ፡ የእግዚአብሔር ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ የሚባል ፡ አይደለምና ።

ዳዕሙ ፡ አወ ፡ ኮነ ፡ በእንቲአሁ ።
ስለርሱ ፡ ወኢተቶሰሐ ፡ አወ ፡ ወአልቦ ፡ እንዳልሁ ። የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፳ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘአሰፈወ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኮነ ፡ አሙነ ፡ በክርስቶስ ።
(ዘአሰፈወ ፡ በክርስቶስ ፡ ኮነ ፡ አሙነ ፡ በክርስቶስ ) ፡ እግዚአብሔር ፡ በነቢያት ፡ አድሮ ፡ ስለክርስ ቶስ ፡ ያናገረው ፡ ተስፋ ፡ በክርስቶስ ፡ ተፈጽሟልና ።

ወበእንተዝ ፡ ቦቱ ፡ ወበእንቲአሁ ፡ አሚነ ፡ ስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነሀብ ። (ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፫ ፡ ፲፬ ፡)
ቦቱና ፡ በእንቲአሁ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ስለዚህ ፡ በሱ ፡ አምነን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ (አሚነ፡ ስብሐት) ፡ ምስጋና ፡ ያለው ፡ አዎታ ፡ (ስብሐተ ፡ አሚን) ፡ አዎታ ፡ ያለው ፡ ምስጋና ፡ እናቅርብ ። አንድም ፡ ቦቱና ፡ በእንቲአሁ ፡ በየራሱ ፤ እሱ ፡ ስለካሰልን ፡ በሱ ፡ አምነን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ያለው ፡ አዎታ ፤ አዎታ ፡ ያለው ፡ ምስጋና ፡ እናቅርብ ።

፳፩ ፡ ወእግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ዘያጸንዓነ ፡ ምስሌክሙ ፡ በአሚን ፡ በክርስቶስ ።
ከእናንተ፡ ጋራ ፡ በክርስቶስ ፡ በማመን ፡ ከናንተ ፡ ጋራ ፡ የሚያጸናን ፡ እሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ፡ ነሀብ ፡ ላለው ።

ዘቦቱ ፡ ቀብዐነ ።
እኛን ፡ ያከበረበት ።

ወዐተበነ ፡ (፩ ፡ ዮሐ ፡ ፪ ፡ ፳፯ ።)
ከኢአማንያን ፡ የለየበት ፡ ራሱን ፡ ያስመሰለበት ።

፳፪ ፡ ወወሀበነ ፡ ዐረቦነ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ውስተ ፡ ልብነ ፡ (ም ፡ ፭ ፡ ፭ ፡ ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፲፯ ፡ ኤፌ ፡ ፩ ፡ ፲፬ ።)
የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ፈለግ ፡ በልቡናችን ፡ የሣለበት ።

፳፫ ፡ ወአነ ፡ አስምዮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ነፍስየ ። (ም ፡ ፲፩ ፡ ፴፩ ፡ ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፱ ።)
እኔ ፡ በሰውነቴ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ምስክር ፡ እጠራበታለሁ ።

ከመ ፡ በምሒከ ፡ ዚአክሙ ፡ ኢመጻእኩ ፡ ቆሮንቶስ ።
ወደቆሮንቶስ ፡ ያልመጣሁ ፡ ለናንተ ፡ በማዘን ፡ በመራራት ፡ እንደ ኾነ ፡ (አለ) ፡ በነፋስ ፡ እንዳልሰቀ ላችሁ ፤ በሌጊዎን ፡ እንዳልነጻችሁ ፡ እንደኾነ ።

፳፬ ፡ ወአኮሰ ፡ ዘናጌብረክሙ ፡ ትእመኑ ።
ከዚህ ፡ ቀደም ፤ ያላመናችሁ ፡ ኾኖ ፡ አንግዴህ ፡ ታምኑ ፡ ዘንድ ፡ ግድ ፡ የምንላችሁ ፡ አይደለም ።

ዳዕሙ ፡ ንረድአክሙ ፡ ለገቢረ ፡ ፍሥሓክሙ ።
ደስ ፡ ብሏችሁ ፡ ሥራችሁን ፡ ትሠሩ ፡ ዘንድ ፡ እናጸናችኋለን ፡ እንጂ ።

እስመ ፡ በአሚን ፡ ቆምክሙ ።
በሃይማኖት ፡ ጸንታችኋልና ።

ወአዋባዕክሙ ፡ በሃይማኖት ፡ (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፭ ፡ ፫ ።)
በሃይማኖት ፡ ጸንታችሁ ፡ መከራውን ፡ ለመቀበል ፡ ጨክናችኋልና ።

## ምዕራፍ ፪ ።

### ክፍል ፡ ፪ ።

፩ ፡ ወዘንተ ፡ እንከ ፡ መከርኩ ፡ በነፍስየ ፡ ኢይምጻእ ፡ ትኩዝየ ፡ ኀቤክሙ ።
ያዘንሁ ፡ የተከዝሁ ፡ ኾኜ ፡ ወደናንተ ፡ እንዳልመጣ ፡ በልቡናዬ ፡ ይህን ፡ መከርሁ ።

፪ ፡ ወአመሰ ፡ አነ ፡ አተከዝኩክሙ ፡ መኑ ፡ ያስተፌሥሐኒ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘአነ ፡ አተከዝክዎ ።
ትኩዝየን ፡ ይዞ ፡ አንተ ፡ ሌላውን ፡ ብታሳዝን ፡ እንጂ ፡ አንተን ፡ ማን ፡ ያሳዝንሃል ፡ ትሉኝ ፡ እንደ ኾነ ፡ ባሳዝናችሁም ፡ እኔ ፡ ያሳዘንኳችሁ ፡ ማሳዘን ፡ ደስ ፡ ቢያሰኝልኝ ፡ እንጂ ፡ ሌላ ፡ ማን ፡ ደስ ፡ ያሰ ኛልኛል ፡ (አለ) ፡ ለአስተዋፅኦ ፡ እንድትተጉ ፤ ለምግባር ፡ ለትሩፋት ፡ እንድትፋከሩ ፤ አነ ፡ ዘጳውሎስ፡ ወአነ ፡ ዘአጵሎስ ፤ ወአነ ፡ ዘኬፋ ፤ ማለትን ፡ እንድትተው ። ያባቱን ፡ሚስት ፡ የነሣውን ፡ የመምህሩን ሹመት ፡ የተሾመውን ፡ እንድትለዩ ፡ አድርጉ ። አንድም ፡ ኢይምጻእን ፡ ይዞ ፡ ብትመጣስ ፡ ባትመጣስ ፡

www.ethiopianorthodox.org

ኃዘኑ ፡ ቀርቶልናል ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ ባሳዝናችሁም ፡ ያሳዘንኋችሁ ፡ እኔ ፡ ደስ ፡ ባሰኛችሁ ፡ እንጂ ፡
ሌላ ፡ ማን ፡ ደስ ፡ ያሰኘልኛል ።

፫ ፡ ወዘኒ ፡ ዘጸሐፍኩ ፡ ለክሙ ፡ ከመ ፡ መጺእየ ፡ ኢይርከበኒ ፡ ኃዘን ፡ በዘህለወኒ ፡ እትፌሣሕ ፤ (ም ፡ ፲፪ ፡ ፳፩)
ይህንም ፡ የጻፍኩላችሁ ፡ ወደናንተ ፡ በመጣሁ ፡ ጊዜ ፡ ስለደስታዬ ፡ ፈንታ ፡ ኃዘን ፡ እንዳያገኘኝ ፡ ነው
ተአሚንየ ፡ በኵልክሙ ፡ ከመ ፡ ፍሥሐ ፡ ዚአየ ፡ ዘኵልክሙ ፡ ውእቱ ።
የኔ ፡ ደስታ ፡ የናንተ ፡ ደስታ ፡ የኔ ፡ ኃዘን ፡ የናንተ ፡ ኃዘን ፡ እንደኾነ ፡ ዐውቄ ፡ ኢይርከበኒ ።

፬ ፡ እስመ ፡ እምነ ፡ ብዙኅ ፡ ሕማም ፡ ወኀዘነ ፡ ልብ ፡ ጸሐፍኩ ፡ ዘንተ ፡ በብዙኅ ፡ አንብዕ ።
ከብዙ ፡ መከራ ፡ ከብዙ ፡ ኃዘን ፡ የተነሣ ፡ ይህነን ፡ በብዙ ፡ ዕንባ ፡ ጽፌላችኋለሁ ፡ (አለ) ፡ ቀለ
ሙን ፡ በዕንባው ፡ በጥብጦ ፡ ጽፎታልና ። አንድም ፡ እያለቀሰ ፡ ጽፎታልና ።
ወአኮ ፡ ከመ ፡ ትተክዙ ።
እንዲህም ፡ ማለቴ ፡ ታዝኑ ፡ ዘንድ ፡ አይደለም ።
ዳዕሙ ፡ ከመ ፡ ታእምሩ ፡ እፍቀሮትየ ፡ ከመ ፡ ፈድፋደ ፡ አፈቅረክሙ ።
ፈጽሞ ፡ እንድወዳችሁ ፡ ጽና ፡ ፍቅሬን ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፭ ፡ ወዘኒ ፡ አተከዘኒ ፡ አኮ ፡ ኪያየ ፡ ዘያቴክዝ ።
እኔንም ፡ ያሳዘነ ፡ እኔን ፡ ብቻ ፡ ያሳዘነ ፡ አይደለም ።
ዳዕሙ ፡ ኵልክሙ ፡ ዘእንበለ ፡ እሐዱ ፡ ኀብር ።
ከናንተ ፡ አንዱ ፡ ሳይቀር ፡ ኹላችሁንም ፡ ያሳዘነ ፡ ነው ፡ እንጂ ። አንድም ፡ ከናንተ ፡ አንድ ፡ ወገን፡
ከሚኾን ፡ ከቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ በቀር ፡ ኹላችሁንም ፡ ያሳዘነ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ወይእዜኒ ፡ ኢያከብድ ፡ ቃልየ ፡ ላዕሌክሙ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፩ ።)
አሁንም ፡ ሥርዓት ፡ አላጸናባችሁም ፡ ነገር ፡ አላበዛባችሁም ።

፮ ፡ ተአክሎ ፡ ለዘከመዝ ፡ ዛቲ ፡ ተግሣጽ ፡ እንተ ፡ ረከበቶ ፡ እምብዙኃን ።
(እንተ ፡ ረከበቶ ፡ እምብዙኃን ፡ ተግሣጽ ፡ እምብዙኃን ፡ ብለህ ፡ ግጠም) ፡ እንዲህ ፡ ላለው ፡ ሰው ፤
ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ የተነሣ ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተለይቶ ፡ ያገኘችው ፡ መከራው ፡ ትበቃዋለች ፤ መለየቱ ፡
ከብዙ ፡ ነውና ፡ ሲለዩት ፡ ብዙ ፡ ኹነው ፡ ነውና ።

፯ ፡ ወዓዲ ፡ ይደሉ ፡ ከመ ፡ ትስረዩ ፡ ሎቱ ፡ ወታስተፍሥሕዎ ፡
ዳግመኛ ፡ ታርቃችሁ ፡ ደስ ፡ ልታሰኙት ፡ ይገባል ።
ከመ ፡ ኢይሰጠም ፡ እምብዝኀ ፡ ኃዘን ፡ ዘከመዝ ።
እንዲህ ፡ ያለ ፡ ቀቢጸ ፡ ተስፋ ፡ ባመጣው ፡ ኃዘን ፡ ባሕር ፡ እንዳይሰጠም ።

፰ ፡ ወበእንተዝ ፡ አስተበቍዐክሙ ፡ አጽንዑ ፡ ተፋቅሮ ፡ ምስሌሁ ።
ስለዚህ ም ፡ ታረቁት ፡ ብየ ፡ እማልዳችኋለሁ ።

፱ ፡ ወበእንተዝ ፡ ጸሐፍኩ ፡ ለክሙ ፡ ከመ ፡ እእምር ፡ ግዕዘክሙ ፡ ለእመሁ ፡ በኵሉ ፡ ትትኤዘዙኒ ።
ስለዚህም ፡ ለዩት ፡ ብላችሁ ፡ ትለዩት ፡ እንደኾነ ፡ ታረቁት ፡ ብላችሁ ፡ ትታረቁት ፡ እንደኾነ ።
እው ፡ አልቦ ። (ም ፡ ፯ ፡ ፲፯ ።)
አንድ ፡ ጊዜ ፡ ታረቁት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለዩት ፡ ይለናልን ፡ ብላችሁ ፡ አይኾንም ፡ ትሉኝም ፡ እንደኾነ፡
ግብራችሁን ፡ አውቅ ፡ ዘንድ ፡ ጻፍኩላችሁ ።

፲ ፡ ወእመቦ ፡ ዘሰረይክሙ ፡ ሎቱ ፡ አነሂ ፡ ሰረይኩ ፡ ምስሌክሙ ፡ ወእመኒቦ ፡ ዘኀደግሙ ፡ ሎቱ ፡ ኀደጉ ፡
ለልየ ፡ በእንቲአክሙ ፡ (ሉቃ ፡ ፲ ፡ ፲፯ ።)

እንታረቀውስ ፡ እንታረቀውስ ፡ እንተ ፡ ያለህ ፡ በፊልጵስዩስ ፡ እኛ ፡ ያለን ፡ በቆሮንቶስ ፡ ማነን ፡ ይዘን
ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ የናንት ፡ መተው ፡ የኔ ፡ መተው ፡ የናንት ፡ መታረቅ ፡ የኔ ፡ መታረቅ ፡ ነው ።

አንድም ፡ እሱ ፡ ታርቆ ፡ የዕርቅ ፡ ዳረጎት ፡ ይልክብናል ፡ እንዳይሉት ፡ እኔስ ፡ የምተወው ፡ እናንት ፡
ብትተውት ፡ ነው ፡ የምታረቀውም ፡ እናንት ፡ ብትታረቁት ፡ ነው ።
በገጹ ፡ ለክርስቶስ ፡
(አጽንዑ ፡ ተፋቅሮ ፡ ምስሌሁ ፡ በገጹ ፡ ለክርስቶስ) ፡ በክርስቶስ ፡ ግብር ፡ ታረቁት ፡ ብዬ ፡ እማልዳ
ችኋለሁ ፡ ከመ ፡ ኢይትዓገለነ ፡ ማንሻ ፡

፲፩ ፡ ከመ ፡ ኢይትዓገለነ ፡ ሰይጣን ። (ሉቃ ፡ ፳፪ ፡ ፴፩ ።)
(በገጹ ፡ ለክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ኢይትዓገለነ ፡ ሰይጣን ፡ ብለህ ፡ ግጠም) ፡ በክርስቶስ ፡ ዳኝነት ፡ ወንድ
ማችነን ፡ ሰይጣን ፡ እንዳይቀማን ።

www.ethiopianorthodox.org

ዘአኮ ፡ ንስሕቶ ፡ ሕሊናሁ ።

የሰይጣንን ፡ ነገሩን ፡ የምንስተው ፡ አይደለምና ፡ ከወንድሞቻችን ፡ አንዱንም ፡ አንዱን ፡ እየነጠቀ ፡ ወደገሃነም ፡ ለማውረድ ፡ እንደኾነ ፡ አንድም ፡ ቢመለስሳ ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ የዚያን ፡ ሰው ፡ ግብሩን፡ የምንስተው ፡ አይደለም ፡ ቢመለስም ፡ እንለየዋለን ።

ወበጺሕየ ፡ ጢሮአዳ ፡ ውስተ ፡ ትምህርቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፳ ፡ ፮ ።)

ለእመሁ ፡ በኵሉ ፡ ትትኤዘዙኒ ፡ አው ፡ አልቦ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ እንታዘዝህስ ፡ እንታዘዝህስ ፡ አንተ ፡ ያለህ ፡ በፊልጵስዩስ ፡ እኛ ፡ ያለን ፡ በቆሮንቶስ ፡ ብትመጣ ፡ አልነበረምን ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ እንዳል መጣስ ፡ የክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ ትምህርት ፡ ወንጌልን ፡ በማስተማር ፡ ጢሮአዳ ፡ በደረስሁ ፡ ጊዜ ።

ተከሥተ ፡ ሊተ ፡ ፍኖተ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፬ ፡ ፳፮ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፮ ፡ ፱ ።)

ትምህርት ፡ ተሰጣኝ ፡ ዕዝነ ፡ ሰማዕያን ፡ ተከፈተልኝ ።

፲፪ ፡ ወኢረከብኩ ፡ ዕረፍተ ፡ ለነፍስየ ።

ለሰውነቴም ፡ ዕረፍትን ፡ አላገኘሁም ።

እስመ ፡ ኢረከብክዎ ፡ ለቲቶ ፡ እኁየ ።

ሰማዕያን ፡ በዝተው ፡ እኔ ፡ በቀኝ ፡ ብኾን ፡ እሱ ፡ በግራ ፡ እኔ ፡ በግራ ፡ ብኾን ፡ እሱ ፡ በቀኝ ፡ ኾኖ ፡ የሚያስተምርልኝ ፡ ቲቶ ፡ ወንድሜን ፡ አላገኘሁትምና ።

ወተፈለጥኩ ፡ እምኔሁ ።

ከሱ ፡ ተለይቼአለሁና ፡ ኢረከብኩ ።

ወሖርኩ ፡ መቄዶንያ ።

(በጺሕየ ፡ ጢሮአዳ ፡ ሖርኩ ፡ መቄዶንያ ፡ ተከሥተ ፡ ሊተ ፡ ፍኖተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብለህ ፡ ግጠም ።)

ወበጺሕየ ፡ ጢሮአዳ ፡ ውስተ ፡ ትምህርቱ ፡ ለክርስቶስ ።

ጢሮአዳ ፡ ደርሼ ፡ መቄዶንያ ፡ በኼድኩ ፡ ጊዜ ፡ ትምህርት ፡ ተሰጠኝ ፤ ዕዝነ ፡ ሰማዕያን ፡ ተከፈተልኝ። አንድም ፡ በቀዳሚ ፡ እሑር ፡ መቄዶንያ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ያውስ ፡ ቢኾን ፡ በፊት ፡ ወደኛ ፡ ባልመ ጣህም ፡ ነበር ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ በፊት ፡ እንዳልመጣስ ፡ የክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ ወንጌልን ፡ በማስተማር፡ ጢሮአዳ ፡ በደረስሁ ፡ ጊዜ ፡ ፍኖት ፡ ለኀበ ፡ አቡሁ ፡ አንቀጽ ፡ ዘመንገስ ፡ ወላዲሁ ፡ የሚባል ፡ ጌታ ፡ ተገለጠልኝ ፡ (አፈ ፡ ወር) ።

ወኢረከብኩ ፡ ዕረፍተ ፡ ለነፍስየ ።

ለሰውነቴም ፡ ዕረፍትን ፡ አላገኘሁም ።

እስመ ፡ ኢረከብክዎ ፡ ለቲቶ ፡ እኁየ ።

ቢጣሉ ፡ የሚያስታርቅልኝ ፡ ከታብ ፡ ወስዶ ፡ የሚሰጥልኝ ፡ ቲቶ ፡ ወንድሜን ፡ አላገኘሁትምና ።

ኢረከብኩ ፡ ወተፈለጥኩ ፡ እምኔሁ ።

ከሱ ፡ ተለይቻለሁና ።

ወሖርኩ ፡ መቄዶንያ ፡ ።

(ተከሥተ ፡ ሊተ ፡ ፍኖተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሖርኩ ፡ መቄዶንያ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ።)

ፍኖት ፡ ለኀበ ፡ አቡሁ ፤ አንቀጽ ፡ ዘመንገለ ፡ ወላዲሁ ፡ የሚባል ፡ ጌታ ፡ በአምሳለ ፡ መኰንን ፡ መቄ ዶንያዊ ፡ ተገልጦ ፡ ኅልፍ ፡ እንተ ፡ መንገሌነ ፡ ለመቄዶንያ ፡ ወነዓ ፡ ርድአነ ፡ አለኝ ፡ (ግብ፡ ሐዋ፡ ፲፮ ፡ ፰፡ ) (ሖርኩ ፡ መቄዶንያ) ፡ ወደመቄዶንያ ፡ ሔድሁ ።

፲፬ ፡ እኩት ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘዘልፈ ፡ ያዐቅበነ ፡ በእግዚእነ ፡ ክርስቶስ ።

ነገር ፡ ግን ፡ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኹልጊዜ ፡ አናንተንም ፡ እኛንም ፡ የሚጠብቀን ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

ወተዐውቀ ፡ በላዕሌነ ፡ መዓዛ ፡ አእምሮቱ ፡ በኵሉ ፡ በሐወርቅ ።

(ተዐውቀ ፡ በኵሉ) ፡ የዕውቀቱ ፡ ዕውቀት ፡ ብሬቱ ፡ መዓዛን ፡ በኛ ፡ ለኹሉ ፡ እንዲታወቅ ፡ ያደረገ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

፲፭ ፡ እስመ ፡ መዓዛ ሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ንሕነ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ።

ፅንዉት ፡ በመዓዛው ፡ እንዲታወቅ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የክርስቶስ ፡ መታወቂያው ፡ እኛ ፡ ነንና ።

በእንተ ፡ እለ ፡ ይድኀኑ ( ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፲፰ ። )

አምነው ፡ ስለሚድኑ ።

ወእለሂ ፡ ይትኀጐሉ ።

ከደው ፡ ስለሚጐዱም ። ኹለቱም ፡ አርአስት ፡ ነው ፡ ለኹለቱም ፡ ያመጣል ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፮ ፡ እስመ ቦ ፡ እለ ፡ ይደልዎሙ ፡ መዓዛ ፡ ሞት ፡ ለሞት ።
ሞት ፡ ሊኾንባቸው ፡ ሞትን ፡ የሚያመጣ ፡ እውቀት ፡ የሚሰጣቸው ፡ አሉና ፡ በአንተ ፡ እለ ፡ ይትኀጐሉ
ወቦ ፡ እለ ፡ ይደልዎሙ ፡ መዓዛ ፡ ሕይወት ፡ ለሕይወት ።
ድኅነት ፡ ሊኾንላቸው ፡ ድኅነትን ፡ ሊያመጣላቸው ፡ ድኅነትን ፡ የሚያመጣ ፡ እውቀት ፡ የሚሰጣቸው
አሉና ፡ በአንተ ፡ እለ ፡ ይድኅኑ ፡ ላለው ።
ወመኑ ፡ ዘይደልዎ ፡ ዝንቱ ። (ም ፡ ፫ ፡ ፩ ፡ ፮ ፡ ሉቃ ፡ ፪ ፡ ፴፬ ።)
ይህ ፡ መዓዛ ፡ ሕይወት ፡ ለሕይወት ፡ ያለው ፡ የሚገባው ፡ ሰው ፡ ማነው ፡ አንድም ፡ (ወለመኑ ፡ ይደሉ ፡
ዝንቱ) ፡ ይህ ፡ መዓዛ ፡ ሕይወት ፡ ለሕይወት ፡ ያለው ፡ ለማን ፡ ይገባል ፡ (ወመኑ ፡ ዘይደሉ ፡ ለዝንቱ) ፡
ለዚህ ፡ መዓዛ ፡ ሕይወት ፡ ለሕይወት ፡ ላለው ፡ የሚበቃ ፡ ማነው ።

፲፯ ፡ እስመ ፡ ኢኮነ ፡ ከመ ፡ ብዙኃን ፡ እለ ፡ ይትሜየንዎ ፡ ለቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በካልእ ፡
ክርስቶስን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወንጌልን ፡ ዲቃላ ፡ ሕግ ፡ በማለት ፡ እንደ ፡ ሚተነኩሉ ፡ እንደቢጽ ፡ ሐሳ
ውያን ፡ አይደለንምና ።
ዳእሙ ፡ በንጽሕ ።
ክርስቶስን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወንጌልን ፡ ዲቃላ ፡ ሕግ ፡ ከማለት ፡ ተከልክለን ፡ እናስተምራለን ፡ እንጂ ።
(እንድም) ።
እሰመ ፡ ኢኮነ ፡ ከመ ፡ ብዙኃን ፡ እለ ፡ ይትሜየንዎ ፡ ለቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በካልእ ።
አንድም ፡ ወንጌልን ፡ መባያ ፡ በማድረግ ፡ እንደሚተነኩሉ ፡ እንደቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ አይደለንምና ።
ዳዕሙ ፡ በንጹሕ ።
ዋጋ ፡ ከመብላት ፡ ተከልክለን ፡ እናስተምራለን ፡ እንጂ ።
ወከመ ፡ ዘመጽአ ፡ እምእግዚአብሔር ፡ ንነግር ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ። (ም ፡ ፩ ፡ ፲፪)
ወበሳድስ ፡ ወርኅ ፡ ተፈነወ ፡ ገብርኤል ፡ መልአክ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲል ፡ (ሉቃ ፡
፩ ፡ ፳፮ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታዝዞ ፡ እንደመጣ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ገብርኤል ፡ እሱ ፡ ወይሰመይ ፡
ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔርነቱን ፡ እንዳስተማረ ። እኛም ፡ ወልደ ፡ እግዚአ
ብሔርነቱን ፡ እናስተምራለን ። አንድም ፡ ወሀሎ ፡ ፩ ፡ ብእሲ ፡ ዘተፈነወ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡
ዘስሙ ፡ ዮሐንስ ፡ እንዲል ፡ (ዮሐ ፡ ፩ ፡ ፮ ፡) ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ታዝዞ ፡ እንደመጣ ፡ እንደ ፡ ዮሐንስ ፡
እሱ ፡ ለልየ ፡ ርኢኩ ፡ ወአነ ፡ ሰማዕቱ ፡ ከመ ፡ ዝንቱ ፡ ወልዱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ (ዮሐ ፡
፩ ፡ ፴፬ ፡) ወልደ ፡ እግዚአብሔርነቱን ፡ እንዳስተማረ ፡ እኛም ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔርነቱን ፡ እናስተምራ
ለን ።
አንድም ፡ ወፃእኩ ፡ እምአብ ፡ ወመጻእኩ ፡ አቡየ ፡ ፈነወኒ ፡ ወአነ ፡ ተፈኖኩ ፡ እንዲል ፡ (ዮሐ ፡ ፰ ፡ ፵፪ ፡)
ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ተልኮ ፡ እንደመጣ ፡ እንደራሱ ፡ እሱ ፡ ለምንት ፡ ትብሉኒ ፡ ትፀርፍ ፡ ልእመ ፡
አቤለከሙ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አነ ፡ ብሎ ፡ (ዮሐ ፡ ፲ ፡ ፴፮ ፡) ወልደ ፡ እግዚአብሔርነቱን ፡ እንዳስ
ተማረ ። እኛም ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ነቱን ፡ እናስተምራለን ፡ እናስተምራለን ፡ እንጂ ፡ ኢኮነ ፡ ላለው ።

## ም ዕ ራ ፍ ፫ ።

፩ ፡ አኃዊነ ፡ ንእኀዝኑ ፡ካዕበ ፡ ይእዜ ፡ ንንግርክሙ ፡ ንወድስ ፡ ርእሰነ ። (ም ፡ ፭ ፡ ፲፪ ።)
ወንድሞቻችን ፡ ዳግመኛ ፡ አሁን ፡ ራሳችንን ፡ እያመሰገን ፡ እንነግራችሁ ፡ ዘንድ ፡ (ንእኀዝኑ) ፡ እንጀ
ምራለን ? ። (ነአኀዝኑ) ፡ እንጀምርን ? ።
ወቦኑ ፡ ዘንፈቅድ ፡ ከመ ፡ እልክቱ ፡ ካልእን ።
ራሳችንንማ ፡ እያመሰገን ፡ እንነግራችሁ ፡ ዘንድ ፡ በውኑ ፡ ራሳቸውን ፡ እንደሚያመሰግኑ ፡ እንደቢጽ ፡
ሐሳውያን ፡ የምንሻው ፡ ነገር ፡ አለን ።?
እስከ ፡ ንጽሐፍ ፡ ኀቤክሙ ፡ በእንቲአነ ፡ መጽሐፈ ።
አንድም ፡ ራሳችንን ፡ አመስግነን ፡ ይህን ፡ አድርጉልን ፡ ብለን ፡ ከታብ ፡ እስከመጻፍ ፡ ድረስ ፡ ደር
ሰን ፡ ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ የምንሻው ፡ ነገር ፡ አለን ፡
አው ፡ ከመ ፡ ትጽሐፉ ፡ እንትሙ ።
ወይስ ፡ እናንተ ፡ ትጽፉልን ፡ ዘንድ ፡ የኛማ ፡ መምህሮቻችን ፡ አዋቆች ፡ ጠንቃቆች ፡ ናቸው ፡ ብላችሁ ፡
፪ ፡ ወለነሰ ፡ መጽሐፍነ ፡ አንትሙ ፡ ይእቲ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፪ ። ፡)
የኛስ ፡ መታወቂያችን ፡ እናንተ ፡ ናችሁ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወጽሑፍት ፡ ውስተ ፡ ልብነ ።
እናንተ ፡ በልቡናችን ፡ ታውቃችኋል ። ውስተ ፡ ልብክሙ ፡ ይላል ፡ በልቡናችሁ ፡ ታውቀናል ።
ወትትዓወቅ ፡ ወያነብባ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ።
ሰው ፡ ኹሉ ፡ ያውቃችኋል ፡ ይመለከታችኋል ።

፫ ፡ ወየአምሩክሙ ፡ ከመ ፡ መልእክተ ፡ ክርስቶስ ፡ አንትሙ ፡ እንተ ፡ ተልእክናሃ ።
እኛ ፡ የፋቅናት ፡ የራመምናት ፡ የዳመጽናት ፡ የክርስቶስ ፡ የደብዳቤው ፡ መጻፊያ ፡ እንደኾናችሁ ፡
ሰው ፡ ኹሉ ፡ ያውቃችኋል ፡ (አለ) ፡ እኛ ፡ ያስተማርናችሁ ፡ ያሳመናችሁ ፡ ያጠመቅናችሁ ፡ ያቈረብናችሁ ።
የክርስቶስ ፡ ማደሪያ ፡ እንደኾናችሁ ፡ ሰው ፡ ኹሉ ፡ ያውቃችኋል ።
ወጽሕፍት ፡ ይእቲ ።
ጽሕፈቱን ፡ ተናግሮ ፡ መጻፊያውን ፡ አልተናገረም ፡ ነበርና ፡ መጻፋችሁም ።
ወአኮ ፡ በማየ ፡ ሕመት ።
በጥቁር ፡ ቀለም ፡ እይደለም ።
ዘእንበለ ፡ በመንፈስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያው ።
የሕያው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሕይወት ፡ በሚኾን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቀለምነት ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ወዘኢኮነ ፡ ጽሌ ፡ ዘዕብን ። ( ዘፀአ ፡ ፳፬ ፡ ፲፪ ። )
በደንጊያም ፡ ስሌዳነት ፡ አይደለም ።
ዘእንበለ ፡ ጽሌ ፡ ልብ ፡ ዘሥጋ ።
የሥጋ ፡ ሕይወት ፡ በምትኾን ፡ በነባቢት ፡ ነፍስ ፡ ስሌዳነት ፡ ነው ፡ እንጂ ።
እንድም ፡ የሥጋ ፡ ሕይወት ፡ የምትኾን ፡ የደመ ፡ ነፍሲ ፡ ሕይወት ፡ በምትኾን ፡ በነባቢት ፡ ነፍስ ፡ ስሌዳነት ፡
ነው ፡ እንጂ ።

፬ ፡ ወብነ ፡ ባሕቱ ፡ ከመዝ ፡ ተስፋ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ (ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፮ ።)
በክርስቶስ ፡ ስላመነ ፡ የክርስቶስን ፡ ስም ፡ ስላስተማርን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ተስፋ ፡ አለን ።

፭ ፡ ወኢይደልወነ ፡ ነሐሊ ፡ ለሊነ ፡ ለርእስነ ፡ ወኢምንተኒ ።
ነገር ፡ ግን ፡ ራሳችንን ፡ ልናመሰግን ፡ አይገባንም ።

፮ ፡ እስመ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይልነ ። (ም ፡ ፮ ፡ ፲፮ ።)
ኃይላችን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነውና ፡ አለ ። ኃይላችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ነውና ፡ (እንድም ፡)
ወብነ ፡ ባሕቱ ፡ ዘከመዝ ፡ ተስፋ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ።
በክርስቶስ ፡ ስም ፡ ስላመነ ፡ የክርስቶስን ፡ ስም ፡ ስላስተማርን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ተስፋ ፡ አለን ።
ወኢይደልወነ ፡ ነሐሊ ፡ ለሊነ ፡ ለርእስነ ፡ ወኢምንተኒ ።
እንኪያስ ፡ ምን ፡ ምን ፡ ለራሳችን ፡ ልናስብ ፡ አይገባንም ።
እስመ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይልነ ፡ (ም ፡ ፮ ፡ ፲፮ ።)
እውቀታችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነውና ፡ (አለ ) ፡ አውቆ ፡ ያደርግልናልና ። ወበከመ ፡ ብርሃን
ሰኀበ ፡ ጸሐፊ ፡ ከማሁ ፡ ልብነኒ ፡ እመንገለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲል ፡ (ማሪ ፡ ይስ) ።

፯ ፡ ዘረሰየነ ፡ ላእካነ ፡ ለሐዲስ ፡ ሕግ ።
ለሐዲስ ፡ ሕግ ፡ ለወንጌል ፡ አገልጋዮች ፡ ያደረገን ።
አኮ ፡ በሕገ ፡ መጽሐፍ ።
አገልጋዮችም ፡ ያደረገን ፡ በሕገ ፡ ሥጋ ፡ በኦሪት ፡ በንባብ ፤ አይደለም ።
አላ ፡ በሕገ ፡ መንፈስ ፡ (ሮሜ ፡ ፯ ፡ ፮ ።)
በሕገ ፡ ነፍስ ፤ በወንጌል ፤ በትርጓሜ ፤ ነው ፡ እንጂ ።
እስመ ፡ መጽሐፍ ፡ ይቀትል ።
ሕገ ፡ ሥጋ ፤ ኦሪት ፡ ንባብ ፤ ይጐዳልና ፡ አኮ ፡ በሕገ ፡ መጽሐፍ ።
ወመንፈስ ፡ ያሐዩ ፡ (ዮሐ ፡ ፯ ፡ ፷፫ ።)
ሕገ ፡ ነፍስ ፤ ወንጌል ፡ ትርጓሜ ፤ ይጠቅማልና ፡ አላ ፡ በሕገ ፡ መንፈስ ።

፯ ፡ ወሶበ ፡ ለእንታክቲ ፡ መልእክተ ፡ ሞት ፡ እንተ ፡ ተጽሕፈት ፡ ባእብን ፡ ተገብረ ፡ ላቲ ፡ ስብሐት ።
በደንጊያ ፡ ስሌዳነት ፡ ለተጻፈች ፡ ለዚያች ፡ ለሕግ ፡ ኦሪት ፡ ክብር ፡ ከተደረገላት ።
እስከ ፡ ኢይክሉ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ነጽሮተ ፡ ገጹ ፡ ለሙሴ ፡ በእንተ ፡ ስብሐተ ፡ ገጹ ፡ ኃላፊ ፡ (ዘፀአ ፡
፴፬ ፡ ፴ ።)
በፊቱ ፡ ኃላፊ ፡ ብርሃን ፡ ስለተሣለበት ፡ የሙሴን ፡ ፊት ፡ ማየት ፡ የማይቻላቸው ፡ እስኪኾን ፡ ድረስ ፡
ክብር ፡ ከተደረገላት ፡ (ተገልበበ ፡ ለነ ፡ ሙሴ ፡ ተገልበበ ፡ ለነ ፡ ብለውታልና ) ።

www.ethiopianorthodox.org

፰ ፡ እፎ ፡ እንከ ፡ ይትገበር ፡ ፈድፋደ ፡ ስብሐት ፡ ለመልእክተ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ (ገላት ፡ ፫ ፡ ፪ ፡ ፭ ።)
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላጸፋት ፡ ሕግ ፡ ለወንጌልማ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ክብር ፡ ይደረግላት ፡ ይኾን ።

፱ ፡ ሶበ ፡ ለመልእክት ፡ እንተ ፡ ታኬንን ፡ ወታሕስብ ፡ ተገብረ ፡ ላቲ ፡ ስብሐት ፡ ብዙኅ ።
ሞትን ፡ ለምታስፈርድ ፤ ኃጢአትን ፡ ቈጥራ ፡ ቈጥራ ፡ ለምትናገር ፡ ለዚያች ፡ ለሕገ ፡ ኦሪት ፡ ብዙ ፡ ክብር ፡ ከተደረገላት ።

ሚመጠን ፡ ፈድፋደ ፡ መልእክተ ፡ ጽድቅ ፡ ትሴባሕ ፡ ወትከብር ፡ (ሮሜ ፡ ፩ ፡ ፲፯ ፡ ፫ ፡ ፳፩ ።)
ሕይወት ፡ የሚገኝባት ፡ ሕገ ፡ ጽድቅ ፡ ወንጌልማ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ትክብር ፡ ይኾን ።

፲ ፡ እስከ ፡ ትከውን ፡ እንተ ፡ ተሰብሓት ፡ ከመ ፡ ዘኢተሰብሐት ፡ ሶበ ፡ ያስተዔርይዋ ፡ በዝንቱ ፡ ስብሐት ፡ ዓቢይ ።
በዚህ ፡ ፍጹም ፡ ክብር ፡ ባነጻጸሯት ፡ ጊዜ ፡ ክብራ ፡ የነበረች ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፡ እንዳልከበረች ፡ እስከት ኾን ፡ ድረስ ።

፲፩ ፡ ሶበ ፡ ኃላፊ ፡ ዘይሠዓር ፡ ረከበ ፡ ስብሐተ ።
ኃላፊው ፡ ሕገ ፡ ኦሪት ፡ ክብር ፡ ካገኘ ።

እፎ ፡ ፈድፋደ ፡ ዘይነብር ፡ ይረክብ ፡ ቀዋሚ ፡ ስብሐተ ።
(ዘይነብር ፡ ቀዋሚ) ፡ ባለማለፍ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖረው ፡ ሕገ ፡ ወንጌልማ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ክብር ፡ ያገኝ ፡ ይኾን ፡ እንድም ፡ (ኃላፊ) ፡ ይላል ፡ ኃላፊውን ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ የያዘ ፡ ክብር ፡ ካገኘ ። (ቀዋሚ) ፡ ባለ ማለፍ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ሕገ ፡ ወንጌልንማ ፡ የያዘ ፡ ምን ፡ ያህል ፡ ክብርን ፡ ያገኝ ፡ ይኾን ፡ (ሐተታ)፡ ምነው ፡ በኦሪቱ ፡ በሙሴ ፡ ግንባር ፡ ብርሃን ፡ ተሥሎበታል ። በወንጌል ፡ በፊቱ ፡ ብርሃን ፡ የተሣለበት ፡ የለም ፤ ስለምን ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ በወንጌልም ፡ የበቁት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሳሉ ፡ ብርሃን ፡ ያያሉ ፡ በባሕረ ፡ ብርሃን ፡ ይዋኛሉ ፡ ያልበቁትም ፡ በሞት ፡ ጊዜ ፡ ረቂቅ ፡ የብርሃን ፡ ጦር ፡ ረቂቅ ፡ የብርሃን ፡ ጋሻ ፡ ሰዶላቸው ፡ ድል ፡ ነሥተው ፡ ይገባሉና ፡ (ማሪ ፡ ይስ) ።

፲፪ ፡ ወእንዘ ፡ ብነ ፡ መጠነዝ ፡ ተስፋ ።
ይህን ፡ ያህል ፡ ተስፋ ፡ ካለን ።

ርቱዕ ፡ ንቅረብ ፡ በገጽ ፡ ገሃደ ።
ገጸ ፡ ልቡናችንን ፡ ገልጸን ፡ ልንቀርብ ፡ ይገባናል ።

፲፫ ፡ ወአኮ ፡ ከመ ፡ ሙሴ ፡ ዘይገለብብ ፡ ገጾ ፡ ከመ ፡ ኢይርአይዎ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ። ( ዘፀአ ፡ ፴፬ ፡ ፴፫ ፡ ፴፭)
(አኮ ፡ ከመ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል) ፡ ገጸ ፡ ልቡናችንንም ፡ ገልጸን ፡ መቅረባችን ፡ ሙሴ ፡ ፊቱን ፡ እንዳያ ዩት ፡ እንደሚሸፈንባቸው ፡ እንደ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ አይደለም ።

፲፬ ፡ ወባሕቱ ፡ ተጸለለ ፡ ልቦሙ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ።
እስራኤልማ ፡ እንጂ ፡ የሙሴን ፡ ፊት ፡ ማየት ፡ የማይቻለው ፡ እስቲኾን ፡ ድረስ ፡ ልቡናቸው ፡ ደነቆረ፤ ተገልበብ ፡ ስን ፡ ብለውታልና ።
(አንድም ፡ መልስ) ።

ወእንዘ ፡ ብነ ፡ መጠነዝ ፡ ተስፋ ።
ይህን ፡ ያህል ፡ ተስፋ ፡ ሲኖረን ፡ ከተገኘን ።

ርቱዕ ፡ ንቅረብ ፡ በገጽ ፡ ገሃደ ።
ፊት ፡ ለፊት ፡ በባለሟልነት ፡ ልንቀርብ ፡ ይገባል ።

ወእኮ ፡ ከመ ፡ ሙሴ ፡ ዘይገለብብ ፡ ገጾ ፡ ከመ ፡ ኢይርአይዎ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ።
ፊት ፡ ለፊት ፡ በባለሟልነት ፡ መቅረባችንም ፡ እስራኤል ፡ እንዳያዩት ። ፊቱን ፡ ይሸፍንባቸው ፡ እንደነበረ ፡ እንደሙሴ ፡ አይደለም ። (ሐተታ) ፡ ሙሴ ፡ ኹለቱን ፡ ፫ቱን ፡ መጋረጃ ፡ ገብቶ ፡ ከዚያ ፡ አያልፍም ፡ ነበረ ፡ እኛ ፡ ግን ፡ ውሳጤ ፡ መንጦላዕት ፡ የምንገባ ፡ ኾነናልና ፡ ሙሴ ፡ በስቍረተ ፡ አብን ፡ በሥጥቀተ ፡ ዕፅ ፡ ያይ ፡ ነበር ፡ እኛ ፡ ግን ፡ በኩነት ፡ ነውና ።

ወባሕቱ ፡ ተጸለለ ፡ ልቦሙ ፡ እስከ ፡ ይእዜ ።
እስራኤል ፡ የሙሴን ፡ ፊት ፡ ማየት ፡ የማይቻላቸው ፡ እስቲኾን ፡ ድረስ ፡ ልቡናቸው ፡ ደንቍሯልና ፡ ዘይገለብብ ፡ ገጾ ፡ ከመ ፡ ኢይርአይዎ ፡ ደቂቀ ፡ እስራኤል ፡ ላለው ።

እስመ ፡ ውእቱ ፡ ግሉ ፡ ነበረ ፡ ውስተ ፡ ሕግ ፡ ብሉይ ።
በብሉይ ፡ በኦሪት ፡ ድንቁርና ፡ ጸንቶ ፡ ስለነበረ ።

አምጣነ ፡ ተነበ ፡ ወኢተከሥተ ።
ስለተነበበ ፡ ስላልተተረጐመ ። ተነበ ፡ ስላልተተረጐመ ። የተነበበ ፡ ያህል ። ያልተተረጐመ ፡ ያህል።

www.ethiopianorthodox.org

እስከ ፣ እጽርዖ ፣ ክርስቶስ ። (ሮሜ ፣ ፲፩ ፣ ፳፭ ።)
ክርስቶስ ፣ እስኪያሳልፈው ፣ ድረስ ።

፲፭ ፣ ወእስከ ፣ ዮም ፣ ሶበ ፣ ያነቡ ፣ ኦሪተ ፣ ሙሴ ፣ ይገልዎሙ ፣ ልቦሙ ።
ግና ፣ እስከ ፣ ዛሬ ፣ ኦሪትን ፣ በተመለከቱ ፣ ጊዜ ፣ ድንቁርና ፣ ልቡናቸውን ፣ ይሸፍነዋል ።

፲፮ ፣ ወእምከመ ፣ ተመይጡ ፣ ኀበ ፣ እግዚአብሔር ፣ የዐትት ፣ ውእቱ ፣ ግላ ፣ እምኔሆሙ ፣ (ሮሜ ፣ ፲፩ ፣ ፳፫ ፣ ፳፮ ።)
ወደእግዚአብሔር ፣ በተመለሱ ፣ ጊዜ ፣ ግን ፣ ድንቁርና ፣ ይርቅላቸዋል ፤

፲፯ ፣ እስመ ፣ እግዚአብሔር ፣ መንፈስ ፣ ውእቱ ። (ዮሐ ፣ ፬ ፣ ፳፬ ።)
እግዚአብሔር ፣ ዕውቀት ፣ ስለኾነ ።

ወኀበ ፣ ሀሎ ፣ መንፈሰ ፣ እግዚአብሔር ፣ ህየ ፣ ሀሎ ፣ ግእዛን ።
ከእግዚአብሔር ፣ የሚገኝ ፣ እውቀት ፣ ካለ ፣ ዘንድ ። ከድንቁርና ነጻ ፣ መኾን ፣ ከዚያ ፣ አለና ።

፲፰ ፣ ወንሕነሰ ፣ ኵልነ ፣ ከሢተነ ፣ ገጸነ ፣ ንነጽር ፣ ስብሐተ ፣ እግዚአብሔር ፣
እንኪያስ ፣ ገጸ ፣ ልቡናችነን ፣ ገልጠን ፣ እግዚአብሔር ፣ የሚያወርሰንን ፣ ክብር ፣ እንወቅ ።

ከመ ፣ ዘበመጽሔት ።
ፊቱን ፣ በመስታያት ፣ እንደሚያይ ፣ ሰው ።

ወንትመሰል ፣ በአርአያ ፣ ዚአሁ ።
ፊቱን ፣ በመስታወት ፣ የሚያየውን ፣ ሰው ፣ እንምሰለው ።

ከመ ፣ ንባእ ፣ እምክብር ፣ ውስተ ፣ ክብር ።
ያ ፤ አንዱን ፣ አይቶ ፣ አንዱን ፣ እንዲያይ ፤ እኛም ፣ ከዕውቀት ፣ ወደ ፣ ዕውቀት ፣ እንኼድ ፣ ዘንድ ።
በከመ ። ይሁበነ ፣ መንፈሰ ፣ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር ፣ ዕውቀትን ፣ እንደሰጠን ፣ መጠን ፣

ወንሕነሰ ፣ ኵልነ ፣ ከሢተነ ፣ ገጸነ ፣ ንነጽር ፣ ስብሐተ ፣ እግዚአብሔር ።
ፊት ፣ ለፊት ፣ በባለሟልነት ፣ ቀርበን ፣ የእግዚአብሔርን ፣ ክብሩን ፣ ጌትነቱን ፣ እንይ ።

ከመ ፣ ዘበመጽሔት ፣
በስቁረት ፣ እብን ፣ በስጥቀት ፣ ዕፅ ፣ ያይ ፣ እንደነበረ ፣ እንደ ፣ ሙሴ ።

ወንትመሰል ፣ በአር አያ ፣ ዚአሁ ።
ሙሴን ፣ እንምሰለው ።

ከመ ፣ ንባእ ፣ እምክብር ፣ ውስተ ፣ ክብር ።
እሱ ፣ አንዱን ፣ ኹለቱን ፣ መጋረጃ ፣ ገልጦ ፣ ይገባ ፣ እንደነበረ ፣ እኛም ፣ ከክብር ፣ ወደክብር ፣ እንሔድ ፣ ዘንድ ። ይህስ ፣ አኮ ፣ ከመ ፣ ሙሴ ፣ ብሎታል ፣ ብሎ ።

ወንሕነሰ ፣ ኵልነ ፣ ከሢተነ ፣ ገጸነ ፣ ንነጽር ፣ ስብሐተ ፣ እግዚአብሔር ።
በስጥቀት ፣ ዕፅ ፣ በስቁረት ፣ ኰኵሕ ፣ ያይ ፣ እንደነበረ ፣ እንደ ፣ ሙሴ ፣ ያይደለ ፣ ፊት ፣ ለፊት ፣
በባለሟልነት ፣ ቀርበን ፣ የእግዚአብሔርን ፣ ጌትነቱን ፣ ክብሩን ፣ እንይ ።
ወንትመሰል ፣ በአርአያ ፣ ዚአሁ ።
በባሕርይ ፣ የሚተካከለው ፣ በመልክ ፣ የሚመስለው ፣ ክርስቶስን ፣ እንምሰለው ።

ከመ ፣ ንባእ ፣ እምክብር ፣ ውስተ ፣ ክብር ።
እሱ ፣ ወደየማን ፣ አብ ፣ ወደዘባን ፣ ኪሩብ ፣ እንደሔደ ፣ (ውሳጤ ፣ መንጦላዕት) ፣ እንደገባ ፣ እኛም ፣
ከክብር ፣ ወደ ፣ ክብር ፣ እንሔድ ፣ ዘንድ ፣ ውሳጤ ፣ መንጦላዕት ፣ እንገባ ፣ ዘንድ ።

ከመ ፣ ይሁበነ ፣ መንፈሰ ፣ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር ፣ ክብሩን ፣ እንዲሰጠን ፣ መጠን ።

## ምዕራፍ ፣ ፬ ።

፩ ፣ ወበእንተ ፣ ዝንቱ ፣ እስመ ፣ ብነ ፣ ዝንቱ ፣ መልእክት ፣ በከመ ፣ ምሕረቱ ፣ ዘጸገወነ ፣ (ም ፣ ፫ ፣ ፮ ።)
እንደቸርነቱ ፣ የሰጠን ፣ ይህ ፣ ሐዋርያነት ፣ አለንና ፣ ይህ ፣ ስላለን ።

ኢንትሐከይ ።
ምግባር ፣ ትሩፋት ከመሥራት ፣ ቸል ፣ እንበል ።
ወኢንትቈጣዕ ፣ (፩፣ ቆሮ ፣ ፯ ፣ ፳፭ ።)
መከራውን ፣ እንሰልች ፣ እንሰቀቅ ፣ እንመረር ።

www.ethiopianorthodox.org

፯ ፡ አላ ፡ ንኀድጎ ፡ ለምግባረ ፡ ኀፍረት ፡ ዘኅቡዕ ።
ቀስ ፡ ቀስ ፡ ብለው ፡ የሚሠሩትን ፡ የረበናትን ፡ ሥራ ፡ ትተን ፡ ምግባር ፡ ትሩፋትን ፡ እንሥራ ፡ እንጂ ፡ ኢንትሐከይ ። መከራውን ፡ ታግሠን ፡ እንቀበል ፡ እንጂ ፡ ኢንትቈጣዕ ።

ወኢንሖር ፡ በትምይንት ።
በተንኮል ፡ እንዋርም ፡ እንኑር ።

ወኢንትመየኖ ፡ ለቃለ ፡ እግዚአብሔር ፡ (፩ ተሰሎ ፡ ፪ ፡ ፭ ።)
ክርስቶስን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወንጌልን ፡ ዲቃላ ፡ ሕግ ፡ አንበል ።
ወናቅም ፡ ርእሰነ ፡ በጽድቅ ፡ ገሀደ ።
በሃይማኖት ፡ በምግባር ፡ እንጽና ፡ እንጂ ።

እንበይነ ፡ ግእዘ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር ፡ በሚያውቀው ፡ ነገር ፡ ለሰው ፡ ኹሉ ፡ አብነት ፡ ስለመኾን ።
እንድም ፡ ወኢንትመየኖ ፡ ለቃለ ፡ እግዚአብሔር ።
ወንጌልን ፡ መባያ ፡ እናድርግ ።

ወናቅም ፡ ርእሰነ ፡ በጽድቅ ፡ ገሃደ ።
በጸጋ ፡ ዘነሣእክሙ ፡ በጸጋ ፡ ሀቡ ፡ በከንቱ ፡ ዘነሣእክሙ ፡ በከንቱ ፡ ሀቡ ፡ ባለው ፡ ዋጋ ፡ ባለመብላት ፡ እንጽና ፡ እንጂ ።

እንበይነ ፡ ግእዘ ፡ ኵሉ ፡ ሰብእ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ።
ስለቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ ግብር ፡ ፈንታ ።

ወእመኒ ፡ ክዱን ፡ ትምህርትነ ፡ ክዱን ፡ ውእቱ ፡ ለኀርቱማን ፡ ወለንፉቃን ፡ በዝንቱ ፡ ዓለም ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩፡፲፰ ።)
የሌላውን ፡ ንኀድጎ ፡ ለምግባረ ፡ ኃፍረት ፡ ዘኅቡዕ ፡ ትላለህ ፡ እንጂ ፡ አንተስ ፡ የተገለጠ ፡ ታስተምራለኽን ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፤ እኛስ ፡ ትምህርታችን ፡ የተሰወረ ፡ ቢኾን ፡ መሰወሩ ፡ ከመናፍቃን ፡ ነው ።
እንድም ፡ ከመናፍቃን ፡ መሰወሩ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ነው ፡ (በጽርዕ ፡ ምላሹ) ፡ ወበዓለምሰ ፡ ዘይመጽእ ፡ ሀለዎሙ ፡ ያእምርዎ ፡ መናፍቃን ፡ ብሎ ፡ ያነበዋል ።

እለ ፡ ጸለሎሙ ፡ ልቦሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ዘለዓለም ።
ቢያውቁት ፡ ክብር ፡ የማይጨመርለት ፡ ባያውቁት ፡ ክብር ፡ የማይጐልበት ፡ እግዚአብሔር ፡ ዕውቀቱን ፡ ነሥቷቸዋልና ።

ከመ ፡ ኢይርአዩ ፡ ብርሃነ ፡ ትምህርተ ፡ ስብሐተ ፡ ክርስቶስ ።
የክርስቶስ ፡ ጌትነቱን ፡ የምትናገር ፡ ወንጌልን ፡ የሚያውቁበትን ፡ ዕውቀት ፡ እንዳያውቁ ፡ ዕውቀቱን ፡ ነሥቷቸዋልና ።

ዘውእቱ ፡ አርአያሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ (ዕብ ፡ ፩ ፡ ፫ ።)
ይኸውም ፡ እግዚአብሔርን ፡ በመልክ ፡ የሚመስለው ፡ በባሕርይ ፡ የሚተካከለው ፡ ነው ።

፭ ፡ ወአኮ ፡ በርእስነ ፡ ዘንሰብክ ። (ም ፡ ፩ ፡ ፳፬ ።)
ለራሳችን ፡ ማኅበር ፡ ልናበዛ ፡ ቤተ ፡ ሰብእ ፡ ልናስፋ ፡ የምናስተምር ፡ አይደለም ።

ዘእንበለ ፡ ለእግዚአብሔር ።
ለእግዚአብሔር ፡ ማኅበር ፡ ልናበዛ ፡ ቤተ ፡ ሰብእ ፡ ልናስፋ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አንድም ፡ (ወአኮ ፡ በርእስነ ፡ ዘንሰብክ) ፡ ለራሳችን ፡ እኅበላበት ፡ እንጠጣበት ፡ ብለን ፡ የምናስተምር ፡ አይደለም ።

ዘእ ንበለ ፡ ለእግዚአብሔር ።
እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ነው ፡ እንጂ ።

በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሥር ፡ አብነት ፡ ስለኾነን ።

ወለክሙሰ ፡ አቅነይነ ፡ ርእሰነ ።
ለናንተስ ፡ እኛ ፡ ተገዝተናል ።

በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አብነት ፡ ስለኾነን ።

፮ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘይቤ ፡ ይሥርቅ ፡ ብርሃን ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ውእቱ ፡ አብርሀ ፡ ውስተ ፡ ልብነ ፡ ብርሃነ ፡ እእምሮ ፡ ስብሓቲሁ ፡ በገጹ ፡ ለኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ። (ዘፍጥ ፡ ፩ ፡ ፫ ፡ ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፱)
ይሥርቅ ፡ ብርሃን ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በክርስቶስ ፡ ግብር ፡ ጌትነቱን ፡ የምና

www.ethiopianorthodox.org

ውቅበትን ፡ ዕውቀት ፡ በልቡናችን ፡ ሥሎብናልና ። አንድም ፡ ጌትነቱን ፡ የምናስመሰግንበትን ፡ ሥራ ፡ የምንሠራበትን ፡ ዕውቀት ፡ በልቡናችን ፡ ሥሎብናልና ። አሪት ፡ ለይኩን ፡ ብርሃን ፡ ያለውን ። ኢሳይያስ ፡ ዘገብሮ ፡ ለብርሃን ፡ ምስለ ፡ ጽልመት ፡ ብሎታል ።

ኢሳይያስ ፡ ዘገብሮ ፡ ለብርሃን ፡ ምስለ ፡ ጽልመት ፡ ያለውንም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘይቤ ፡ ይሥርቅ ፡ ብርሃን ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ብሎ ፡ አነበበው ።

## ክፍል ፡ ፫ ።

፯ ፡ ወብነ ፡ ዝንቱ ፡ መዝገብ ፡ ውስተ ፡ ንዋየ ፡ ልሕኵት ። (ም ፡ ፩ ፡ ፭ ።)
እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘይቤ ፡ ይሥርቅ ፡ ብርሃን ፡ ውስተ ፡ ጽልመት ፡ ውእቱ ፡ አብርሃ ፡ ውስተ ፡ ልብነ ፡ ብርሃነ ፡ አእምሮ ፡ ስብሐቲሁ ፡ በገጹ ፡ ለክርስቶስ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ውእቱ ፡ አብርሀ ፡ ያለውን ፡ ይተረጕማል ፡ አብርሀ ፡ ውስተ ፡ ልብነ ፡ ያልከው ፡ እንደምነው ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ ከ፲ቱ ፡ ባሕርያት ፡ በተፈጠረ ፡ በዚህ ፡ በሥጋችን ፡ ነፍስ ፡ አለችን ።

ከመ ፡ ይኩን ፡ ዕበየ ፡ ኃይል ፡ ዘእምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወአኮ ፡ ዘእምኀቤነ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፭ ።)
ከኛ ፡ ዘንድ ፡ ያይደለ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የሚገኝ ፡ ፍጹም ፡ ዕውቀት ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ።
(አንድም ። )

ወብነ ፡ ዝንቱ ፡ መዝገብ ፡ ውስተ ፡ ንዋየ ፡ ልሕኵት ።
ኢንትሐከይ ፡ ወኢንትቈጣዕ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ በዚህ ፡ በሰውነታችን ፡ ልጅነት ፡ አለን ።

ከመ ፡ ይኩን ፡ ዕበየ ፡ ኃይል ፡ ዘእምኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡
ከኛ ፡ ዘንድ ፡ ያይደለ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የሚኾን ፡ ብዙ ፡ ተአምራት ፡ ይደረግልን ፡ ዘንድ ።
(አንድም)

ወብነ ፡ ዝንቱ ፡ መዝገብ ፡ ውስተ ፡ ንዋየ ፡ ልሕኵት ።
ከመ ፡ ንባእ ፡ አምክብር ፡ ውስተ ፡ ክብር ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ፈራሽ ፡ በስባሽ ፡ በሚኾን ፡ በሥጋችን ፡ ትንሣኤ ፡ አለን ።

ከመ ፡ ይኩን ፡ ዕበየ ፡ ኃይል ፡ ዘእምእግዚአብሔር ።
ከኛ ፡ ዘንድ ፡ ያይደለ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የሚገኝ ፡ ፍጹም ፡ ክብር ፡ ይሰጠን ፡ ዘንድ ።

፰ ፡ እንዘ ፡ በኵሉ ፡ ንሐምም ፡ ኢንትመነደብ ። (ም ፡ ፩ ፡ ፰ – ፱ ፡ ፭ ።)
ስለዚህም ፡ በውስጥ ፡ በአፍአ ፡ መከራ ፡ ስንቀበል ፡ አንጨነቅም ።

ንትሜነን ።
እንናቃለን ።

ወኢነኀሥር ።
እንዋረድም ።

፱ ፡ ንስደድ ።
አገር ፡ እስኪለው ፡ ይበዱናል ።

ወኢንትገደፍ ።
አንጣልም ።

ንጼዐርኒ ።
ጭንቅ ፡ ጭንቅ ፡ መከራ ፡ ያመጡብናል ።

ወኢንትኀጐል ። (መዝ ፡ ፴፯ ፡ ፳፬ ፡ ፴፫ ።)
አንጠፋም ።

፲ ፡ ወዘልፈ ፡ ንጸውር ፡ ሞቶ ፡ ለክርስቶስ ፡ በሥጋነ ።
ክርስቶስ ፡ የተቀበለውን ፡ መከራ ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ በሥጋችን ፡ እንቀበላለን ።

ከመ ፡ ይትዐወቅ ፡ ሕይወቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ በላዕለ ፡ ዝንቱ ፡ ነፍስትነ ፡ መዋቲ ፡ (ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፲፯)
ፈራሽ ፡ በስባሽ ፡ በሚኾን ፡ በዚህ ፡ በሥጋችን ፡ ላይ ፡ የክርስቶስ ፡ ሕይወቱ ፡ ሕይወትነቱ ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ።

፲፩ ፡ እስመ ፡ ንሕነ ፡ ዘነሐዩ ፡ ወትረ ፡ ንትሜጠው ፡ ለሞት ፡ በእንተ ፡ ኢየሱስ ፡ ከመ ፡ ሕይወቱኒ ፡ ለኢየሱስ ፡ ይትዐወቅ ፡ በላዕለ ፡ ነፍስትነ ፡ መዋቲ ።
(ነሐዩ ፡ ወትረ ፡ ንትሜጠ ፡ ወትረ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፤) ። የኢየሱስ ፡ ሕይወቱ ፡ ሕይወትነቱ ፡ በፈራሽ ፡

www.ethiopianorthodox.org

በበስበሽ ፡ ሰውነታችን ፡ ይገለጥ ፡ ዘንድ ፡ ኋላ ፡ ሞተን ፡ ተነሥተን ፡ ልዘለዓለሙ ፡ ሕያው ፡ ኾነን ፡ የምንኖር እኛ ፡ ዛሬ ፡ ኹልጊዜ ፡ ስለ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለሞት ፡ እንሰጣለን ፤ እስመ ፡ በእንቲአሁ ፡ ይቀትሉነ ፡ ኵሎ ፡ ዕሚረ ፡(መዝ ፡ ፵፫ ፡ ፳፪) ፡ ዳንኤል ፡ ሞት ፡ ብዙኅ ፡ ጊዜያት ፡ በአንተ ፡ አምላኩ ፡ አን ዲል ፡ (እፌ ፡ ወርቅ) ።

፲፪ ፡ ወይእዜሰ ፡ ጸንዐ ፡ በላዕሌነ ፡ ሞት ።
ዛሬ ፡ መከራ ፡ ጸንቶብናል ።
አንዘ ፡ ሕይወት ፡ ኀቤነ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፱ ።)
ኋላ ፡ ሕይወት ፡ ሳለን ።
እንድም ፡ ለሌላው ፡ ሕይወት ፡ መኾን ፡ ሳለን ፡ በኛ ፡ መከራ ፡ ጸንቶብናል ።

፲፫ ፡ ወብነ ፡ አሐዱ ፡ መንፈስ ፡ ዘሃይማኖት ።
ሃይማኖትን ፡ የምንናገርበት ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ አለን ።
እንድም ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ አለን ፤ ይኸውም ፡ ሃይማኖትን ፡ የምንናገርበት ፡ ነው ።
በከመ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፍ ፡ አመንኩ ፡ በዘነበብኩ ። ( መዝ ፡ ፻፲፭ ፡ ፲ )
በተናገርሁት ፡ አመንሁ ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደተናገረ ፡ ብነ ፡ ፩ ፡ መንፈስ ፡ ዘሃይማኖት ፡ ካለው ፡ ወንሕነኒ ፡ ማገናኘ ።
ወንሕነኒ ፡ አመነ ፡ በዘነበብነ ።
ያፌ ፡ ሌላ ፡ የልቤ ፡ ሌላ ፡ ሳይኾን ፡ በተናገርሁት ፡ አመንሁ ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደተናገረ ።
(ወንሕነኒ ፡ አመነ ፡ በዘነበብነ ፡)
እኛም ፡ ያፋችን ፡ ሌላ ፡ የልባችን ፡ ሌላ ፡ ሳይኾን ፡ በተናገርነው ፡ እናምናለን ፡ (ሐተታ) ፡ በአፍ ፡ አምኖ ፡ በልብ ፡ ቢክዱ ፡ አንደ ፡ አርዮስ ፡ (በልብ ፡ አምኖ ፡ በአፍ ፡ ቢክዱ ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥ ሮስ ፡ መኾን ፡ ነውና) ።

፲፬ ፡ ወነእምር ፡ ከመ ፡ ዘአንሥኦ ፡ ለኢየሱስ ፡ እግዚእነ ፡ ያነሥአነ ፡ ከያነሂ ፡ ምስሌሁ ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፫ ፡ ፲፭)
ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ከሙታን ፡ ለይቶ ፡ ያስነሣው ፡ እግዚአብሔር ፡ እኛንም ፡ ከሱ ፡ ጋራ ተዋሕዶ ፡ ለመኖር ፡ እንደሱ ፡ እንዲያስነሣን ፡ እናውቃለን ።
ወያቀውመነ ፡ ምስሌክሙ ፡ ኀቤሁ ።
አስነሥቶ ፡ ከናንት ፡ ጋራ ፡ ከሱ ፡ ዘንድ ፡ በባለሟልነት ፡ ያኖረናል ፡ እንዲያኖረን ፡ እናውቃለን ።

፲፭ ፡ እስመ ፡ ኵሉ ፡ በእንቲአክሙ ።
ኹሉ ፡ ስለናንት ፡ ነውና ፡ ምስሌክሙ ።
ከመ ፡ ትፈድፍድ ፡ ጸጋሁ ፡ በላዕለ ፡ ብዙኃን ።
ጸጋው ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ በዝታ ፡ ትሰጥ ፡ ዘንድ ።
ወይብዛኅ ፡ አኰቴቱ ፡ ለስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ( ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፲፰ ። )
የእግዚአሔርም ፡ ጌትነቱ ፡ በዝቶ ፡ ይመስገን ፡ ዘንድ ፡ (ያቀውመነ) ፡ ምስሌክሙ -) እንድም ፡ ጸጋ ውን ፡ በዝታችሁ ፡ ታገኙ ፡ ዘንድ ፤ ክብሩን ፡ ለመውረስ ፡ በዝታችሁ ፡ በሱ ፡ ቃል ፡ ትመስገኑ ፡ ዘንድ ፡ ኵሉ ፡ በእንቲአክሙ ።

፲፮ ፡ ወበእንተዝ ፡ ኢንትቈጣዕ ።
ስለዚህ ፡ መከራን ፡ አንሰለች ፤ አንሰቀቅ ፤ አንመረር ።
ወኢንትሐከይ ።
ምግባር ፡ ትሩፋት ፡ ከመሥራት ፡ ቸል ፡ አንበል ።
እስመ ፡ ዘእንተ ፡ እፍእነ ፡ ብእሲ ፡ በላዪ ፡ ( ፩ ፡ ጴጥ ፡ ፬ ፡ ፩ ። )
እፍእዊ ፡ ሰውነታችን ፡ ኃላፊ ፡ ነውና ።
ወዘእንተ ፡ ውስጥነሰ ፡ ይትሔደስ ፡ ኵሎ ፡ አሚረ ። (ኤፌ ፡ ፫ ፡ ፲፮)
ውሳጣዊ ፡ ሰውነታችን ፡ ግን ፡ ኹልጊዜ ፡ በተሐድሶ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራልና ።

፲፯ ፡ እስመ ፡ ሕማምነ ፡ ዘለሰዓት ፡ ቀሊል ፡ ክብረ ፡ ወስብሐተ ፡ አፈድፋዶ ፡ ይገብር ፡ ለነ ። (ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፲፰)
ለጥቂት ፡ ሰዓት ፡ የሚኾን ፡ መከራችን ፡ ክብርን ፤ የክብር ፡ ክብርን ፡ አብዝቶ ፡ የሚያመጣልን ፡ ፅለኾነ ፡ ይትሔደስ ።

፲፰ ፡ እስመ ፡ ኢንሴፎ ፡ ዘያስተርኢ ፤ አላ ፡ ዘኢያስተርኢ ። ( ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፳፬ ፡ ፳፭)
የማይታየውን ፡ ነው ፡ እንጂ ፤ የሚታየውን ፡ ዓለም ፡ ተስፋ ፡ አናደርገውምና ፡ ይትሔደስ ።

www.ethiopianorthodox.org

እስመ ፡ ዘያስተርኢ ፡ ዓለም ፡ ኃላፊ ፡ ውእቱ ።
የሚታየው ፡ ዓለም ፡ ኃላፊ ፡ ስለኾነ ፡ (ኢንቤፎ ፡ ዘያስተርኢ ።)
ወዘሰ ፡ ኢያስተርኢ ፡ ቀዋሚ ፡ እስከ ፡ ለዓለም ፡ ውእቱ ።
የሚታየው ፡ ዓለም ፡ ግን ፡ ባለማለፍ ፡ ጸንቶ ፡ የሚኖር ፡ ስለኾነ ፡ (እላ ፡ ዘኢያስተርኢ) ።

## ምዕራፍ ፭

፩ ፡ ወነአምር ፡ ከመ ፡ ለእመሂ ፡ ተነሥተ ፡ ቤተ ፡ ማኀደርነ ፡ ዘበምድር ፡ ( ኢዮ ፡ ፬ ፡ ፲፱ ፡ ፪ ፡ ጴጥ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ።)
የነፍሳችን ፡ ማደሪያ ፡ የሚኾን ፡ ሥጋችን ፡ ቢፈርስ ፡ ቢበሰብስ ፡ ዘውእቱ ፡ ሥጋ ።
ቤት ፡ ያለውን ፡ ተረጐመ ፡ ይኸውም ፡ ሥጋ ፡ ነው ፡ ወሰመየ ፡ ሥጋቲነ ፡ አብያተ ፡ ዘጽቡር ፡ እስመ ፡
ነፍሳቲነ ፡ ኅዱራት ፡ ውስቴቱ ፡ እንዲል ። (ኢዮ) ፡ ብነ ፡ ሕንጸ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰማያት ፡ ዘኢ
ገብሮ ፡ እደ ፡ ሰብእ ፡ (ዮሐ ፡ ፲፬ ፡ ፪ ።)
በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በልዕልና ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ያልፈጠረው ፡ ሌላ ፡ ሥጋ ፡ እንዳለን ፡(እለ) ፡
ሐዲስ ፡ ሥጋ ፡ እንዳለን ፡ እናውቃለን ፡ (ሐተታ) ፡ ምነው ፡ ይህን ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ፈጥሮታልና ፡ እንዲህ ፡
አለ ፡ ቢሉ ፡ ይህ ፡ በምክንያተ ፡ ዘርዕ ፡ ተገኝቷል ፡ የኋላው ፡ ግን ፡ ምክንያት ፡ የለውምና ።

፪ ፡ ወኪያሁ ፡ ንሴፎ ፡ ንልበስ ፡ ቤተነ ፡ ዘውስተ ፡ ሰማያት ። ( ሮሜ ፡ ፲፫ ፡ ፲፪ ፡ )
ኪያሁ ፡ ቤተነ ፡ በልዕልና ፡ ያለ ፡ ያንን ፡ ሥጋ ፡ እንድንዋሐድ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ፡ (እለ) ፡ በነፍስ ፡
መደብ ፡ ቆሞ ።

ዘበእንቲአሁ ፡ ንሰርሕ ።
ዛሬ ፡ መከራ ፡ የምንቀበልለት ፤ በመከራው ፡ የምንደክምበት ።

፫ ፡ ወእምከመ ፡ ለበስናሁ ፡ ኢኮነ ፡ ዘንትረከብ ፡ ዕራቃቲነ ።
ከተወሐድነውም ፡ በኋላ ፡ ከክብር ፡ ባዶችነን ፡ አንገኝም ።

፬ ፡ እስመ ፡ እንዘሂ ፡ ሀለውነ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ቤት ፡ ነኀዝን ፡ ፈድፋደ ፡ እምክበደ ፡ ዘአሁ። (፩ ፡ ቆሮ፡ ፲፭፡፶፫)
በዚህ ፡ በሥጋችን ፡ ሳለን ፡ ጠቆረ ፡ እናቅላው ፤ ከሳ ፡ እናወፍረው ፡ በማለት ፡ እናዝናለን ፡ እኮ ።
እንድም ፡ ከመከራው ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ መቸ ፡ በተለየነው ፡ እያልን ፡ እናዝናለን ፡ እኮ ።

ወኢንፈቅድ ፡ ንስለብ ።
ኪያሁ ፡ ቤተነ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ያንን ፡ ሥጋ ፡ ግን ፡ ከተዋሐድነው ፡ በኋላ ፡ ልንለየው ፡ አንሻም ።

ዘእንበለ ፡ ከመ ፡ ንልበስ ፡ ካልአ ፡ መልዕልቱሁ ።
በተዋሕዶው ፡ ጸንተን ፡ ልንኖር ፡ እንወዳለን ፡ እንጂ ። (አንድም ፡ መልስ) ፡

ወነአምር ፡ ከመ ፡ ለእመሂ ፡ ተነሥተ ፡ ቤተ ፡ ማኀደርነ ፡ ዘበምድር ።
የነፍሳችን ፡ ማደሪያ ፡ የሥጋችን ፡ መኖሪያ ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ቢያልፍ ፡

ዘውእቱ ፡ ሥጋ ።
ማኅደር ፡ ያለውን ፡ ተረጐመው ፡ ይኸውም ፡ ሥጋ ፡ ነው ።

ብነ ፡ ሕንጸ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰማያት ፡ ዘኢገብሮ ፡ እደ ፡ ሰብእ ።
በልዕልና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ያልፈጠረው ፡ ሌላ ፡ ዓለም ፡ እንዳለን ፡ እናውቃለን ፡
(ሐተታ) ፡ ምነው ፡ ይህን ፡ የሰው ፡ እጅ ፡ ፈጥሮታልና ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡ ቢሉ ፡ ይህ ፡ በዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡
እጅ ፡ ይናኛል ፤ ያ ፡ ግን ፡ በዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ እጅ ፡ አይናኝምና ።

ወኪያሁ ፡ ንሴፎ ፤ ንልበስ ፡ ቤተነ ፡ ዘውስተ ፡ ሰማያት ። ኪያሁ ፡ ቤተነ ፡ በልዕልና ፡
ያለ ፡ ያንን ፡ ዓለም ፡ እንድንወርስ ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ።

ዘበእንቲአሁ ፡ ንሠርሕ ።
ዛሬ ፡ መከራ ፡ የምንቀበልለት ፡ (በመከራው ፡ የምንደክምለት ።)

ወእምከመ ፡ ለበስናሁ ፡ ኢኮነ ፡ ዘንትረከብ ፡ ዕራቃቲነ ።
ያን ፡ ዓለም ፡ ከወረስነው ፡ በኋላ ፡ ከክብር ፡ ባዶዎችነን ፡ አንገኝም ።

እስመ ፡ እንዘሂ ፡ ሀለውነ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ቤት ፡ ነኀዝን ፡ ፈድፋደ ፡ እምክበደ ፡ ዚአሁ ።
በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሳለን ፡ ሳላ ፡ እናጽናው ፡ ጠበበ ፡ እናስፋው ፡ በማለት ፡ እናዝናለን ፡ እኮ ፡ አንድም ፡
ከመከራው ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ፡ መቸ ፡ በተለየነው ፡ እያልን ፡ እናዝናለን ፡ እኮን ።

ወኢንፈቅድ ፡ ንስለብ ።
ዘበእንቲአሁ ፡ ንሠርሕ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ያንን ፡ ዓለም ፡ ግን ፡ ከወረስነው ፡ በኋላ ፡ ለዚህ ፡ ብለን ፡
መከራ ፡ ተቀበልን ፡ አንልም ።

www.ethiopianorthodox.org

ዘእንበለ ፡ ከመ ፡ ንልበስ ፡ ካልአ ፡ መልዕልቴሁ ።

ምነው ፡ በመከራ ፡ ላይ ፡ መከራን ፡ በጨመርንበት ፡ እንላለን ፡ እንጂ ፡ (ሐተታ) ፡ ገበሬ ፡ ሲያርስ ፡ ክርሞ አምኾውን ፡ ሲያሀድ ፡ . ብለን ፡ መከራ ፡ ተቀበልን ፡ አንልም ፤ ምነው ፡ በመከራ ፡ ላይ ፡ መከራ ፡ በጨመርንበት ፡ እንላለን ፡ እንጂ ።

ከመ ፡ ይሰጠም ፡ መዋቲ ፡ በሕይወት ።

ይህ ፡ መዋቲ ፡ ሰውነታችን ፡ በሕይወት ፡ ባሕር ፡ ይሰጠም ፡ ዘንድ ።

፭ ፡ ወውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረድአነ ፡ በዝንቱ ።

በዚህም ፡ የሚረዳን ፡ እሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ እሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይረዳናል ።

ዘወሀበነ ፡ አረቦነ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ውስተ ፡ ልብነ ፡ (ም፡ ፩ ፡ ፳፪ ፡ ሮሜ፡ ፰ ፡ ፲፮ ፡ ፳፫ ፡ ኤፌ ፡ ፩፡ ፲፫ ፡ ፲፬)

የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ፈለማ ፡ በልቡናችን ፡ ያሳደረብን ።

፮ ፡ ተአመኑ ፡ እንከ ።

እንዲህም ፡ ከኾነ ፡ ጽኑ ።

ወእጥብዑ ፡ በኵሉ ፡ ጊዜ ፡ ( ዕብ ፡ ፲፩ ፡ ፲፫ ። )

ኹልጊዜ ፡ መከራውን ፡ ለመቀበል ፡ ጨክኑ ።

ወተአምሩ ፡ እንከ ፡ ከመ ፡ እንግዳ ፡ እንትሙ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ሥጋ ፡

በዚህ ፡ በሥጋችሁ ፡ አድሮ ፡ ሒያጅ ፡ እንደኾናችሁ ፡ ታውቃላችሁና ።

ወትነግዱ ፡ እምነፍስትክሙ ፡ ወተሐውሩ ፡ ኀበ ፡ እግዚእነ ።

ከዚህ ፡ ከሥጋችሁ ፡ ተለይታችሁ ፡ ወደጌታችን ፡ ትሔዳላችሁና ።

፯ ፡ እስመ ፡ በአሚን ፡ ነሐውር ።

በውነት ፡ እንሔዳለንና ።

ወአኮ ፡ በአድልዎ ፡ ( ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፫ ፡ ፲፪ ። )

ለሞት ፡ ወሬኛ ፡ የለውምና ፡ በሐሰት ፡ ያይደለ ፡ ባዎንታ ፡ እንሄዳለንና ።

፰ ፡ ወፈድፋደ ፡ ንትአመን ፡ ወንትፌሣሕ ።

ይልቁንም ፡ እምነን ፡ ደስ ፡ ይለናል ፤ ደስ ፡ ይበለን ።

እስ መ ፡ ወፂአነ ፡ እምነፍስትነ ፡ ነሐውር ፡ ኀቤሁ ( ፊልጵ ፡ ፩ ፡ ፳፫ ። )

ከሥጋችን ፡ ተለይተን ፡ ወደርሱ ፡ እንሔዳለንና ።

ወናሠምሮ ፡ ለእግዚእነ ።

ጸንተን ፡ ብንገኝ ፡ ጌታችንን ፡ ደስ ፡ እናሰኘዋለንና ።

፱ ፡ ወይእዜኒ ፡ ናእኵቶ ፡ እመኒ ፡ ነገድነ ፡ ወእመኒ ፡ ሀሎነ ።

እንዲህም ፡ ከኾነ ፡ ብንሔድም ፡ ብንኖርም ፡ እናመስግነው ፤ ሎቱ ፡ ዳዕሙ ፡ ማንሻ ።

ሎቱ ፡ ዳዕሙ ፡ ናድሉ ፡ በምግባሪነ ፡ ( መዝ ፡ ፴፱ ፡ ፲፫ ። )

ብንሔድም ፡ እናመስግነው ፡ ብንኖርም ፡ በሥራችን ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ ደስ ፡ እናሰኘው ። አንድም ፡ ብን ሔድም ፡ ብንኖርም ፡ በሥራችን ፡ እሱን ፡ ብቻ ፡ ደስ ፡ እናሰኘው ።

፲ ፡ እስመ ፡ ሀለወነ ፡ ኵልነ ፡ ንቁም ፡ ቅድመ ፡ መንበረ ፡ ምኵናኑ ፡ ለክርስቶስ ፡ ( ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፯ ፡ ፴፩ ። ) (ሮሜ ፡ ፪ ፡ ፮ ፡ ፲፬ ፡ ፲ ።)

ኹላችንም ፡ ክርስቶስ ፡ በሚፈርድበት ፡ ዐደባባይ ፡ እንቆም ፡ ዘንድ ፡ አለንና ።

ከመ ፡ ንትፈደይ ፡ በከመ ፡ ገበርነ ፡ በሥጋነ ።

በሥጋችን ፡ እንደሠራነው ፡ እንደሠራነው ፡ ዋጋችነን ፡ እንቀበል ፡ ዘንድ ።

እመኒ ፡ ሠናየ ፡ ወእመኒ ፡ እኩየ ።

በጎም ፡ ቢኾን ፡ ክፉም ፡ ቢኾን ፡ (አለ) ፡ በጎ ፡ ብንሠራ ፡ ዋጋችነን ፡ ክፉ ፡ ብንሠራ ፡ ፍዳችነን ፡ እንቀበል ዘንድ ።

## ክ ፍ ል ፡ ፬ ።

፲፩ ፡ ወእንበይነ ፡ ዘነአምር ፡ ጽድቀ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወፈሪሆቶ ፡ ( ኢዮ ፡ ፴፩ ፡ ፳፫ ። )

(ጽድቀ ፡ እግዚአብሔር ) ፡ ምስትነቱን ፡ (ፈሪሆቶ) ፡ እንድነቱን ፤ ጽድቀ ፡ (እግዚአብሔር ፡) ለብከተ ፡ ሐዋርያትን ። (ፈሪሆቶ ፡) ትንቢተ ፡ ነቢያትን ፡ ስላወቅነ ።

www.ethiopianorthodox.org

ኅእምን ፡ ሰብአ ።
ሰው ፡ መኾኑን ፡ አምነን ፤ ሎቱ ፡ ዳዕሙ ፡ ናድሉ ፡ በምግባሪኒ ፡ ላለው ፡ እንድም ፡ ሰው ፡ መኾንን ፡ እምነን ፡ (ጽድቀ ፡ እግዚአብሔር ፤) ዘአምነ ፡ ወዘተጠምቀ ፡ ይድኅን ፡ ያሉውን ፡ (ወፈሪሆቶ ፡) ዘኢአምነ፡ ወዘኢተጠምቀ ፡ ይደየን ፡ ያለውን ። እንድም ፡ ጽድቀ ፡ እግዚአብሔር ፤ ለጻድቁ ፡ ፈርዶ ፡ የሚሰጠውን ፡ ዋጋ ፡ (ወፈሪሆቶ ።) በኃጥኡ ፡ ፈርዶ ፡ የሚያመጣውን ፡ ፍዳ ፡ ስላወቅነ ፡ ሎቱ ፡ ዳዕሙ ፡ በምግባሪኒ ፡ ላለው ። ለእግዚአብሔር ፡ ንሕነ ፡ ክሡታን ፡ ሎቱ ፡ ማንሻ ።

ለእግዚአብሔርሰ ፡ ንሕነ ፡ ክሡታን ፡ ሎቱ ።
ወአኮ ፡ ለርእስነ ፡ ዘንሰብክ ፡ ዘእንበለ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ (ጽድቀ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጸጋ ፡ ዘነሣእክሙ ፡ በጸጋ ፡ ሀቡ ፡ በከንቱ ፡ ዘነሣእክሙ ፡ በከንቱ ፡ ሀቡ ፡ ያለውን ፡(ማቴ፡ ፲ ፡ ፱፡) (ወፈሪሆቶ ፡ ገብር ፡ ሐካይ ፡ ለምንት ፡ ኢያገባዕከ ፡ ወርቅየ ፡ ውስተ ፡ ማዕድየ ፡ ለዝንቱ ፡ ገብር እስሩ ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ፡ ያለውን፡ (ማቴ ፡ ፳፭ ፡ ፳፮-፴፡) ስላወቅነ ፡ ናእምን ፡ ሰብአ) ፡ ዙረን ፡ ዙረን ሰውን ፡ ሁሉ ፡ ስናስተምር ።

(ለእግዚአብሔርሰ ፡ ንሕነ ፡ ክሡታን ፡ ሎቱ ።)
በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ዋጋ ፡ ባለመቀበል ፡ የታወቅን ፡ ነን ።

ወንትአመን ፡ ከመሂ ፡ ንትከሠት ፡ በልብክሙ ።
በናንተም ፡ በልቡናችሁ ፡ ታውቀን ፡ እንዳለ ፡ እናምናለን ።

፲፪ ፡ ወአኮ ፡ ዘንዌድስ ፡ ካዕበ ፡ ርእሰነ ፡ በዝንቱ ፡ በኀቤክሙ ፡ (ም ፡ ፫ ፡ ፩ ።)
ነገር ፡ ግን ፡ በናንት ፡ ዘንድ ፡ ራሳችንን ፡ በዚህ ፡ የምናመሰግን ፡ አይደለም ፡

ወዳዕሙ ፡ ንሁበክሙ ፡ ምክንያተ ፡ ትጽንዑ ፡ በዘትትሜክሑ ፡ ብነ ፡ አንትሙኒ ፡ ከማነ ።
እናንተም ፡ እንደኛ ፡ በምትመኩ ፡ ገንዘብ ፡ ትጸኑ ፡ ዘንድ ፡ የምትመኩበትን ፡ ምክንያት ፡ እንነግራ ችኋለን ፡ እንጂ ።

ከመ ፡ ይኩንክሙ ፡ ለኀበ ፡ አለ ይትሜክሑ ፡ ለገጽ ፡ ወአኮ ፡ ለልብ ።
ለልቡና ፡ ያይደለ ፡ ለሰው ፡ ይምሰል ፡ በሚመኩ ፡ በቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ ፊት ፡ መመኪያ ፡ ሊኾናችሁ።

፲፫ ፡ እስመ ፡ ንሕነሰ ፡ ለእመኒ ፡ ኮነ ፡ አብዳነ ፡ አበድነ ፡ ለእግዚአብሔር ።
ስንፍናህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ አስተምረህ ፡ ዋጋ ፡ አትብላ ፡ ያለህን ፡ አለ ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆነ ፡ እኛስ ፡ ስነ ፎችም ፡ ብንኾን ፡ ስንፍናችን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማገልገል ፡ ነው ።

ወእመኒ ፡ ኮነ ፡ ጠቢባነ ፡ ጠበብነ ፡ ለክሙ ።
ይኸውም ፡ እንጂ ፡ ልባምነትህ ፡ ትሉኝ ፡ እንደሆነ ፡ ልባሞችም ፡ ብንኾን ፡ ልባምነታችን ፡ ለናንት፡ ብለን ፡ ነው ።
እንድም ፡ (እመኒ ፡ አበድነ ፡ አበድነ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወእመኒ ፡ ጠበብነ ፡ ለክሙ ፡ ይላል፡)
ብንሰንፍ ም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብለን ፡ ሰንፈናል ፡ ብንለብምም ፡ ለእናንት ፡ ብለን ፡ ለብመናል ።

፲፬ ፡ እስመ ፡ ፍቅረ ፡ ክርስቶስ ፡ ያጌብረነ ፡ ናጥብዕ ፡ ውስተ ፡ ዝንቱ ፡ ሐሊና ።
ክርስቶስን ፡ መውደድ ፡ በዚህ ፡ በመመካቱ ፡ እንድንጸና ፡ ያደርገናልና ፡ ወዳዕሙ ፡ ንሁበክሙ ፡ ምክንያተ ፡ ላለው ።
እንድም ፡ ክርስቶስን ፡ መውደድ ፡ ዋጋ ፡ ባለማብላት ፡ እንድንጸና ፡ ያደርገናልና ፡ እመኒ ፡ አበድነ ፡ አበድነ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ላለው ።

እስመ ፡ አሐዱ ፡ ሞተ ፡ ቤዛ ፡ ኵሉ ፡ (ዕብ ፡ ፪ ፡ ፱ ።)
እንዱ ፡ እሱ ፡ ለኹሉ ፡ ቤዛ ፡ ኾኖ ፡ ስለሞተ ።

በዘወድአ ፡ ሞተ ፡ ኵሉ ።
ሰው ፡ ኹሉ ፡ ሞትን ፡ በፈጸመ ፡ ገንዘብ ፡ (አለ) ፡ ፈጽሞ ፡ በሞተ ፡ ገንዘብ ፡ በነፍስ ፡ በሥጋ ፡ ሲል ፡ ነው ።
እንድም ፡ ሞተ ፡ ኵሉ ፡ የኹሉን ፡ ሞት ፡ በሞተ ፡ ገንዘብ ፡ ተፈልጦው ፡ አንድ ፡ ነውና ፡ አማኑኤል ፡ ሞተ ፡ ከመ ፡ ሞተ ፡ ዚአነ ፡ ዘውእቱ ፡ ተፈልጦተ ፡ ነፍስ ፡ እምሥጋ ፡ እንዲል ፡ (ሳዊሮ) ።
እንድም ፡ ሞት ፡ ኵሎ ፡ ሞት ፡ ሁሉን ፡ በፈጸመ ፡ ገንዘብ ።
እንድም ፡ ሞተ ፡ ኵሉ ፡ ለኹሉ ፡ የሚገባውን ፡ ሞት ፡ በሞተ ፡ ገንዘብ ፡ ሞተሰ ፡ እምደልዎ ፡ ለአዳም ፡ ስቁለ ፡ በመስቀል ፡ ዘበኃሣር ፡ እንዲል ፡ መቅ ፡ ወን ።
እንድም ፡ የኹሉን ፡ ሞት ፡ ድል ፡ በነሣበት ፡ በመስ ቀል ፡ አንዱ ፡ እሱ ፡ ለኹሉ ፡ ቤዛ ፡ ሙቷልና ያጌብረነ ፡ ናጥብዕ ።

፲፭ ፡ ውእቱ ፡ ሞተ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፪ ፡ ፮ ።)
ውእቱ ፡ ሞተ ፡ ቤዛ ፡ ኵሉና ፡ ሞተ ፡ በእንተ ፡ ኵሉ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ እንድም ፡ በየራሱ ፡ ስማውጣት፡ አንድ ፡ እሱ ፡ የኹሉ ፡ ቤዛ ፡ የሚኾን ፡ ሞትን ፡ ስለኹሉ ፡ በሞተ ፡ ገንዘብ ፡ በል ።

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ፡ እለሂ ፡ የሐይዉ ፡ አኮ ፡ ለርእሶሙ ፡ ዘየሐይዉ ፡ (ሮሜ ፡ ፲፬ ፡ ፯ ፡ ፰ ።)
ትንሣኤ ፡ ልቡና ፡ የሚነው ፡ ራሳቸውን ፡ ለማገልገል ፡ እንዳይደለ ፡ መጠን ።

ዘእንበለ ፡ ለዝኩ ፡ ዘበእንቲአሆሙ ፡ ሞተሂ ፡ ወሐይወሂ ።
ስለሳቸው ፡ ሞቶ ፡ የተነሣ ፡ ክርስቶስን ፡ ለማገልገል ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፲፮ ፡ ወይእዜሰ ፡ አልቦ ፡ ዘነአምር ፡ በሥጋ ።
ዛሬስ ፡ በግዘፍ ፡ የምናውቀው ፡ የለም ።

ወእመኒ ፡ አእመርናሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ በሥጋ ።
ክርስቶስንም ፡ ከዚህ ፡ አስቀድሞ ፡ በግዘፍ ፡ ብናውቀው ።

እምይእዜሰ ፡ አልቦ ፡ ዘነአምሮ ፡ እንከ ።
ከትንሣኤ ፡ በኋላ ፡ በግዘፍ ፡ የምናውቀው ፡ አይደለም ።

፲፯ ፡ ወይእዜሰ ፡ በክርስቶስ ፡ ተሐደሰ ፡ ኵሉ ፡ ዘኮነ ። (ሮሜ ፡ ፰ ፡ ፩-፲ ።)
ዛሬስ ፡ የሆነው ፡ ሁሉ ፡ በክርስቶስ ፡ ታድሷል ።

ወኀለፈ ፡ ዘትካት ። (ኢሳ ፡ ፵፫ ፡ ፲፱ ። ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፳፩ ፡ ፭ ።)
ብሉይ ፡ ግብር ፡ አልፏል ።

፲፰ ፡ ወናሁ ፡ ኮነ ፡ ኵሉ ፡ ሐዲሰ ፡ እምኀበ ፡ እግዚአብሔር ። (ሮሜ ፡ ፭ ፡ ፲ ።)
እነሆ ፡ ኹሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የታደሰ ፡ ኾኗል ።

ዘአቅረበነ ፡ ኀቤሁ ፡ በክርስቶስ ።
በክርስቶስ ፡ ወደሱ ፡ ባቀረበን ፡ በእግዚአብሔር ።

ወወሀበነ ፡ መልእክተ ፡ ሥምረቱ ።
ፈቃዱን ፡ የምንፈጽምበት ፡ ልጅነትን ፡ በሰጠን ።

፲፱ ፡ እስመ ፡ ተዋሰጠ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓለመ ፡ በክርስቶስ ።
እግዚአብሔር ፡ ዓለሙን ፡ በክርስቶስ ፡ ዋጅቶታልና ፡ ዘአቅረበነ ፡ ኀቤሁ ፡ በክርስቶስ ።

እናሕሰዮ ፡ ኃጢአቶሙ ። (ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፳፬ ፡ ፳፭ ። )
ኃጢአታቸውን ፡ ንቆ ፡ አቃለ ።

ወኢነጺሮ ።
ዕዳ ፡ አልልም ፡ ብሎ ።

ወረሰየ ፡ ላዕሌነ ፡ ቃለ ፡ ሥምረቱ ።
ወዶ ፡ የሠራት ፡ ወንጌልን ፡ እንድናስተምር ፡ አድርጎናልና ፡ ዘአቅረበነ ።

ወወሀበነ ፡ መልእክተ ፡ ሣህሉ ። (ቈላ ፡ ፩ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።)
ይቅርታውን ፡ የምናገኝበት ፡ ሐዋርያነትን ፡ ሰጥቶናልና ። የላይኛውን ፡ ሐዋርያነት ፡ ያሉ ፡ እንደ
ኾነ ፡ ይህን ፡ ልጅነት ፡ የላይኛውን ፡ ልጅነት ፡ ያሉ ፡ እንደሆነ ፡ ይህን ፡ ሐዋርያነት ።

፳ ፡ ወንሕነሰ ፡ ንተነብል ፡ በእምሳለ ፡ ክርስቶስ ። (ኢሳ ፡ ፶፪ ፡ ፯ ።)
እንግዲህስ ፡ ክርስቶስን ፡ መስለን ፡ በክርስቶስ ፡ አምሳል ፡ እንጸልያለን ፡ እናስተምራለን ።

ወይሁበክሙ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍሥሐ ፡ በላዕሌነ ።
በኛ ፡ ጸሎት ፡ በኛ ፡ ትምህርት ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅነትን ፡ ሕይወትን ፡ ይሰጣችኋል ።

ወንስእለክሙ ፡ በክርስቶስ ፡ ከመ ፡ ታሥምርዎ ፡ በእግዚአብሔር ።
ንስእለክሙ ፡ በክርስቶስ ፡ ታሥምርዎ ፡ በክርስቶስ ፡ ብለህ ፡ ግጠም ፡ በክርስቶስ ፡ አሥምሮት ፡ እግዚአ
ብሔርን ፡ ታሠምሩት ፡ ዘንድ ፡ ክርስቶስን ፡ ማላጅ ፡ አድርገን ፡ እንማልዳችኋለን ።

፳፩ ፡ እስመ ፡ ዘኢየአምር ፡ ኀጢአተ ፡ ረሰየ ፡ ርእሶ ፡ ኃጥአ ። (፩ ጴጥ ፡ ፪ ፳፪ ፡ ዕብ ፡ ፬ ፡ ፳ ፡ ገላትያ ፡ ፫ ፡ ፲፫ ።)
ኃጢአት ፡ የሌለበት ፡ እሱ ፡ ስለኛ ፡ ራሱን ፡ ኃጥእ ፡ አሰኝቷልና ።

ከመ ፡ ኪያነ ፡ ያጽድቀነ ፡ ለእግዚአብሔር ። (፩ ቆሮ ፡ ፩ ፴ ፡ ፊልጵ ፡ ፫ ፱ ።)
የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ለመኾን ፡ እኛን ፡ ጻድቃን ፡ ያሰኘን ፡ ዘንድ ።
(ያከብረን) ፡ ዘንድ ።

## ምዕራፍ ፮ ።

፩ ፡ ወናስተበቍዖሂ ፡ ኀቤክሙ ። (ም ፡ ፩ ፳፬ ። ፭ ፡ ፳ ።)
እናንተን ፡ እንማልዳችኋለን ፡ ለናንት ፡ እንማልዳለን ።

www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

ወገረድእኒ ።
    እናዝንላችኋለን ።
ተወከፉ ፡ ለነ ።
    ትምህርታችነን ፡ ተቀበሉን ፡ ብለን ፡ ናስተ በቍዕ ።
ወኢትረስዩ ፡ ለከንቱ ፡ ለጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንተ ፡ ንግእክሙ ።
    የተቀበላችኋትን ፡ ልጅነት ፡ መከራ ፡ ላለመቀበል ፡ እታድርጓት ፤ አታድርጓት ፡ ብለን ፡ ንረድእኒ ፡
  ላለው ።

፪ ፡ እስመ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ በዕለት ፡ ኀሪት ፡ እሰምዐከ ።
  በተመረጠች ፡ ቀን ፡ እሰማሃለሁ ፡ ብሏልና ፡ ናስተበቍዐኒ ።
ወበዕለተ ፡ መድኀኒት ፡ እረድአከ ። (ኢሳ ፡ ፵፱ ፡ ፰ ።)
    ድኅነት ፡ በሚደረግባትም ፡ ቀን ፡ እዝንልሃለሁ ፡ ብሏልና ፡ ንረድእኒ ።
ወናሁ ፡ ይእዜ ፡ ዕለት ፡ ኀሪት ።
እነሆ ፡ ዕለት ፡ ኀሪት ፡ ዛሬ ፡ ናት ።
ወናሁ ፡ ዮም ፡ ዕለተ ፡ አድኅኖት ። (ሉቃ ፡ ፬ ፡ ፲፱ ፡ ፳ ።)
    ዕለተ ፡ አድኅኖትም ፡ ዛሬ ፡ ናት ፡ (ሐተታ) ፡ በአሪቱ ፡ ዕለት ፡ ኀሪት ፡ በግዐ ፡ ፋሥ ሑን ፡ የበሉባት
  ቀን ፡ ናት ፡ ዕለተ ፡ አድኅኖተ ፡ ከግብጽ ፡ የወጡባት፡ቀን፡ናት፤እንድም፡ዕለት፡ኀሪት፡ ዕለተ፡ኤዋዌ፡ናት ፡
ኀሪት ፡ እሳት ፡ ሚጠቱን ፡ ሰምተው ፡ የወረዱ ፡ አሉና ፡ ወዘይበዝኀ ፡ ሕዝበ ፡ አውረድከ ፡ በትፍሥሕት ፡
  እንዲል ፡ (ኢሳ) ፡ ዕለተ ፡ አድኅኖት ፡ ዕለተ ፡ ሚጠት ፡ አንድም ፡ በሐዲሱ ፡ (ዕለት ፡ ኀሪት) ፡ ዕለተ ፡
  ፅንስ፡ ዕለተ፡አድኅኖት) ፡ ዕለተ ፡ ልደት፡እንድም፡ (ዕለት፡ኀሪት)፡ዕለተ ፡ ዓርብ፡(ዕለተ፡አድኅኖት) ፡ ዕለተ
  ትንሣኤ ፡ አንድም ፡ ዕለት ፡ ኀሪት ፡ ዘመነ ፡ [illegible] ፡ ዕለተ ፡ አድኅኖት) ፡ [illegible] ፡ መዋዕለ ፡ ንስሐ ።

፫ ፡ ዑቁ ፡ እንከ ፡ ወኢተሀቡ ፡ ለመኑሂ ፡ ዕቅፍተ ።
    ለማንም ፡ ለማን ፡ ዕንቅፋት ፡ እንዳታኖሩ ፡ ዕወቁ ፡ (እስ) ፡ ማንንም ፡ ማንን ፡ እንዳታሳዝኑ ፡ ዕወቁ ።
ከመ ፡ ኢታልስሑ ፡ መልእክተከሙ ።
    ሕጋችሁ ፡ ወንጌልን ፡ እንዳታስጠሉ ።
ወኢታንውርዋ ።
    እንዳታስነቅፏት ፡ ዕወቁ ።

፬ ፡ ወበኵሉ ፡ አርትዑ ፡ ርእሰክሙ ፡ (ም ፡ ፮ ፡ ፪ ።)
    በውስጥ ፡ በአፍአ ፡ ርእስ ፡ ልቡናችሁን ፡ የቀና ፡ አድርጉ ።
ወኩኑ ፡ ላእካነ ፡ ለእግዚአብሔር ።
    ለእግዚአብሔር ፡ አገልጋዮች ፡ ኹኑ ።
በብዙኅ ፡ ትዕግሥት ።
    ፍጹም ፡ ትኅግሥት ፡ ኹናችሁ ።
በኵሉ ፡ ሕማም ፡
    በፍጹም ፡ መከራ ፡ ኹናችሁ ።
ወጻዕር ።
    ጭንቅ ፡ ጭንቅ ፡ በሚኾን ፡ መከራ ።
ወበምንዳቤ ፡ በጸዋትወ ፡ መከራ ።

፭ ፡ ወበተቀሥፎ ፡ በመገረፍ ።
ወበተሞቅሖ ፡ በመታሰር ።
ወበሥራኅ ፡ በሰገድ ፡ በቀዊም ።
ወበተሀውኮ ፡ በሁከት ፡ መንፈሳዊ ።
በትጋሁ ። በትጋሀ ፡ ሌሊት ።

፮ ፡ ወበንጽሕ ፡ በንጽሕና ፡ ኹናችሁ ።
ወበጾም በጾም ።
ወበአእምሮ ፡ በምክር ።
    በዕውቀት ፡ ኹናችሁ ፡ በፈሊጥ ፡
ወበተፀግዎ ፡ በምሕር ፡ (፩ ፡ ጢሞ ፡ ፫ ፡ ፲፪ ።)
    በመታገሥ ፡ ኹናችሁ ፡ ለሰው ፡ በማዘን ፡ በመራራት ።

www.ethiopianorthodox.org

፮ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በፍቅር ።
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ልጆች ፡ ኾናችሁ ፡ በፍቅር ።
ዘእንበለ ፡ አድልዎ ፡ በነገረ ፡ ጽድቅ ።
ያለሐሰት ፡ በውነት ፡ (ያለጥርጥር ።)
በኀይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፪ ፡ ፬ ።)
(ኵኑ ፡ ሳዕካን ፡ በኀይለ ፡ እግዚአብሔር ) ፡ በእግዚአብሔር ፡ አጋዥነት ፡
ኵኑ ፡ ሳእካን ።
ወወልታ ፡ ጽድቅ ፡ ዘእምየማን ፡ ወዘእምፀጋም ።
ግራ ፡ ቀኝ ፡ እሳባሽ ፡ ጋሻ ፡ ያዙ ፡ ኹለቱም ፡ እርእስት ፡ ነው ፡ ለኹለቱም ፡ ያመጣል ።
፰ ፡ በክብር ።
ቢያከብሩዋችሁ ፡ ደስ ፡ ሳይላችሁ ፡ የማን ፡ ሳለው ።
ወበኀሣር ።
ቢያዋርዱዋችሁ ፡ ሳይከፋችሁ ፡ ፀጋም ፡ ሳለው ።
በምድኅር ።
ቢመርቋችሁ ፡ ደስ ፡ ሳይላችሁ ፡ የማን ፡ ሳለው ።
ወበመርገም ።
ቢረግሙዋችሁ ፡ ሳይከፋችሁ ፡ ፀጋም ፡ ሳለው ።
ከመ ፡ ኃጥኣን ።
እንደኃጥአን ፡ ቢያደርጓችሁ ፡ ሳይከፋችሁ ።
ወጻድቃን ።
እንደጻድቃን ፡ ቢያደርጓችሁ ፡ ደስ ፡ ሳይላችሁ ።
፱ ፡ ከመ ፡ እለ ፡ ኢየአምርዎሙ ።
እንደማያውቋቸው ፡ ቢያደርጓችሁ ፡ ሳይከፋችሁ ።
ወዕውቃን ።
እንደሚያውቋቸው ፡ ቢያደርጓችሁ ፡ ደስ ፡ ሳይላችሁ ።
ከመ ፡ አብዳን ።
እንዳላዋቆች ፡ ቢያደርጓችሁ ፡ ሳይከፋችሁ ።
ወጠቢባን ።
እንዳዋቆች ፡ ቢያደርጓችሁ ፡ ደስ ፡ ሳይላችሁ ።
ከመ ፡ ምውታን ።
እንደምውታን ፡ ቢያደርጓችሁ ።
ወንሕነኒ ፡ ሕያዋን ።
እኛስ ፡ ሕያው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አድሮብናልና ፡ ሕያዋን ፡ ነን ፡
ብላችሁ ፡ ሳይከፋችሁ ፡ ኵኑ ፡ ሳእካን ።
ከመ ፡ ምንስዋን ።
ድል ፡ እንደተነሡ ፡ ቢያደርጓችሁ ፡ ሳይከፋችሁ ።
ወኢቅቱላን ፡ (ም ፡ ፬ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ። መዝ ፡ ፪ ፡ ፲፰ ፡ ፲፯ ።)
ድል ፡ እንደነሡ ፡ ቢያደርጓችሁ ፡ ደስ ፡ ሳይላችሁ ።
ከመ ፡ ትኩዛን ።
እንዳዘናችሁ ፡ ቢያደርጓችሁ ።
ወዘልፈ ፡ ንትፌሣሕ ።
እኛስ ፡ ቅብዓ ፡ ትፍሥሕት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አድሮብናልና ፡ ኹልጊዜ ፡ ደስ ፡ ይለናል ፡ ብላችሁ ፡
ሳይከፋችሁ ፡ ኵኑ ፡ ሳዕካን ።
ከመ ፡ ነዳያን ።
እንደ ፡ ነዳያን ፡ ቢያደርጓችሁ ፡ ሳይከፋችሁ ።
፲ ፡ ወለብዙኃን ፡ ታብዕሉ ።
ብዙ ፡ ሰዎችንም ፡ እንደምታከብሩ ፡ ቢያደርጓችሁ ፡ ደስ ፡ ሳይላችሁ ፡ አንድም ፡ እንደ ፡ ነዳያን ፡ ቢያደ
ርጓችሁ ፡ ወለብዙኃን ፡ ናብዕል ፡ ይላል ፡ እኛስ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ እናከብራለን ፡ ብላችሁ ፡ ሳይከፋችሁ ፡
ኵኑ ።

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ፡ ዘአልብከሙ ፡ ምንትኒ ።
ምንም ፡ ምን ፡ እንደሌላችሁ ፡ ቢያደርጓችሁ ፡ ሳይከፋችሁ ።

ወኵሉ ፡ ውስተ ፡ እዴክሙ ።
ኹሉ ፡ በእጃችሁ ፡ ፡ እንደተያዘ ፡ ቢያደርጓችሁ ፡ (አንድም ፡ ) ምንም ፡ ምን ፡ እንደሌላችሁ ፡ ቢያደ
ርጓችሁ ፡ ወኵሉ ፡ ውስተ ፡ እዴን ፡ ይላል ፡ ውፋይ ፡ ያለበት ፡ ነው፡ እኛስ ፡ ኹሉ፡ በእጃችን፡ የተያዘ ፡
ነው ፡ ብላችሁ ፡ ሳይከፋችሁ ፡ ኩኑ ፡ ላእካነ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሳለው ።

፲፩ ፡ አፉነ ፡ ክሡት ፡ ለከሙ ፡ አ ሰብአ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ወርሒብ ፡ ልብነ ።
ከዚህም ፡ ቢጽ ፡ ሐሰውያን ፡ ገብተው ፡ ጳውሎስ ፡ ከሀብታችሁን ፡ የማይቀበላችሁ ፡ ባይወዳችሁ ፡
እንጂ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ነገሯቸው ፡ አዝነዋል ፡ ለዚህ ፡ ያመጣል ።
እናንተ ፡ የቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ የወደዱትን ፡ ምግብ ፡ አፍን ፡ ከፍቶ ፡ ሆድን ፡ አስፍቶ ፡ እንዲመገቡት፡
እኛም ፡ አፋችንን ፡ መልተን ፡ ልባችንን ፡ አስፍተን ፡ እንወዳችኋለን ።

፲፪ ፡ ወአልብነ ፡ ንሂከ ፡ እምኔከሙ ።
ከናንተም ፡ መጥቶ ፡ በኛ ፡ ላይ ፡ የሰፈረ ፡ ኃዘን ፡ የለም ።

ወኢላዕሌከሙ ፡ እምኔነ ።
ከኛም ፡ ሔዶ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ የሰፈረ ፡ ኃዘን ፡ የለም ።

አላ ፡ ንህከሙ ፡ ወተመነደብከሙ ፡ ለምሕረትከሙ ።
ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ይቅርታን ፡ ለማግኘት ፡ መከራ ፡ ተቀብላችሁ ፡ አዝናችኋል ፡ እንጂ ።

፲፫ ፡ አብለከሙ ፡ ከመ ፡ ዘለደቂቅየ ።
ልጆቼ ፡ እንደመሆናችሁ ፡ ለልጆቼ ፡ እንድነግር ፡ እነግራችኋለሁ ።

በእንተ ፡ ውእቱ ፡ ፍድዩ ፡ ዘይደሉ ፡ ሊተ ፡ ላዕሌከሙ ፡ አርኀቡ ፡ ሊተ ፡ አፍቅሮተከሙ ፡ እንትሙኒ ።
( ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፲፬ ። )
በላያችሁ ፡ ላይ ፡ ስለሚገባኝ ፡ ብድራት ፡ እናንተም ፡ ፍቅራችሁን ፡ ግለጡልኝ ፡ (አለ) ። አብዝቼ ፡
እንደወደድኋችሁ ፡ እናንተም ፡ አብዝታችሁ ፡ ውደዱኝ ፡ ብዬ ፡ እነግራችኋለሁ ።

፲፬ ፡ ወኢትኩኑ ፡ ንፉቃነ ።
አይወደንም ፡ ብላችሁ ፡ አትጠራጠሩ ። አንድም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሕገ ፡ ሥጋ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ
ሕገ ፡ ነፍስ ፡ አትበሉ ።

ወኢትሑሩ ፡ ውስተ ፡ አርዑት ፡ እለ ፡ ኢየአምኑ ። ( ዘዳግ ፡ ፯ ፡ ፫ ፡ ፬ ። )
ባላመኑ ፡ ሰዎች ፡ ግብር ፡ አትኑሩ ።

መኑ ፡ ዘያስተዓርያ ፡ ለጽድቅ ፡ ምስለ ፡ ኃጢአት ።
ሕገ ፡ ሥጋውንስ ፡ ሕገ ፡ ነፍሱን ፡ አንድ ፡ አድርገን ፡ ብንይዘው ፡ ምንዋ ፡ ትለኝ ፡ እንደሆነ ፡ ጽድቅን፡
ከኃጢአት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የሚያደርጋት ፡ ማነው ? ጽድቅ ፡ ስትሠራ ፡ ኃጢአት ፡ ኃጢአት ፡ ስትሠራ ፡
ጽድቅ ፡ የምትቀር ፡ አይደለምን ።

ወመኑ ፡ ዘይዴምር ፡ ለብርሃን ፡ ምስለ ፡ ጽልመት ። ( ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፲፩ ። )
ብርሃንንስ ፡ ከጭለማ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የሚያደርገው ፡ ማነው ? ብርሃን ፡ ሲመጣ ፡ ጨለማ ፡ ጨለማ ፡
ሲመጣ ፡ ብርሃን ፡ የሚለቅ ፡ አይደለምን ።

፲፭ ፡ ወመኑ ፡ ዘያኀብሮ ፡ ለክርስቶስ ፡ ምስለ ፡ ቤልሆር ።
ክርስቶስን፡ ከሰይጣን ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የሚያደርገው ፡ ማነው ፡ ክርስቶስ ፡ ሲያድር ፡ ሰይጣን ፡ የሚርቅ ፡
ሰይጣን ፡ ሲያድር ፡ ክርስቶስ ፡ የሚለይ ፡ አይደለምን ።

ወመኑ ፡ ዘይከፍሎሙ ፡ ለመሃይምናን ፡ ምስለ ፡ ንፉቃን ።
ምእመናንን ፡ ከመናፍቃን ፡ ጋር ፡ አንድ ፡ አድርጎ ፡ ርስት ፡ የሚያካፍላቸው ፡ ማነው ፡ የምእመናን ፡
ርስት ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ የመናፍቃን ፡ ርስት ፡ ገሃነም ፡ አይደለምን ።

፲፮ ፡ ወመኑ ፡ ዘይዴምር ፡ ታቦተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ።
ታቦተ ፡ እግዚአብሔርንስ ፡ ከቤተ ፡ ጣዖት ፡ አግብቶ ፡ የሚያኖር ፡ ማነው ፡ (ሐተታ) ፡ አንድ ፡
ቀንስ ፡ እንኳ ፡ ታቦተ ፡ ጽዮን ፡ ከቤተ ፡ ጣዖት ፡ ገብታ ፡ ብታድር ፡ ዳጎንን ፡ ጕማምዳ ፡ ጣለችው ።
እንደዚህስ ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ ሰውነቱን ፡ የሰይጣን ፡ ማደሪያ ፡ የሚያደርግ ፡ ማነው ።

እኮኑ ፡ ንሕነ ፡ ውእቱ ፡ ቤቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሕያው ። ( ፩ ፡ ቆሮ ፡ ፫ ፡ ፲፮ ። )
የእግዚአብሔር ፡ ማደሪያ ፡ እኛ ፡ አይደለንምን ።

ዘከመ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ እኔ ፡ አኀድር ፡ ሀቤሆሙ ፡ ወአንሶሱ ፡ ማእከሎሙ ። ( ዘሌዋ ፡ ፳፮ ፡ ፲፪ ። )
እኔ ፡ አድርባቸዋለሁ ፡ በመካከላቸው ፡ እኖራለሁ ፡ (በነፍስ ፡ በሥጋ ፡ ሲል ፤ ይደጋግማል ።)

www.ethiopianorthodox.org

ወእከውኖሙ ፡ አምላኮሙ ።
አባት ፡ እኾናቸዋለሁ ።
ወእሙንቱኒ ፡ ይከውኑኒ ፡ ሕዝብየ ።
እነሱም ፡ ልጆቼ ፡ ይኾኑኛል ፤ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረ ፡ ንሕነ ፡ ውእቱ ፡ ቤቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ላለው ።

፲፯ ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ፃኡ ፡ እማእከሎሙ ፡ ወተፈለጡ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ። (ኢሳ ፡ ፶፩ ፡ ፩፭ ፡ ፶፪ ፡ ፲፩ ። ራእ ፡ ዮሐ ፡ ፲፰ ፡ ፬ ።)
በእንተ ፡ ዝንቱን ፡ በመካከል ፡ እንደ ፡ ሹልዱ ፡ አገብቶታል ፤ ስለዚህም ፡ ከመካከላቸው ፡ ተለዩ ፡ አለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረ ፡ ንሕነ ፡ ውእቱ ፡ ቤቱ ።
ወኢትቅረቡ ፡ ኀበ ፡ ርኩሳን ።
ድል ፡ ከተነሡ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ አትገናኙ ።
ወአነ ፡ እትዌከፈከሙ ።
እንዲህ ፡ የኾነ ፡ እንደኾነ ፡ እኔ ፡ በረድኤት ፡ እቀበላችኋለሁ ።
ወእከውነክሙ ፡ አባከሙ ።
አባት ፡ እኾናችኋለሁ ።
ወአንትሙኒ ፡ ትከውኑኒ ፡ ደቂቅየ ፡ ወአዋልድየ ፡ ይቤ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘኵሎ ፡ ይመልክ ። (ኤር ፡ ፴፩ ፡ ፩ ፡ ፱ ፡ ፴፫ ፡ ፴፪ ።)
ኹሉን ፡ ፈጥሮ ፡ የሚገዛ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሴቶችም ፡ ወንዶችም ፡ ልጆቼ ፡ ትኾናላችሁ ፡ አለ ፡ ብሎ ፡ ነቢይ ፡ እንደተናገረ ፡ ንሕነ ፡ ውእቱ ፡ ቤቱ ።

## ምዕራፍ ፯ ።

### ክፍል ፩ ።

፩ ፡ ወበእንተ ፡ ዘብነ ፡ ዝንቱ ፡ ተስፋ ።
ይህ ፡ ቃል ፡ ስላለን ።
አኀዊነ ፡ ናንጽሕ ፡ ርእሰነ ።
ወንድሞቻችን ፡ ሰውነታችንን ፡ ከኃጢአት ፡ እንለይ ።
ወኢናገምን ፡ ነፍስተነ ።
ሰውነታችንን ፡ በኃጢአት ፡ አናሳድፍ ።
ወንግበር ፡ በዘንትቀደስ ፡ በፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ።
በፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኾነን ፡ በምንከብር ፡ ገንዘብ ፡ የምንከብርበትን ፡ ሥራ ፡ እንሥራ ፡ እንጂ ።

፪ ፡ ወይእዜኒ ፡ ተእምሩ ፡ አኃዊነ ።
ወንድሞቻችን ፡ ይህንን ፡ ታውቃላችሁ ።
አስመ ፡ አልቦ ፡ ዘአበስነ ።
የበደልነው ፡ እንደሌለ ።
ወአልቦ ፡ ዘገፋዕነ ።
የቀማነው ፡ እንደሌለ ።
ወአልቦ ፡ ዘአማሰነ ።
ያጠፋነው ፡ እንደሌለ ።
ወአልቦ ፡ ዘተዐገልነ ። (ም ፡ ፲፪ ፡ ፲፯ ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፳ ፡ ፴፫ ።)
የቀማነው ፡ እንደሌለ ፡ (በምክንያት ፡ እንበለ ፡ ምክንያት ፡ ሲል ፡ ይደጋግማል ።)

፫ ፡ ወአኮ ፡ ለአድልዎ ፡ ዘእብል ።
ይህንም ፡ በሐሰት ፡ ለሰው ፡ አድልዬ ፡ የምናገር ፡ አይደለም ።
እስመ ፡ ወቅድመ ፡ እቤ ፡ ከመ ፡ ምስሌነ ፡ አንትሙ ፡ ውስተ ፡ ልብነ ፡ ለመዊትኒ ፡ ወለሕይወትኒ ። (ም ፡ ፮ ፡ ፲፩ ፡ ፲፫ ።)
ሞታችንን ፡ ሞት ፡ ሕይወታችንን ፡ ሕይወት ፡ ለማድረግ ፡ በልቡናችን ፡ ታውቃላችሁ ፡ እንዳለ ፡ መጠን ፡ ቀድሞ ፡ አድርጌ ፡ እሱን ፡ ከመ ፡ ለከመ ፡ ... ሰብአ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ... ሁኖ ፡ ይህን ፡ ... በሐሰት ፡ ለሰው ፡ ... እንዳላደረገ ፡ ...

www.ethiopianorthodox.org

፬ ፡ ወከመዝ ፡ ብየ ፡ ብዙኅ ፡ ሞገስ ፡ በኀቤክሙ ።
በናንት ፡ ዘንድ ፡ ይህን ፡ ያህል ፡ መወደድ ፡ መታፈር ፡ እንዳለኝ ፡ መጠን ።
ወብዙኅ ፡ ትምክሕትየ ፡ በእንቲአክሙ ።
እናንተን ፡ በማስተማር ፡ የምመካው ፡ ትምክሕት ፡ ብዙ ፡ እንደኾነ ፡ መጠን ።
ወፈጸምኩ ፡ ፍሥሐየ ።
ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ እንዳለኝ ፡ መጠን ።
ወፈድፈደኒ ፡ ሐሤትየኒ ፡ እምዅሉ ፡ ሕማምየ ።
ከመከራዬ ፡ ይልቅ ፡ ደስታዬ ፡ እንደበዛ ፡ መጠን ፡ ቍርጥ ፡ አርጌ ፡ አፉን ፡ ከሠተ ፡ ለከሙ ፡ እ ፡ ሰብአ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ወርኀብ ፡ ልብነ ፡ እሳለሁና ፡ ይህን ፡ የምል ፡ በሐሰት ፡ ለሰው ፡ ይምሰል ፡ እንዳይ ደለ ፡ እወቁ ።

፭ ፡ ወበጺሕነ ፡ መቄዶንያ ፡ ኢረከብነ ፡ ወኢአሐተኒ ፡ ዕረፍተ ፡ ለነፍስነ ።
እምዅሉ ፡ ሕማምየ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ መቄዶንያም ፡ በደረስነ ፡ ጊዜ ፡ (አሐተኒ) ፡ እንድ ፡ ወገንስ ፡ እንኳ ፡ (ሐተኒ) ፡ ጥቂትስ ፡ እንኳ ፡ ለሰውነታችን ፡ ዕረፍት ፡ አላገኘንም ።
ወበኵሉ ፡ አሕመሙነ ።
በውስጥ ፡ በአፍኣ ፡ መከራ ፡ አጸኑብን ፡ እንጂ ።
በአፍአኒ ፡ ቀትል ፡ ወመንሱት ።
በአፍአም ፡ ጠብ ፡ ክርክር ፡ ነበር ።
ወበውስጥኒ ፡ ፍርሃት ።
በውስጥም ፡ ፍርሃት ፡ ነበር ፡ የቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ ትምህርታችንን ፡ ይቀበሉን ፡ አይቀበሉን ፡ በማለት ።

፮ ፡ ወባሕቱ ፡ ውእቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘያስተፌሥሖሙ ፡ ለሕሙማን ፡ አስተፍሥሐነ ፡ በምጽአቱ ፡ ለቲቶ
(ም ፡ ፩ ፡ ፫ ፡ ፬ ። ፪ ፡ ፲፫ ።)
ነገር ፡ ግን ፡ ኀዙናንን ፡ ደስ ፡ ያሰኛቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ በቲቶ ፡ መምጣት ፡ ደስ ፡ አሰኘን ።

፯ ፡ ወአኮ ፡ በምጽአቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዓዲ ፡ በፍሥሓ ፡ ዘአስተፍሥሕክምዎ ።
ደስ ፡ ያሰኘንም ፡ በቲቶ ፡ መምጣት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ደስ ፡ ባሰኛችሁትም ፡ ደስታ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ወዜነወነ ፡ አፍቅሮተክሙ ፡ ዘከመ ፡ ትጽህቁ ፡ ለነ ።
ለኛ ፡ ማሰባችሁን ፡ እኛን ፡ መውደዳችሁን ፡ ስለነገረን ፡ ነው ፡ እንጂ ። ወትትቃነው ።
ለምግባር ፡ ለትሩፋት ፡ እንድትፈካከሩ ፡ ስለነገረን ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ወሰሚዕየ ፡ ዘንተ ፡ ጸንዐ ፡ ፍሥሐየ ፡ ብክሙ ።
ይህንም ፡ በሰማሁ ፡ ጊዜ ፡ ደስታዬ ፡ በናንት ፡ በዛ ።

፰ ፡ ወእመኒ ፡ አተከዝኩክሙ ፡ ቀዳሚ ፡ በመጽሐፍ ፡ ዘጸሐፍኩ ፡ ለክሙ ፡ ኢያኔስሐኒ ፡ (ም ፡ ፪ ፡ ፬ ።)
ቀድሞ ፡ ጽፌ ፡ በሰደድሁት ፡ ክታብ ፡ ባሳዝናችሁም ፡ አላዝንም ።
ወእመኒ ፡ ነሳሕኩ ፡ ናሁ ፡ እሬእያ ፡ ለይእቲ ፡ መልእክት ።
ባዝንም ፡ እነሆ ፡ ይችን ፡ ክታብ ፡ ስትሠራችሁ ፡ ስትቀጣችሁ ፡ አያታለሁና ።
እመሂ ፡ ለአሐቲ ፡ ሰዓት ፡ አተከዝኩክሙ ፡ ናሁ ፡ ይእዜ ፡ እትፌሣሕ ፡ በእንቲአሃ ፡ ብዙኀ ።
ምንም ፡ ለጥቂት ፡ ሰዓት ፡ ባሳዝናችሁ ፡ እነሆ ፡ ዛሬ ፡ በሷ ፡ ፈጽሞ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ። እነ ፡ ዘጳውሎስ ፡ ወእነ ፡ ዘአጵሎስ ፡ ወእነ ፡ ዘኬፋ ፡ ማለትን ፡ እንድትተው ፡ ለአስተዋፅኦ ፡ እንድትተጉ ፡ ለምግባር ፡ ለትሩፋት ፡ እንድትፈካከሩ ፡ ያባቱን ፡ ሚስት ፡ የነሣውን ፡ የመምህሩን ፡ ሹመት ፡ የተሾመውን ፡ እንድትለዩ ፡ ስላደረገቻችሁ ።

፱ ፡ ወአኮሰ ፡ ውእቱ ፡ እስመ ፡ ተከዝክሙ ።
ደስ ፡ ያለኝም ፡ ስላዘናችሁ ፡ አይደለም ።
ዳዕሙ ፡ እስመ ፡ ተከዝክሙ ።
ተከዝክሙና ፡ ተከዝክሙ ፡ እንድ ፡ ወገን ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብላችሁ ፡ ንስሓ ፡ ትገቡ ፡ ዘንድ ፡ የን ስሓ ፡ ኀዘን ፡ አዝናችኋልና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
ከመ ፡ ትነስሑ ፡ እስመ ፡ እንበይነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተከዝክሙ ፡ ከመ ፡ ኢይትሐጐል ፡ አሐዱሂ ፡ እምኔክሙሂ ።
ከናንተ ፡ አንድ ፡ ሰውስ ፡ እንኳ ፡ እንዳይጎዳ ፡ የንስሐ ፡ ኀዘን ፡ አዝናችኋልና ፡ ስለዚህ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ተከዝክሙ ፡ ላለው ።

www.ethiopianorthodox.org

፲ ፡ እስመ ፡ ዘበእንተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃዘን ፡ ንስሓሁ ፡ ለሕይወት ፡ ዘለዓለም ፡ ይከውን ።
ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብሎ ፡ የሚያዝኑት ፡ ኃዘን ፡ ምላሹ ፡ የዘለዓለም ፡ ሕይወት ፡ ነውና ፡ እንበይነ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተከዘከሙ ።

ወትካዝሰ ፡ ዘበእንተ ፡ ዓለም ፡ ሞተ ፡ ያመጽእ ፡ (ማቴ ፡ ፳፯ ፡ ፫ - ፲ )
ስለ ፡ ዓለሙ ፡ ብሎ ፡ የሚያዝኑት ፡ ኃዘን ፡ ግን ፡ ሞትን ፡ ያመጣልና ፡ ከመ ፡ ኢይትኃጎል ፡ አሐዱሂ ፡ እምኔክሙ ፡ (ሐተታ ፡ ) የሚገባ ፡ ኃዘን ፡ የማይገባ ፡ ኃዘን ፡ አለ ። የማይገባ ፡ ኃዘን ፤ እናት ፡ አባት ፡ ሞቱብኝ ፡ እኅት ፡ ወንድም ፡ አጣሁ ፤ የምበላው ፡ የምጠጣው ፡ አጣሁ ፤ ርስቴን ፡ ጉልቴን ፡ ተቀማሁ ፡ ብሎ ፡ ማዘን ፡ አይገባም ፡ እንደናት ፡ እንዳባት ፡ ሥላሴ ፤ እንደ ፡ እኅት ፡ እንደ ፡ ወንድም ፡ መላእክት ፡ እንደ ፡ መብል ፡ መጠጥ ፡ ሥጋው ፡ ደሙ ፤ እንደ ፡ ርስት ፡ እንደ ፡ ጉልት ፡ የማታልፍ ፡ ርስት ፡ ጉልት ፤ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ አለችና ። የሚገባ ፡ ኃዘን ፡ የራስን ፡ ኃጢአት ፡ አስቦ ፡ ማዘን ፡ ይገባል ፡ እንደ ፡ አዳም ፡ እንደ ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ። የወንድምንም ፡ ኃጢአት ፡ አስቦ ፡ ማዘን ፡ ይገባል ፡ እስከ ፡ ማዕዜኑ ፡ ሳሙኤል ፡ ትላህዎ ፡ ለሳኦል ፡ እስመ ፡ አነ ፡ መነንክዎ ፡ ወገደፍክዎ ፡(፩ ፡ ሳሙ ፡ ፲፮፡ ፩፡) ወሶበ ፡ ርእዮ ፡ ለዘያገብእ ፡ ተሐውከ ፡ በመንፈሱ ፡ ወሶበ ፡ ርእያ ፡ ለሀገር ፡ በከየ ፡ ላዕሌሃ ፡ እንዲል ፡ ሉቃ፡(፲፱ ፡ ፵፩ ፡)ግፍዐ ፡ ሰማዕታትንም ፡ አስቦ ፡ ማዘን ፡ ይገባል ፡ ዕደው ፡ ጻድቃን ፡ ብከይዎ ፡ ለእስጢፋኖስ ፡ ወለሀውዎ ፡ ዓቢየ ፡ ላሀ ፡ እንዲል(፡ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፰ ፡ ፪ ፡)ሞተ ፡ ወልደ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አስቦ ፡ ማዘን ፡ ይገባል ፡ ዮሐንስ ፡ የዕለተ ፡ ዓርቡን ፡ እያሰበ ፡ ፸ ፡ ዘሚን ፡ ቁጺረ ፡ ገጽ ፡ ሁኖ ፡ ዕንባው ፡ እንደ ፡ ሡስሡስት ፡ ውኃ ፡ ሲፈስ ፡ ኑሯል ።

፲፩ ፡ ወናሁ ፡ ውእቱ ፡ ትካዝ ፡ ዘበእንተ ፡ እግዚአብሔር ።
ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብላችሁ ፡ ያዘናችሁት ፡ ኃዘን ።
ጸሀቀ ።
ለአስተዋፅኦ ፡ መትጋትን ።
ወቅሥተ ።
ያባቱን ፡ ሚስት ፡ የነሣውን ፡ የመምህሩን ፡ ሹመት ፡ የተሾመውን ፡ መለየትን ።
ወፍርሃተ ።
አነ ፡ ዘጳውሎስ ፡ ወአነ ፡ ዘአጵሎስ ፡ ወአነ ፡ ዘኬፋ ፡ አለማለትን ።
ወግርማ ።
መፈራትን ።
ወተፋቅሮ ።
ፍቅርን ።
ወተቃኅዎ ።
መንፈሳዊ ፡ ፍክክርን ።
ፍዳ ፡ ገብረ ፡ ለክሙ ።
ፍዳን ፡ አደረገላችሁ ፡ አንድም ፡ ፍዳ ፡ ገብረ ፡ ለክሙ ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ብድራት ፡ አደረገላችሁ ።
እስከ ፡ አቀምክሙ ፡ ርእሰክሙ ፡ በንጽሕ ፡ ወበምግባር ፡ ከመ ፡ ዘኢተአምሩ ፡ ወኢምንተኒ ።
በምግባር ፡ በሃይማኖት ፡ እስከትጸኑ ፡ ድረስ ፡ ደርሳችሁ ፡ ምንም ፡ ምን ፡ እንደማታውቁ ፡ ኹናችሁ ።

፲፪ ፡ ወዘኒ ፡ ዘጸሐፍኩ ፡ ለክሙ ፡ አኮ ፡ በእንተ ፡ ዘገፍዐ ፡ ወዘተገፍዐ ።
ይህንም ፡ የጻፍኩላችሁ ፡ ልጅ ፡ ስለበደለ ፡ አባት ፡ ስለተበደለ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።
ዳዕሙ ፡ ከመ ፡ ይትዐወቅ ፡ ከመ ፡ ጽሕቅሙ ፡ በእንቲአነ ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር ፡ በሚያውቀው ፡ ነገር ፡ ስለኛ ፡ ለምግባር ፡ ለትሩፋት ፡ እንድትተጉ ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፲፫ ፡ ወበእንተዝ ፡ ተፈሣሕነ ።
ስለዚህም ፡ ደስ ፡ አለን ፡ (አለ ፡ ) ጢሞቴዎስ ፡ እንበለ ፡ ክታብ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ።
ወዓዲ ፡ ዲበ ፡ ፍሥሐነ ፡ ተፈሣሕነ ።
ዳግመኛም ፡ በደስታችን ፡ ላይ ፡ ደስ ፡ አለን ፡ (አለ ፡ ) ጢሞቴዎስ ፡ ክታብ ፡ ይዞ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ።
ወፈድፋደሰ ፡ በፍሥሓ ፡ ቲቶ ።
ይልቁንም ፡ በቲቶ ፡ ደስታ ፡ ደስ ፡ አለን ፡ (አለ ፡ ) እንበለ ፡ ክታብ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ አንድም ፡ ወበእንተዝ ፡ ተፈሣሕነ ።
ጢሞቴዎስ ፡ ክታብ ፡ ይዞ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወዓዲ ፡ ዲበ ፡ ፍሥሐነ ፡ ተፈሣሕነ ።
ቲቶ ፡ እንበለ ፡ ክታብ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ።
ወፈድፋደሰ ፡ በፍሥሓ ፡ ቲቶ ።
ይልቁንም ፡ ቲቶ ፡ ክታብ ፡ ይዞ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ።
አንድም ፡ ወበእንተዝ ፡ ተፈሣሕነ ።
ቲቶ ፡ እንበለ ፡ ክታብ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ።
ወዓዲ ፡ ዲበ ፡ ፍሥሓነ ፡ ተፈሣሕነ ።
ክታብ ፡ ይዞ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ።
ወፈድፋደሰ ፡ በፍሥሓ ፡ ቲቶ ።
ይልቁንም ፡ ዘመድ ፡ ዘመድ ፡ ስላላችሁት ፡ ደስ ፡ አለን ።
እስመ ፡ አዕረፍክምዋ ፡ ለነፍሱ ፡ በኀበ ፡ ኵልክሙ ።
ሰውነቱን ፡ ከኹላችሁ ፡ ዘንድ ፡ አሳርፋችኋታልና ፡ (አሴ ፡ ) ዘመድ ፡ ዘመድ ፡ ብላችኋታልና ፡ (አትረፍ ክምዎ ፡ ይላል ፡ ) ባይ ፡ ገሬውን ፡ ሰዳችሁታልና ።

፲፬ ፡ እስመ ፡ ኢያስተኀፈርከሙኒ ፡ በኵሉ ፡ ዘተመካሕኩ ፡ ሎቱ ፡ በእንቲአክሙ ።
በናንት ፡ ተመክቼ ፡ በነገርሁት ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አላሳፈራችሁኝምና ።
እማነ ፡ ረሰይክሙ ፡ ለነ ፡ ዘነገርናሁ ፡ ከማሁ ፡ እሙነ ፡ ኮነ ።
በእውነት ፡ የነገርነውን ፡ እንደነገርነው ፡ እውነት ፡ አደረጋችሁልን ፡ እንጂ ።
፲፭ ፡ ወፈድፋደ ፡ የአኵተክሙ ፡ ወይዜክረክሙ ፡ ዘከመ ፡ ትትኤዘዙ ፡ ሎቱ ።
ይልቁንም ፡ እንደታዘዛችሁለት ፡ መጠን ፡ እያነሣሣ ፡ ያመሰግናችኋል ።
ወትትዌክፍዎ ፡ በፍርሀት ፡ ወበረዓድ ፡ (ም ፡ ፪ ፡ ፱ ።)
በፍርሀት ፡ በረዓድ ፡ ኾናችሁ ፡ እንደተቀበላችሁት ፡ መጠን ።
፲፮ ፡ ወእትፌሣሕ ፡ ባሕቱ ።
(ባሕቱ ፤ ቦቱ ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ) በዚህም ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።
እስመ ፡ በኵሉ ፡ እትአመነክሙ ።
ቲቶ ፡ በነገረኝ ፡ ነገር ፡ ኹሉ ፡ አምናችኋለሁና ።

## ምዕራፍ ፡ ፰ ።

### ክፍል ፡ ፲ ።

፩ ፡ እነግረክሙ ፡ አኀዊነ ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘተውህበ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ዘመቄዶንያ ( ሮሜ ፡ ፲፭፡ ፳፯ ፡ ፩ ፡ ቆሮ ፲፯ ፡ ፩ ።)
ወንድሞቻችን ፡ በመቄዶንያ ፡ ላሉ ፡ ምእመናን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተሰጠ ፡ የልጅነትን ፡ ነገር ፡ እን ግራችኋለሁ ፡ (እንድም ፡ ) ዘአመቄዶንያ ፡ ይላል ፡ እንደ ፡ ያሬድ ፡ አብነት ፡ በመቄዶንያ ፡ ካሉ ፡ ምእመ ናን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተሰጠ ፡ የአስተዋፅኦውን ፡ ነገር ፡ እነግራችኋለሁ ፡ ዝኒ ፡ ሀብተ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲል ።

፪ ፡ እስመ ፡ እምብዙኅ ፡ መከራ ፡ ሕማሞሙ ፡ ፈድፈደ ፡ ፍሥሐሆሙ ።
በብዙ ፡ መከራ ፡ ከመፈተናቸው ፡ የተነሣ ፡ ደስታቸው ፡ በዝታለችና ፡ በመቄዶንያ ፡ ላሉ ፡ ምእመናን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተሰጠ ፡ የልጅነትን ፡ ነገር ፡ እነግራችኋለሁ ።
ወምስለ ፡ ዕመቀ ፡ ንዴቶሙ ፡ ፈድፈደት ፡ ፍሥሓ ፡ ብዕሎሙ ።

ከንዴታቸውም ፡ ጽናት ፡ ጋራ ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ እንስጥ ፡ ማለታቸው ፡ ጸንታለችና ፡ በመቄዶንያ ካሉ ፡ ምእመናን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የተሰጠ ፡ የአስተዋፅኦውን ፡ ነገር ፡ እነግራችኋለሁ ።

፫ ፡ እስመ ፡ ለልየ ፡ ሰማዕቶሙ ፡ ከመ ፡ በአምጣነ ፡ ኃይሎሙ ፡ ወዘእንበለ ፡ ኃይሎሙሂ ፡ ጥቡዓን ፡ እሙንቱ ፡ ለሊሆሙ ፡ (ም ፡ ፱ ፡ ፩ ፡ ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፩ ፡ ፳፱ ።)
ቢቻላቸውም ፡ ባይቻላቸውም ፡ እንስጥ ፡ በማለት ፡ ቆርጠው ፡ እንዳሉ ፡ እኔ ፡ ምስክራቸው ፡ ስለኾንኹ ።

፬ ፡ ወብዙኅ ፡ አስተብቍዑነ፡ በእንተ ፡ ሱታፌ ፡ መልእክተ ፡ ቅዱሳን ።
ለቅዱሳን ፡ ለነዳያን ፡ ስለሚኾን ፡ ስለአስተዋፅኦውም ፡ አንድነት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ መላልሰው ፡ ማለዱን ፡ እናንተ ፡ ጉልበት ፡ እኛ ፡ ክብት ፡ እንኹን ፡ ብለው ።

፭ ፡ ወእኮሂ ፡ በከመ ፡ ተሐዘብነ ።

www.ethiopianorthodox.org

ነገር ፡ ግን ፡ እንደጠረጠርነው ፡ አይደለም ፡ አሕዛብ ፡ የሰው ፡ ክብት ፡ ይቀማሉ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ፡ ክብታቸውን ፡ ይሰጣሉ ፡ አይባሉምና ።

እስመ ፡ ሰሊሆሙ ፡ አቅደሙ ፡ በፈቃዶሙ ፡ ወመጠዉ ፡ ነፍሶሙ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እስቀድመው ፡ ወደው ፡ ክብታቸውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሰጥተዋልና ፡ (ሐተታ ፡ ) ነፍሶሙ ፡ አለው ፡ የበሉት ፡ የጠጡት ፡ ደም ፡ ይኾናል ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነፍስ ፡ ከሥጋ ፡ ጋራ ፡ ተዋሕዳ ፡ ትኖራለችና ፤ እስመ ፡ ነፍስ ፡ ተኃድር ፡ በደም ፡ እንዲል ።

ወሰነኒ ።

ለኛም ፡ የጦም ፡ ቆሎ ፡ የበዓል ፡ ዶሮ ፡ ብለውናል ። በከመ ፡ ፈቀደ ፡ ማንሻ ።

እስመ ፡ ለሊሆሙ ፡ አቅደሙ ፡ በፈቃዶሙ ፡ ወመጠዉ ፡ ነፍሶሙ ፡ ለእግዚአብሔር ።

እንድም ፡ አስቀድመው ፡ ወደው ፡ ሰውነታቸውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አስገዝተዋልና ፡ እኮ ፡ በከመ ፡ ተሐዘብነ ።

ወለነኒ ፡ በከመ ፡ ፈቀደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወእስተፍሥሐነ ፡ ቲቶ ።

ለኛም ፡ እግዚአብሔር ፡ በሚወደው ፡ ግብር ፡ ጸንትዋል ፡ ብሎ ፡ የናንተን ፡ ነገር ፡ ነግሮ ፡ ቲቶ ፡ ደስ ፡ አሰኘን ።

፮ ፡ ወእስተብቍዕናሁ ፡ ከመ ፡ ይፈጽም ፡ ለክሙ ፡ ጸጋሁ ፡ በከመ ፡ ወጠነ ። ቲቶ ፡ እንደጀመረ ፡ የጀመረውን ፡ በጎነት ፡ ይፈጽምላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ማለድነው ። እንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደጀመረ ፡ የጀመረውን ፡ ቸርነት ፡ ይፈጽምላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ለመነው ።

፯ ፡ እስመ ፡ ፈድፈድክሙ ፡ በኵሉ ።

በሥራው ፡ ኹሉ ፡ ፍጹማን ፡ ኾናችኋልና ።

በሃይማኖት ።

በኵሉ ፡ ያለውን ፡ ይተረትራል ፡ በሃይማኖት ።

ወበቃል ፡ ባነጋገር ።

ወበጥበ ፡ በዕውቀት ።

ወበጽሂቅ ፡ በኵሉ ፡ ዘኮነ ፡ ኀቤክሙ ።

ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ በሚኾነው ፡ ኹሉ ፡ በመትጋት ።

ወእፍቅሮተክሙ ፡ ኪያነ ።

እኛንም ፡ በመውደድ ፡ ፍጹማን ፡ ሁናችኋልና ። (ከማሁ ፡ ማንሻ ፡ ) እንድም ፡ እኛንም ፡ በመውደድ ፡ ላይ ከማሁ ፡ አፈድፍዱ ፡ ካዕበ ፡ ውስተ ፡ ዛቲ ፡ ጸጋ ።

እስተዋፅኦውን ፡ አብዝታችሁ ፡ አወጣጡ ።

፰ ፡ ወኢኮ ፡ በግብር ፡ እብለክሙ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ግድ ፡ አድርጉት ፡ የምላችሁ ፡ አይደለም ።

እስመቦ ፡ እለ ፡ ይጽሀቅዎ ፡ እምኔክሙ ።

ከናንተ ፡ ወገን ፡ ይኸንን ፡ አስተዋፅኦውን ፡ ለማወጣጣት ፡ የሚተጉ ፡ የሚወዱ ፡ ሰዎች ፡ አሉና ።

ወናሁ ፡ አአመርኩ ፡ ጽንዐ ፡ አፍቅሮትክሙ ።

እነኾ ፡ የሃይማኖታችሁን ፡ ጽናት ፡ የፍቅራችሁን ፡ ብዛት ፡ አውቃለሁና ፡

፱ ፡ ተአምሩ ፡ ጸጋሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስንም ፡ ቸርነቱን ፡ ታውቃላችሁና ።

በእንቲአክሙ ፡ እንደየ ፡ ርእሶ ፡ እንዘ ፡ ባዕል ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡ አንትሙኒ ፡ ትብዐሉ ፡ በንዴተ ፡ ዚአሁ ፡ (ማቴ ፡ ፳ ፡ ፳፰ ።)

በሉ ፡ ንዴት ፡ እናንተ ፡ ትከብሩ ፡ ዘንድ ፡ ባዕል ፡ ሲኾን ፡ ስለናንተ ፡ ራሱን ፡ ነዳይ ፡ እንዳሰኘ ።

፲ ፡ ወበዝንቱ ፡ እምክርኩክሙ ፡ ዘይበቍዐክሙ ።

በዚህም ፡ የሚረባችሁን ፡ የሚጠቅማችሁን ፡ ነገር ፡ መክርኋችሁ ፡ እንጂ ፤ ስመክራችሁ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ እኮ ፡ በግብር ።

እስመ ፡ ፈቀድክሙ ፡ ወእቅደምክሙ ፡ ትመጥዉ ፡ ነፍስክሙ ፡ እምቀዳሚ ፡ ዓም ።

ካምና ፡ ጀምሮ ፤ ከጥንተ ፡ ስብከት ፡ ጀምሮ ፡ ቢል ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ክብታችሁን ፡ ታወጣጡ ፡ ዘንድ ፡ አስቀድማችሁ ፡ ወዳችኋልና ፡ እምክርኩክሙ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፩ ፡ ይእዜሰ ።

አሁንስ ፡ እንዲያው ፡ በምኞትን ፡ ትቀሩ ።

ግበሩሂ ።

እስተዋፅኦውን ፡ አወጣጡ ፡

ወፈጽሙሂ ፡

ለወሳጅ ፡ ስጡ ፤ አንድም ፡ (ግበሩሂ ፡ ) ለወሳጅ ፡ ስጡ ፡ (ወፈጽሙሂ ፡ ) ኢየሩሳሌም ፡ አድርሱ ፤ አንድም ፡ ግበሩሂ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ አድርሱ ፡ (ወፈጽሙሂ ፡ ) በልበ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ቀልፉ ።

እስመ ፡ ፈቂድኒ ፡ እምፈቲው ።

ቁርጥ ፡ ሐልዮ ፤ ከንቅዕ ፡ ሐልዮ ፡ የተነሣ ፡ ነውና ።

ወገቢርኒ ፡ እምረኪብ ።

መስጠትም ፡ ከማግኘት ፡ የተነሣ ፡ ነውና ፡ ግበሩሂ ፡ ወፈጽሙሂ ።

፲፪ ፡ ወእምከመሰ ፡ ፈቂድ ፡ ሀሎ ፡ ይትመዘገን ፤ በዘይትከሀሎ ። መስጠቱንስ ፡ መውደዱ ፡ ካለ ።

ወአኮ ፡ በአምጣነ ፡ ዘኢይትከሀሎ ። (ምሳ ፡ ፫ ፡ ፳፯ ፡ ማር ፡ ፲፪ ፵፫ ።)

የሌለውን ፡ ገንዘብ ፤ ሰጥቶ ፡ ያይደለ ፡ መስጠቱን ፡ በመውደዱ ፡ ብቻ ፡ ይመሰገናል ። ዘሰ ፡ ይፈቅድ ፡ ይግበር ፡ ወኢይክል ፡ ይትጌረዮ ፡ ለዘይገብር ፡ ወይክል ፡ እንዲል ፡ (አፈ ፡ ወር ።) አንድም ፡ የሌለውን ፡ ብዙውን ፡ ሰጥቶ ፡ ያይደለ ፡ ያለውን ፤ ጥቂቱን ፡ ሰጥቶ ፡ ይመሰገናል ።

፲፫ ፡ ወዘአኮ ፡ ከመ ፡ ባዕድ ፡ ያዕርፍ ፡ ኪያከሙ ፡ ናጠውቅ ።

ነገር ፡ ግን ፡ በናንተ ፡ ከብት ፡ ሌላው ፡ ተድላ ፡ ደስታ ፡ ሊያደርግበት ፡ እናንተን ፡ የምናስቸግር ፡ አይደለንም ።

ዳዕሙ ፡ ተሀልው ፡ ዕሩየ ፡ በዝ ፡ መዋዕል ።

በዚህ ፡ ወራት ፡ እነዋራችሁ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

እስመ ፡ ተረፈ ፡ ዚአከሙ ፡ ውስተ ፡ ንትጋ ፡ እልክቱ ፡ ይከውን ።

የናንተ ፡ ተረፍ ፡ የነዚያን ፡ ሕጸጽ ፡ ይመላልና ።

፲፬ ፡ ወተረፈ ፡ ዚአሆሙ ፡ ውስተ ፡ ንትጋ ፡ ዚአከሙ ፡ ይከውን ።

የነዚያም ፡ ተረፍ ፡ የናንተን ፡ ሕጸጽ ፡ ይመላልና ።

ከመ ፡ ይኩን ፡ ሀልዎትከሙ ፡ ዕሩየ ፡ በኵሉ ። (ም ፡ ፱ ፡ ፲፪ ።)

እነዋራችሁ ፡ በሥራው ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ።

፲፭ ፡ እስመ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘበ ፡ ብዙኀ ፡ ኢያትረፈ ።

ብዙ ፡ ያሰው ፡ አልተረፈውም ።

ወዘበ ፡ ውሑድ ፡ ኢያሕጸጸ ፡ ዘዕአ ፡ (፲፯ ፡ ፲፰ ።)

ጥቂትም ፡ ያለው ፡ አላነሰውም ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡ (ሐተታ) ፡ ዘበ ፡ ብዙኀ ፤ በእሪቱ ፤ እምሳ ፡ ጎሞር ፡ ያገባ ፡ ነው ፤ አልተረፈውም ፡ አለ ፡ እምሳ ፡ ኾኖ ፡ ይመገበዋልና ፤ ዘበ ፡ ውሑድ ፡ አምስት ፡ ጎሞር ፡ ያገባ ፡ ነው ፤ አላነሰውም ፡ አለ ፡ አምስት ፡ ኾኖ ፡ ይመገበዋልና ። አንድም ፡ በአዲሱ ፡ (ዘበ ፡ ብዙኀ ፡ ) ብዙ ፡ ብዕለ ፡ ሥጋ ፡ ያላቸው ፡ አሕዛብ ፡ እሉ ፡ አልተረፋቸውም ፡ አለ ፡ ለምእመናን ፡ ይሰጡሰታልና ። (ዘበ ፡ ውሑድ ፡ ) ጥቂት ፡ ብዕለ ፡ ሥጋ ፡ ያላቸው ፡ ምእመናን ፡ እሉ ፡ እንደመጠኑ ፡ ቱከል ፡ ተክለው ፡ ተገብሮ ፡ ይዘው ፡ ይኖራሉ ። አላነሳቸውም ፡ አለ ፡ አሕዛብ ፡ ይጨምሩላቸዋልና ። አንድም ፡ (ዘበ ፡ ብዙኀ ፡ ) ብዙ ፡ ብዕለ ፡ ነፍስ ፡ ያላቸው ፡ ምእመናን ፡ እሉ ፡ እልተረፋቸውም ፡ አለ ፡ ለአሕዛብ ፡ ይጸልያሉና ። (ዘበ ፡ ውሑድ ፡ ) ጥቂት ፡ ብዕለ ፡ ነፍስ ፡ ያላቸው ፡ አሕዛብ ፡ እሉ ፡ አላነሳቸውም ፡ አለ ፡ ምእመናን ፡ ይጸልዩላቸዋልና ።

(አንድም) ፡ ወዘአኮ ፡ ከመ ፡ ባዕድ ፡ ያዕርፍ ፡ ኪያከሙ ፡ ናጠውቅ ።

ምጽዋት ፡ በባለ ፡ ጸጋ ፡ እንጂ ፡ በድኀ ፡ አልታዘዘም ፡ እንዳይሉት ፡ በናንተ ፡ ከብት ፡ ሌላው ፡ አርፎበት ፡ ሊኖር ፡ እናንተን ፡ የምናስጨንቃችሁ ፡ አይደለም ።

ዳዕሙ ፡ ተሀልው ፡ ዕሩየ ፡ በዝ ፡ መዋዕል ።

በዚህ ፡ ወራት ፡ እነዋራችሁ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

እስመ ፡ ተረፈ ፡ ዚአከሙ ፡ ውስተ ፡ ንትጋ ፡ እልክቱ ፡ ይከውን ።

የናንተ ፡ ብዙ ፡ ከነዚያ ፡ ጥቂት ።

www.ethiopianorthodox.org

ወተረፈ ፡ ዚአሆሙ ፡ ውስተ ፡ ንትጋ ፡ ዚአክሙ ፡ ይከውን ።

የነዚያ ፡ ጥቂት ፡ ከናንተ ፡ ብዙ ፡ አንድ ፡ ይኾናልና ።

ከመ ፡ ይኩን ፡ ሀልዎትክሙ ፡ ዕሩየ ፡ በኵሉ ።

በሥራው ፡ ኹሉ ፡ አነዋራችሁ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ይኾን ፡ ዘንድ ።

እስመ ፡ ከመዝ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘበ ፡ ብዙኀ ፡ ኢያትረፈ ።

ብዙ ፡ ያለው ፡ አልተረፈውም ።

ወዘበ ፡ ውኁድ ፡ ኢያሕጸጸ ።

ጥቂትም ፡ ያለው ፡ አላነሰውም ፡ ብሎ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደተናገረ ፤ የናንተ ፡ ብዙ ፡ ከነዚያ ፡ ጥቂት ፡ የነዚያ ፡ ጥቂት ፡ ከናንተ ፡ ብዙ ፡ አንድ ፡ ይኾናል ።

አንድም ፡ ዘበ ፡ ብዙኀ ፡ ) በአሪቱ ፡ የቅዳሜው ፡ ዓርብ ፡ ተደርቦ ፡ ይወርድላቸው ፡ ነበር ፡ ሳስቶ ፡ ከኹለት ፡ ጎሞር ፡ እትርፎ ፡ ያገባ ፡ ነው ፤ አልተረፈውም ፡ አለ ፡ ሸቶበት ፡ ተልቶበት ፡ አውጥቶ ፡ ይጥለዋልና ። (ዘበ ፡ ውኁድ ፡ ) ያኑ ፡ ኹለት ፡ ጎሞር ፡ ያገባ ፡ ነው ። አላነሰውም ፡ አለ ፡ ሳይሸትበት ፡ ሳይትላበት ፡ ይመገበዋልና ። አንድም ፡ (ዘበ ፡ ብዙኀ ፡ ) በሐዲሱ ፡ ብዙ ፡ ብዕለ ፡ ሥጋ ፡ ያላቸው ፡ እስራኤል ፡ አሉ ፡ አልተረፋቸውም ፡ አለ ፡ ሳይሰጡለት ፡ ሳይመጸውቱለት ፡ እሳት ፡ ወራሪ ፡ ዘራፊ ፡ አንበጣ ፡ በልቶባቸው ፡ ወርጭ ፡ በረድ ፡ መትቶባቸው ። (ዘበ ፡ ውኁድ ፡ ) ጥቂት ፡ ብዕለ ፡ ሥጋ ፡ ያላቸው ፡ ምእመናን ፡ አሉ ፡ አላነሳቸውም ፡ (አለ ፡) እሳት ፡ ወራሪ ፡ ዘራፊ ፡ አንበጣ ፡ ሳይበላባቸው ፡ ወርጭ ፡ በረድ ፡ ሳይመታባቸው ፡ የተረፈውን ፡ እግዚአብሔር ፡ አበርክቶላቸው ።

## ክ ፍ ል ፡ ፯

፲፮ ፡ እኩት ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘወሀበነ ፡ ለነሂ ፡ ንጽሐቅ ፡ በእንቲአክሙ ። (ም ፡ ፱ ፡ ፲፭ ።)

ለእኛም ፡ ስለናንተ ፡ እንትጋ ፡ ዘንድ ፡ መትጋቱን ፡ የሰጠን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

በከመ ፡ ይቤ ፡ ቲቶ ።

ቲቶ ፡ እንደተናገረ ። እኩት ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘወደየ ፡ ጸሕቀ ፡ ውስተ ፡ ልበ ፡ ቲቶ ፡ ብሎ ፡ በጽርእ ፡ ምላሹ ፡ ያነበዋል ።

፲፯ ፡ እስመ ፡ የአዙተክሙ ።

ያመሰግናችኋልና ።

ወተወክፈ ፡ ለክሙ ፡ ሥላጤክሙ ።

ፍጹምነታችሁንም ፡ ተረድቶላችኋልና ።

ወአስተፋጠነ ፡ ይምጻእ ፡ ኀቤክሙ ፡ ጥቡዐ ።

ወደናንተም ፡ ሊመጣ ፡ ወዶ ፡ ይቸኩላል ።

፲፰ ፡ ወፈኖነ ፡ ምስሌሁ ፡ እኁነ ፡ ዘንዕድዎ ፡ ኵሉ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በእንተ ፡ ትምህርቱ ።

ስለ ፡ ትምህርቱም ፡ ምእመናን ፡ ኹሉ ፡ የሚያመሰግኑት ፡ የሚያከብሩት ፡ ወንድማችን ፡ ሉቃስንም ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ሰደነዋል ።

፲፱ ፡ ዓዲ ፡ ሥዩም ፡ ውእቱ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ።

ዳግመኛም ፡ ለምእመናን ፡ የተሾመ ። ዓዲ ፡ ለሐዋርያት ፡ ነው ።

ወኅቡር ፡ ምስሌነ ፡ በዛቲ ፡ ጸጋ ፡ እንተ ፡ ተልእክነ ፡ ለስብሐተ ፡ እግዚአብሔር ።

የእግዚአብሔርን ፡ ጌትነቱን ፡ ለማገልገል ፡ በተሾምናት ፡ ሐዋርያነት ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

አንድም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ክብሩን ፡ ለማውረስ ፡ በተቀበልናት ፡ ልጅነት ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነው ።

ከመ ፡ ንትፈጋሕ ።

ደስ ፡ ይለን ፡ ዘንድ ።

፳ ፡ ወተዓቀብዎ ፡ ለዝንቱ ።

ዘመድ ፡ ዘመድ ፡ በሉት ።

ከመ ፡ ኢታንውርዋ ፡ ለመልእክትክሙ ።

ሕጋችሁ ፡ ወንጌልን ፡ እንዳታስነቅፏት ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፩ ፤ ወሠናየ ፤ ሐልዩ ፤ ለቅድመ ፤ እግዚአብሔር ፤ ወለቅድመ ፤ ሰብእ ።
　　በእግዚአብሔርም ፤ በሰውም ፤ ዘንድ ፤ የተወደደውን ፤ ሥሩ ፤ ሥሩ ።

፳፪ ፤ ወናሁ ፤ ፈነውነ ፤ ምስሌሆሙ ፤ ዓዲ ፤ እኁነ ፤ ዘአመከርናሁ ፤ በብዙኅ ።
　　በብዙ ፤ ወገን ፤ የፈተነው ፤ ወንድማችን ፤ አጽሉስንም ፤ ዳግመኛ ፤ ከነሱ ፤ ጋራ ፤ ሰደነዋል ።
ወረከብናሁ ፤ ከመ ፤ ጼሐቂ ፤ ውእቱ ፤ በኵሉ ።
　　በኹሉ ፤ ዘንድ ፤ ዐዋቂ ፤ ኾኖ ፤ ያገኘነው ፤ እንድም ፤ ዐዋቂ ፤ እንደኾነ ፤ ያወቅነው ።
ወይእዜኒ ፤ ፈድፋደ ፤ ያስተፋጥን ፤ ይምጻእ ፤ ኀቤክሙ ፤ ወጽሒቀ ፤ በእንቲአክሙ ።
　　ይልቁንም ፤ እሱ ፤ ዛሬ ፤ ሊያችሁ ፤ ወዶ ፤ ወደናንት ፤ ሊመጣ ፤ ይቸኩላል ።
እስመ ፤ ብዙኀ ፤ ያፈቅረክሙ ።
　　ፈጽሞ ፤ ይወዳችኋልና ።

፳፫ ፤ ወእመኒ ፤ በእንተ ፤ ቲቶ ፤ ሱታፌ ፤ ዘኅብር ፤ ምስሌሁ ፤ ግብረ ፤ (ም ፤ ፯ ፤ ፲፫ ። ፲፱ ፤ ፲፰ ።)
　　በሐዋርያነት ፤ አንድ ፤ ኾነን ፤ በመከራ ፤ ለምንተባበር ። እንድም ፤ በሃይማኖት ፤ አንድ ፤ ኾነን ፤ በል
ጅነት ፤ ለምንተባበር ፤ ለቲቶም ፤ ቢኾን ።
ወበእንተኒ ፤ አኀዊነ ፤ ሐዋርያት ፤ ዘቤተ ፤ ክርስቲያን ፤ ስስብሐተ ፤ እግዚአብሔር ፤ (ሮሜ ፤ ፲፯ ፤ ፯ ።)
　　የእግዚአብሔርን ፤ ጌትነቱን ፤ ለማገልገል ፤ በምእመናን ፤ ላይ ፤ ለተሾሙ ፤ ለወንድሞቻችን ፤ ስሐ
ዋርያትም ፤ ቢኾን ፤ (አጽሉስና ፤ ሉቃስ ፤ ናቸው ። )

፳፬ ፤ ይእዜሰ ፤ አርእዩ ፤ ሎሙ ፤ ክሡተ ፤ ተፋቅሮተክሙ ።
　　ዛሬስ ፤ ፍቅራችሁን ፤ ግለጡላቸው ።
ዝንቱ ፤ ውእቱ ፤ ዘቦቱ ፤ ንትሜካሕ ፤ ብክሙ ፤ ንሕነ ።
　　እኛ ፤ በናንተ ፤ የምንመካው ፤ ትምክህት ፤ ይህ ፤ ነውና ፤ (እስ ፤ ) ፍቅርን ፤ መያዛችሁ ፤ ነውና ።
ወይእዜኒ ፤ አርእዩ ፤ ሎሙ ፤ በቅድመ ፤ ቤተ ፤ ክርስቲያን ፤ (ም ፤ ፯ ፤ ፲፬ ።)
　　ዛሬም ፤ በምእመናን ፤ ፊት ፤ ፍቅራችሁን ፤ ግለጡላቸው ፤ በሙ ፤ ቢል ፤ በነሱ ፤ ለሌላው ፤ ግለጡላቸው ።

## ምዕራፍ ፤ ፱ ።

## ክፍል ፤ ፳ ።

፩ ፤ ወበእንተሰ ፤ መልእክተ ፤ ቅዱሳን ፤ ብዙኅ ፤ ብየ ፤ ዘእጽሕፍ ፤ ለክሙ ፤ (ም ፤ ፰ ፤ ፬ ፤ ፳ ።)
　　ለቅዱሳን ፤ ነዳያን ፤ ስለሚኾን ፤ አስተዋፅኦስ ፤ የምጽፍላችሁ ፤ ብዙ ፤ ነበረኝ ።

፪ ፤ እስመ ፤ አእመርኩ ፤ ከመ ፤ ትጽሕቁ ፤ አንትሙ ።
　　እናንተ ፤ እንድትተጉ ፤ አውቃለሁና ፤ ተውሁት ፤ እንጂ ።
ወበእንተዝ ፤ ንዕድኩክሙ ፤ በኀበ ፤ ሰብአ ፤ መቄዶንያ ።
　　ስለዚህ ፤ በመቄዶንያ ፤ ሰዎች ፤ ዘንድ ፤ አመሰገንኋችሁ ።
ወእቤሎሙ ፤ እስመ ፤ ሰብአ ፤ አካይያ ፤ አስተዳሰዉ ፤ እምቀዳሚ ፤ ዓም ።
　　የአካይያማ ፤ ሰዎች ፤ ካምና ፤ ጀምሮ ፤ አስተዋፅኦውን ፤ አወጣጥተዋል ፤ ብዬ ።
ወናሁ ፤ አጽሐቆሙ ፤ ተቃሕዎተ ፤ ዚአክሙ ፤ ለብዙኃን ፤ ሰብእ ፤ (ም ፤ ፰ ፤ ፲፱ ።)
　　እነሆ ፤ ለብዙ ፤ ሰዎች ፤ እናንተን ፤ መፈካከር ፤ አምሯቸዋል ።

፫ ፤ ወፈነውናሆሙ ፤ ለአኃው ፤ ከመ ፤ ኢይኩንነ ፤ ሐሰተ ፤ በኀቤሆሙ ፤ ዘንእድናክሙ ፤ በዝንቱ ።
　　በዚህ ፤ እናንተን ፤ እያመሰገን ፤ የነገርናቸው ፤ ነገር ፤ በኔሱ ፤ ዘንድ ፤ ሐሰት ፤ እንዳይኾን ፤ አኃውን ፤
ሰደናቸዋል ። አኃውን ፤ የሰደድናቸው ፤ ሐሰት ፤ እንዳይኾንብን ፤ ነው ።
ወከመ ፤ ይርከቡክሙ ፤ ድልዋኒክሙ ፤ በከመ ፤ ንቤሎሙ ፤ (ም ፤ ፰ ፤ ፳፬ ።)
　　አስተዋፅኦውን ፤ አወጣጥተዋል ፤ ብለን ፤ እንደነገርናቸው ፤ አስተዋፅኦውን ፤ አወጣጥታችሁ ፤ ያገ
ኙዋችሁ ፤ ዘንድ ።

፬ ፤ ወእመቦ ፤ ከመ ፤ መጽኡ ፤ ምስሌየ ፤ ሰብአ ፤ መቄዶንያ ።
　　የመቄዶንያ ፤ ሰዎች ፤ ምናልባት ፤ ከኔ ፤ ጋራ ፤ ቢመጡ ፤ እንድም ፤ የሚመጡት ፤ ምምጣት ፤ ቢኖር ።
　　እንድም ፤ እምና ፤ እንደመጡ ፤ ዘንድሮ ፤ ቢመጡ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወረከቡከሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ታስተዳልዉ ፡ ንትኀፈር ፡ ንሕነ ።

አስተዋፅኦውን ፡ ሳታወጣጡ ፡ ቢያገኙዋችሁ ፡ እኛ ፡ እናፍራለንና ።

ከመ ፡ ኢይበሉከሙ ፡ አስተትከሙ ።

ሥርዓት ፡ አፈረሳችሁ ፡ ብለው ፡ እንዳይነቅፏችሁ ፡ (ፈነውናሆሙ) ።

፭ ፡ አስተበቍዐክሙ ፡ አኃዊነ ፡ ግብረ ፡ ረስይዎ ።

ወንድሞቻችን ፡ አስተዋፅኦውን ፡ ማወጣጣቱን ፡ ግድ ፡ አድርጉት ፡ ብዬ ፡ እማልዳችኋለሁ ።

ወአስተዳልዉ ፡ ውእተ ፡ በረከተክሙ ።

አስተዋፅኦውን ፡ አወጣጡ ፡ ብዬ ፡ (ሐተታ ፡ ) በረከተ ፡ ነፍስን ፡ የሚያገኙበት ፡ ስለኾነ ፡ በረከት ፡ አለው ።

ወሥርዐ ፡ ዘነገርኩክሙ ፡ አንተ ፡ ላቲ ፡ ድልዋን ፡ አንትሙ ።

ኹሉ ፡ ብእሲ ፡ እምኔክሙ ፡ ይዝግብ ፡ ሎቱ ፡ ዘተሠርሐ ፡ ብዬ ፡ እንደነገርኋችሁ ፡ ልታወጣጡት ፡ የሚገባችሁንም ፡ አወጣጡ ።

ወከመዝ ፡ ረሲዩዎ ፡ ከመ ፡ ዘበረከት ፡ ወአኮ ፡ ከመ ፡ ዘበትዕግልት ።

ሠርቃችሁ ፡ ቀምታችሁ ፡ ያመጣችሁትን ፡ ያይደለ ፡ በረከተ ፡ ነፍስ ፡ የምታገኙበት ፡ እንደመኾኑ ፡ የደከማችሁበትን ፡ ገንዘባችሁን ፡ አወጣጡ ። አንድም ፡ ሰርቀው ፡ ቀምተው ፡ እንደወሰዱባችሁ ፡ እያዘናችሁ ፡ ያይደለ ፡ በረከተ ፡ ነፍስ ፡ የምታገኙበት ፡ እንደመኾኑ ፡ ደስ ፡ እያላችሁ ፡ አወጣጡ ።

፮ ፡ ወዘሰ ፡ ጠዊኦ ፡ ይዘርኦ ፡ ለዝንቱ ፡ ከማሁ ፡ ይጠውእ ፡ ሎቱኒ ፡ ማዕረሩ ፡

ጨብጦ ፡ የዘራ ፡ ጨብጦ ፡ ያገባል ፡ (አሰ ፡ ) ጥቂት ፡ የዘራ ፡ ጥቂት ፡ መከሩን ፡ ያገኛል ።

ወዘሰ ፡ በበረከት ፡ ይዘርኦ ፡ በበረከት ፡ የአርሮ ፡ (ምሳ ፡ ፲፩ ፡ ፳፬ ፡ ፲፱ ፡ ፲፯ ።)

ታፍኖ ፡ የዘራ ፡ ግን ፡ ታፍኖ ፡ ያገባል ፡ (አሰ ፡ ) ብዙ ፡ የዘራ ፡ ብዙ ፡ መከሩን ፡ ያገኛል ። እንደዚህም ፡ ኹሉ ፡ ጥቂት ፡ የመጸወተ ፡ ጥቂት ፡ ዋጋውን ፡ ያገኛል ፡ ብዙ ፡ የመጸወተም ፡ ብዙ ፡ ዋጋውን ፡ ያገኛል ።

፯ ፡ ወኵሉ ፡ በከመ ፡ አደሞ ፡ ልቡ ፡ ይግበር ፡

ኹሉም ፡ ልቡ ፡ እንደወደደው ፡ እንደወደደው ፡ ያድርግ ።

እስመ ፡ ኢኮነ ፡ በአገብሮ ።

የስጦታ ፡ ነገር ፡ በማገበር ፡ አይኾንምና ።

ዳዕሙ ፡ በፍሥሓ ፡ ሰየሀቡ ።

ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ይስጡ ፡ እንጂ ።

እስመ ፡ ከማሁ ፡ ያፈቅር ፡ እግዚአብሔር ። (ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፰ ።)

እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ የሚሰጠውን ፡ ሰው ፡ ይወዳልና ፡ ብእሴ ፡ ወሀቤ ፡ ወፍሡሓ ፡ ያፈቅር ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲል ፡ (ሰሎ ፡ )

፰ ፡ ወይክል ፡ እግዚአብሔር ፡ አፈድፍዶ ፡ ለክሙ ፡ በረከቶ ፡ ከመ ፡ ያብዝኆ ።

ስጦታችሁሰት ፡ የተረፈውንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሊያበረክትላችሁ ፡ ይቻለዋል ።

ወታተርፍዎ ፡ ለኵሉ ።

ለኹሉ ፡ ታተርፉታላችሁ ።

ወታፈደፍዱ ፡ በገቢረ ፡ ሠናይ ።

በበጎ ፡ ሥራ ፡ ታበዙታላችሁ ።

፲ ፡ በከመ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፍ ፡ ዘረወ ፡ ወወሀበ ፡ ለነዳይ ፡ ወጽድቁኒ ፡ ለዓለም ፡ ይነብር ፡ (መዝ ፡ ፻፲፪ ፡ ፱ ።)

መጽሐፍ ፡ ዘረወ ፡ ወወሀበ ፡ ለነዳይ ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረ ፡ ታተርፍዎ ፡ ለኵሉ ፤ ወጽድቁኒ ፡ ይነብር ፡ ለዓለም ፡ ብሎ ፡ እንደተናገረ ፡ ይክል ፡ እግዚአብሔር ፡ አፈድፍዶ ፡ ለክሙ ፡ ኵሎ ፡ በረከቶ ። (ታሪክ) ፡ እንዳንድ ፡ ባለጸጋ ፡ ሽረሬ ፡ የሚባል ፡ ባለጸጋ ፡ ነበር ፡ ጽኑዩንና ፡ ግብዙን ፡ ለይቶ ፡ የሚያውቅ ፡ ሹሙን ፡ ጠርቶ ፡ በቀን ፡ በቀን ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ ወቄት ፡ ሳትሰጥ ፡ አትዋል ፡ አለው ። ቢሰጥ ፡ እየበዛ ፡ ሔደ ፡ ከበዛስ ፡ ብሎ ፡ ካዘዘው ፡ አትርፎ ፡ ኹለት ፡ ኹለት ፡ ወቄት ፡ ይሰጥ ፡ ጀመረ ። አንድ ፡ ቀንም ፡ ከቤት ፡ መዛግብት ፡ ቢገባ ፡ ገንዘቡ ፡ በዝቶ ፡ ተልከስክሶ ፡ አይቶ ፡ አንተ ፡ ያዘዝሁህን ፡ ትተኸዋል ፡ አለው ። እኔስ ፡ ካዘዝኸኝም ፡ አትርፌ ፡ ኹለት ፡ ኹለት ፡ ወቄት ፡ እሰጣለሁ ፡ አለው ። እንግዲህ ፡ አትገምግም ፡ እጅህ ፡ እንዳነሣ ፡ ስጥ ፡ ብሎታል ።

www.ethiopianorthodox.org

፲ ፡ ወውእቱ ፡ ይሁብ ፡ ዘርአ ፡ ለዘራዒ ፡
ለሚዘራ ፡ እሱ ፡ ዘሩን ፡ ይሰጠዋል ።
ወእክለ ፡ ለሲሳይ ።
ለምግቡም ፡ ትርፉን ፡ ይሰጠዋል ፡ (ሐተታ) ፡ ማድጋ ፡ ዘርዑ ፡ ዐሥር ፡ ማድጋ ፡ ያገባል ፡ ማድጋው ፡
ዘሩ ፤ ዘጠኙ ፤ ትርፉ ፤ ምግቡ ። ሚን ፡ ዘርቶ ፡ ዐሥር ፡ ሚን ፡ ያገባል ። ሚኑ ፡ ዘሩ ፤ ዘጠኙ ፡ ትርፉ ፡
ምግቡ ። እንደዘሩ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ቢፀረብን ፡ የሚገኘው ፡ ክብር ፡ እንደትርፉ ፡ በመንግሥት ፡ ሰማያት ፡
የሚገኘው ፡ ክብር ።
ወያሠምር ፡ ማዕረረ ፡ ጽድቅክሙ ፡ (ኢሳ ፡ ፶፭ ፡ ፲ ፡ ሆሴ ፡ ፲ ፡ ፲፪ ።)
የምጽዋታችሁንም ፡ ዋጋ ፡ ያበዛላችኋል ።

፲፩ ፡ ከመ ፡ ትብፅሉ ፡ በኵሉ ፡ ትፍሥሕት ፡ እንተ ፡ ትገብር ፡ ለክሙ ፡ አኰቴተ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ም ፡ ፰ ፡ ፲፭ ፡
፩ ፡ ፲፫ ።)
ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ ስለሰጣችሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መመስገንን ፡ በምታመጣላችሁ ፡ በፍጹም ፡
ደስታ ፡ ትከብሩ ፡ ዘንድ ። አንድም ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ ስለሰጣችሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መመስገንን ፡
የሚያመጣላችሁን ፡ የምጽዋታችሁን ፡ ዋጋ ፡ ያበዛላችኋል ።

፲፪ ፡ እስመ ፡ ዛቲ ፡ መልእክት ፡ ዘንቱ ፡ ግብር ፡ አኮ ፡ ለዝንቱ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘታመልኡ ።
በዚች ፡ አስተዋፅኦ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማገልገል ፡ ግዳጅ ፡ መፈጸሙ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ብቻ ፡ አይደ
ለምና ።
እስመ ፡ ትፌጽም ፡ ሎሙ ፡ ተጽናሶሙ ፡ ለቅዱሳን ።
በወዲሁ ፡ የቅዱሳን ፡ የንዳያንን ፡ ግዳጅ ፡ የምትፈጽምላቸው ፡ ስለሆነ ፡
ዓዲ ፡ ታፈደፍድ ፡ አኰቴተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በለሰብ ፡ ቅዱሳን ፡ (ም ፡ ፰ ፡ ፲፪ ።)
በወዲያውም ፡ በቅዱሳን ፡ በምእመናን ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መመስገንን ፡ አብዝታ ፡ ታመ
ጣለች ፡ እንጂ ።

፲፫ ፡ ወየአኵትዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በመክፈሪ ፡ ለዛቲ ፡ ሃይማኖትክሙ ።
የማይማኖታችሁ ፡ ፈተና ፡ በምትኾን ፡ በዚች ፡ አስተዋፅኦ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግኑታል ።
እስመ ፡ ተእዘዝክሙ ፡ ለመልእክተ ፡ ክርስቶስ ፡ ወኀበርክሙ ፡ ተፈሚሐክሙ ፡ ወአስተዋፃእክሙ ፡ ኵልክሙ ።
ክርስቶስን ፡ ለማገልገል ፡ እሺ ፡ በጂ ፡ ብላችኋልና ፡ አንድ ፡ ኾናችሁ ፡ ደስ ፡ ብሏችሁ ፡ አስተዋፅኦውን ፡
አውጥታችኋልና ።

፲፬ ፡ ወእሙንቱኒ ፡ ይጼልዩ ፡ በእንቲአክሙ ።
እነሱም ፡ ስለዋት ፡ ይጸልዩላችኋል ።
ወይፈትዉ ፡ ይርአዩክሙ ፡ በእንተ ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘለዐልክሙ ።
ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ ስለምትሰጥ ፡ አስተዋፅኦ ፡ ሊያዩዋችሁ ፡ ይወዳሉ ።

፲፭ ፡ አኰቴት ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ጸጋሁ ፡ እንተ ፡ ኢትትረጎም ።
ስለማትመረመር ።
ወትመጽእ ፡ አመ ፡ ኢትትዐወቅ ።
ባላወቋት ፡ ዕለት ፡ ባልጠረጠሩዋት ፡ ሰዓት ፡ ስለምትሰጥ ፡ አስተዋፅኦ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመ
ስገን ፡ (ሐተታ) ፡ ምነው ፡ የዐርፍ ፡ ነምር ፡ ምጽአቱ ፡ ጠሊ ፡ ወተዛዋ ፡ ምጽአ ፡ በግዕ ፡ ይል ፡ የለም ፡ (ኢዮ
ም ፡ ፲፩ ፡ ቍ ፡ ፯ ።) ቢሉ ፡ ጊዜው ፡ ተለይቶ ፡ ስላልታወቀ ።
እንድም ፡ ስለማትመረመር ፡ ባላወቋት ፡ ዕለት ፡ ባልጠረጠሩዋት ፡ ሰዓት ፡ ስለምትሰጥ ፡ መንግሥተ ፡
ሰማይ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ፡ (ሐተታ ፡) ምነው ፡ ዘመኑ ፡ ዘመኑ ፡ ዮሐንስ ፡ ወርኁ ፡ ወርኀ ፡
መጋቢት ፡ ዕለቱ ፡ ዕለተ ፡ እሑድ ፡ ጊዜው ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ እንደኾነ ፡ ታውቆ ፡ የለምን ፡ ቢሉ ፡ ብዙ ፡
ዘመነ ፡ ዮሐንስ ፡ ብዙ ፡ ወርኀ ፡ መጋቢት ፡ ብዙ ፡ ዕለተ ፡ እሑድ ፡ ብዙ ፡ መንፈቀ ፡ ሌሊት ፡ አለና ፡
ተለይቶ ፡ ስላልታወቀ ።

ም ዕ ራ ፍ ፲ ።

ክ ፍ ል ፡ ፬ ።

፩ ፡ እስተበቍዐክሙ ፡ አነ ፡ ጳውሎስ ፡ በየውሀት ፡ ወበምሕረቱ ፡ ለክርስቶስ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፪ ፡ ፫ ።)
ወንድሞቻችን ፡ እኔ ፡ ጳውሎስ ፡ ብርሃናትን ፡ ማመላለሱን ፡ ማያትን ፡ ማፍሰሱን ፡ ማዓልትና ፡ ሌሊ

www.ethiopianorthodox.org

ትን ፡ በጋና ፡ ከሪምትን ፡ ግፈራረቁን ፡ ነፋሳትን ፡ ማንፈሱን ፡ እማለጅ ፡ አድርጌ ፡ እግልዳችኋለሁ ፡ ይፀል ፡ ያልያዘው ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ብፁዓን ፡ መሐርያን ፡ ብፁዓን ፡ የዋሃን ፡ ያለውን ፡ አማላጅ ፡ አድርጌ ፡ እግልዳችኋለሁ ። እንድም ፡ የክርስቶስን ፡ ምሕረት ፡ የዋሃት ፡ ማላጅ ፡ አድርጌ ፡ እግልዳችኋለሁ ። እንድም ፡ በክርስቶስ ፡ ምሕረት ፡ የዋሃት ፡ አንቼ ፡ ጽኑ ፡ ብዬ ፡ እግልዳችኋለሁ ።

እስመ ፡ ሶበ ፡ እሄሉ ፡ ኀቢክሙ ፡ መጠነ ፡ አነ ፡ በገጽ ።

ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ ሳለሁ ፡ ቃል ፡ ለቃል ፡ ነግሬያችሁ ፡ ነበርና ።

፬ ፡ እስመ ፡ ንዋየ ፡ ሐቅሉ ፡ ለጸብዕነ ፡ ኢኮነ ፡ በሕገ ፡ ሥጋ ።

የሰልፋችን ፡ ጸብቱ ፡ በሥጋዊ ፡ ሥርዓት ፡ አይደለምና ፡ (እለ) ፡ ጦር ፡ በመወርወር ፡ ጋሻ ፡ በመመከት ፡ ፈረስ ፡ በመጋለብ ፡ ነፍጥ ፡ በመተኮስ ፡ አይደለምና ።

አላ ፡ በኀይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ዘይነሥት ፡ እጽዋናተ ፡ ጽኑዓን ። (ኤፌ ፡ ፮ ፡ ፲፫ ፡ ፲፯ ።)

ጽኑ ፡ ጽኑ ፡ አንባን ፡ በሚንድ ፡ (እለ) ፡ አጋንንትን ፡ ድል ፡ በሚነሣ ።

፭ ፡ ወያንሕል ፡ ኵሉ ፡ ዘይትዔበይ ፡ ወይትሌዐል ፡ ላዕለ ፡ እግዚአብሔር ።

በክርስቶስ ፡ ላይ ፡ የሚታበይን ፡ ኹሉ ፡ የሚያፈርስ ፡ (እለ) ፡ ክርስቶስን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወንጌልን ፡ ዲታላ ፡ ሕግ ፡ የሚል ፡ ቢጽ ፡ ሐሳዊን ፡ በማያጠፉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አበጋዝነት ፡ በተአምራቱ ፡ ሠራዊትነት ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፮ ፡ ከመ ፡ ይጼወው ፡ ኵሉ ፡ ልብ ።

ልብ ፡ ኹሉ ፡ ወደሱ ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ።

ወሕሊና ፡ ይግነይ ፡ ለእግዚአብሔር ።

ሕሊናም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ። እንድም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ያምን ፡ ዘንድ ።

፮ ፡ ወድልዋን ፡ ንሕነ ፡ ንትበቀሎ ፡ ለዘይገርር ፡ ወኢይሰምዕ ።

ለእግዚአብሔር ፡ በማይገዛ ፡ ወንጌልን ፡ በማይቀበል ፡ ሰው ፡ እንፈርድበት ፡ ዘንድ ፡ (ድልዋን) ፡ ተዘጋጅተናል ። እንድም ፡ ንትቀበሎ ፡ ይላል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የማይገዛ ፡ ወንጌልን ፡ የማይቀበልን ፡ ሰው ፡ በጠላትነት ፡ እንገጥመው ፡ ዘንድ ፡ (ድልዋን) ፡ ተዘጋጅተናል ።

ሶበ ፡ ፈጸምክሙ ፡ አንትሙ ፡ ትእዛዘ ፡ ዘመንገለ ፡ ገጽ ፡ ርእዩ ፡ ቅድሜክሙ ።

ከቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ ሕግ ፡ ከአሪት ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ የምትኾን ፡ ወንጌልን ፡ በፈጸማችሁ ፡ ጊዜ ፡ ወደፊት ፡ ገሥግሡ ፡ (እለ) ፡ የትሩፋት ፡ ሥራ ፡ ሥሩ ፡ ጨምሩበት ። እንድም ፡ በፈጸማችሁ ፡ ጊዜ ፡ ቀድሞ ፡ የነበራችሁባት ፡ ኦሪትን ፡ እሰቡ ፡ (እለ) ፡ ትጎዳችሁ ፡ እንደነበረ ፡ ዕወቁ ።

እንድም ፡ ከወንጌል ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ የምትኾን ፡ ኦሪትን ፡ ከፈጸማችሁ ፡ ቀድሞ ፡ ወደነበራችሁባት ፡ ወደ ፡ ወንጌል ፡ ተመለሱ ። ዘስሕተእ ፡ ኢይትመየጥ ፡ ወዘወድቀእ ፡ ኢይትነሣእ ፡ እንዲል ፡ የሳቱ ፡ አይመለሱምን ፡ የወደቀ ፡ አይነሣምን ። (ኤር ፡ ፰ ፡ ፬ ።)

እንድም ፡ ከኛ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ የሚኾን ፡ ቢጽ ፡ ሐሳዊን ፡ ሕግ ፡ ከፈጸማችሁ ፡ ቀድሞ ፡ ጽፌ ፡ በሰደድሁት ፡ ክታብ ፡ የተናገርሁትን ፡ ነገር ፡ አስተውሉ ።

እፎኑመ ፡ ትፈቅዱ ፡ እምጸእ ፡ ኀቤክሙ ፡ በበትርኑ ፡ ወሚመ ፡ በተፋቅሮ ፡ ወበየውሃት ፡ ልብ ፡ እንገሊገክሙ ፡ በስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መጥውዎ ፡ ለሰይጣን ፡ ብዬ ።

፯ ፡ ወዘሂ ፡ ተአመነ ፡ በክርስቶስ ፡ ከማሁ ፡ ለየሐሊ ፡ ሊሊሁ ።

በክርስቶስ ፡ ያመነ ፡ እሱ ፡ እንዲህ ፡ ያስብ ።

እስመ ፡ በከመ ፡ ክርስቶስ ፡ ከማሁ ፡ ንሕነኒ ።

እኛ ፡ እንደክርስቶስ ፡ እንደኾነ ።

፰ ፡ ወእመኒቦ ፡ ዘተመከሕኩ ።

የምመካውም ፡ ትምክሕት ፡ ቢኖር ።

ፈቂድየ ፡ በሢመትክሙ ፡ እንተ ፡ ወሀበኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ (ም ፡ ፲፪ ፡ ፮ ።)

እግዚአብሔር ፡ በሰጠኝ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ መሾምን ፡ ወድጄ ፡ ነው ። ለተሐንጾትክሙ ፡ ማንሻ ።

እንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰጠኝ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ መሾምን ፡ ወድጄ ፡ የምመካው ፡ ትምክሕት ፡ ቢኖር ።

ለተሐንጾትክሙ ፡ ወአኮ ፡ ለተነሥቶ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፭ ፡ ፪ ፡ ፲፭ ።)

ለማፍረስ ፡ ያይደለ ፡ እናንተን ፡ ለማነጽ ፡ ነው ፡ ኢይቸገሬር ፡ ማንሻ ። እንድም ፡ ለማፍረስ ፡ ያይደለ ፡ እናንተን ፡ ለማነጽ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰጠኝ ፡ በናንተ ፡ ላይ ፡ መሾምን ፡ ወድጄ ፡ የምመካው ፡ ትምክሕት ፡ ቢኖር ።

www.ethiopianorthodox.org

አይትኀፈር ።

ክዚል ፡ ኦላጣም ።

ወባሕቱ ፡ እምህከ ፡ ዘንተ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ ትምክሕቱን ፡ ሸልጌ ፡ እተወዋለሁ ።

፱ ፡ ከመ ፡ ኢይምስሎ ፡ ለዘይትሐዘብ ፡ ዘአጌርመክሙ ፡ በመጻሕፍትየ ።

ለሚጠራጠር ፡ ቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ ጽፌ ፡ በሰደድሁት ፡ ከታብ ፡ በምናገረው ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ የምገረምባችሁ ፡ እንዳይመስለው ።

፲ ፡ እስመቦ ፡ እምስብእ ፡ ዘይብል ።

ከ ሰው ፡ ወገን ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ አለና ።

እስመ፣ መጻሕፍቲሁሰ ፡ ክቡዳት ፡ ወዕጹባት ።

የጳውሎስ ፡ መጻሕፍትማ ፡ ጭንቅ ፡ ጭንቅ ፡ ናቸው ፡ እኮ ፡ የሚል ፡ አለና ፤ ላሰፈው ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ እፎኑመ ፡ ትፈቅዱ ፡ እምጸአ ፡ ኀቤክሙ ፡ በበትርኑ ፡ ወሚመ ፡ በተፋቅሮ ፡ ወበየውሃት ፡ ልብ ፡ አንገሊክሙ ፡ በስሙ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መጥውዎ ፡ ለሰይጣን ፡ ስል ፡ ሰምቶ ። ለሚመጣው ፡ ነው ፡ ቢሉ ፡ እልቦ ፡ ዘይትሀበል ፡ ላዕሌየ ፡ ዘእንበለ ፡ ዘእነ ፡ እትሀበል ፡ ላዕሌሁ ፡ ስል ፡ ሰምቶ ።

ወሀልዎቱሰ ፡ በሥጋ ፡ ድኩም ፡ ውእቱ ።

አነዋሩ ፡ ግን ፡ በሥጋ ፡ ደካማ ፡ ነው ፡ ልብሱ ፡ ጨርቅ ፡ ምርኩዙ ፡ ሸንበቆ ፡ ነው ።

ወነገሩሂ ፡ ኅጹር ፡ (ቍ ፡ ፭ ።)

ነገሩም ፡ ተርታ ፡ ነው ፡ (አለ) ፡ ታመመ ፡ ደከመ ፡ ጨርቅ ፡ ታጠቀ ፡ ገንድ ፡ ተሸከመ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ አለና ።

፲፩ ፡ ወባሕቱ ፡ ዘንተ ፡ ያእምር ፡ ዘይብል ፡ ዘንተ ፡ ነገረ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ይህን ፡ የሚል ፡ ይህን ፡ ይወቅ ።

ከመ ፡ በቃልነ ፡ በውስተ ፡ መጻሕፍት ፡ እመ ፡ ኢሀለውነ ፡ ከማሁ ፡ በምግባሪነኒ ፡ እመ ፡ ሀለውነ ፡ (ም ፡ ፲፫ ፡ ፱ ፡ ፲ ።)

ፀሐለንበት ፡ ጊዜ ፡ ጽፈን ፡ በሰደድነው ፡ ከታብ ፡ በምንናገረው ፡ ነገር ፡ ግሩማን ፡ እንደኾን ፡ በአለንበትም ፡ ጊዜ ፡ በምንሠራው ፡ ሥራ ፡ ግሩማን ፡ እንደኾን ፡ ይወቅ ።

፲፪ ፡ ወኢንትኀበል ፡ ናጥብዕ ፡ ነሐሲ ፡ ርእሰነ ፡ ለሲነ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ራሳችንን ፡ ልናመሰግን ፡ አንወድም ።

ከመ ፡ እለ ፡ ይንእዱ ፡ ርእሶሙ ።

ራሳቸውን ፡ እንደሚያመሰግኑ ፡ እንደ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ።

በዘእመክሩ ፡ ወዐዩኑ ፡ ለሊሆሙ ።

ራሳቸውን ፡ በመረመሩ ፡ በገመገሙ ፡ ገንዘብ ፡ ራሳቸውን ፡ እንደሚያመሰግኑ ። ዘዐዩኑ ፡ ያስቲዋህቡ ፡ እንዲል ፡ (ዶቂ ፡ ነፀ ። )

ወኢያእምሩ ፡ ፍካሬሁ ፡ ዘለሊሆሙ ፡ ይነብቡ ፡ (ም ፡ ፫ ፡ ፭ ፡ ፮ ፡ ፲፱ ።)

ራሳቸው ፡ የሚናገሩትን ፡ ንባቡ ፡ አሬት ፡ ትርጓሜው ፡ ወንጌል ፤ እንደሆነ ፡ እንደማያውቁ ። አንድም ፡ የሚናገሩትን ፡ በሥራ ፡ እንደማያውቁ ።

፲፫ ፡ ወንሕነሰ ፡ ኢንተሚካሕ ፡ ፈድፋደ ፡ እምዓቅምነ ።

እኛስ ፡ ከመጠናችን ፡ የወጣ ፡ ትምክሕት ፡ አንመካም ።

ዘእንበለ ፡ በመሥፈርት ፡ ወሕግ ፡ ዘእቀመ ፡ ለነ ፡ እግዚአብሔር ።

እግዚአብሔር ፡ በወሰነልን ፡ ልክ ፡ መጠን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ (እለ ፡ ) እግዚአብሔር ፡ ባደረገልን ፡ እንመካለን ፡ እንጂ ፡ እኛ ፡ ባደረግነው ፡ እንመካም ።

እስከ ፡ ንበጽሕ ፡ ኀቤክሙ ፡ (ሮሜ ፡ ፲፪ ፡ ፫ ።)

እናንተ ፡ እስከታውቁት ፡ ድረስ ፡ ደርሰን ።

፲፬ ፡ እስመ ፡ ዘንዌድስ ፡ ርእሰነ ፡ ከመ ፡ ዘኢበጻሕነ ፡ ኀቤክሙ ።

እናንተ ፡ እንደማታውቁን ፡ አድርገን ፡ ራሳችንን ፡ የምናመሰግን ፡ አይደለምና ።

ዳዕሙ ፡ በጻሕነ ፡ ውስተ ፡ ትምህርተ ፡ ክርስቶስ ።

የክርስቶስ ፡ ሕግ ፡ ወንጌልን ፡ በማስተማር ፡ በናንተ ፡ ዘንድ ፡ ታውቀናል ፡ እንጂ ፡

www.ethiopianorthodox.org

፲፭ ፡ ወንሕነሰ ፡ ኢንትሜካሕ ፡ በዘኢይበቍዐ ፡ በጻማ ፡ ነኪር ።
እኛስ ፡ ባላደረግነው ፡ ሌላ ፡ ባደረገው ፡ በማይረባ ፡ በማይጠቅም ፡ ነገር ፡ አንመካም ፤ ቢመካ ፡ ሐሳዊ ፡
ግን ፡ በፈጠን ፡ ቆሞ ፡ ነውና ፡ እሱ ፡ ባላደረገው ፡ ሙሴ ፡ ባደረገው ፡ በመና ፡ በደመና ፡ ይመካል ።
ወባሕቱ ፡ እሴር ፡ ትብዛኁ ፡ ሃይማኖትክሙ ፡ ወትዕበዩ ፡ በላዕሌክሙ ፡ በከመ ፡ ሥርዓትክሙ ፡፡ (ሮሜ ፡ ፲፭ ፡ ፳ ።)
(ሕግ ፡ ተሰፋክሙ ፡ ሲል ፡ ነው ፡) ሃይማኖታችሁ ፡ እንድትጸናላችሁ ፡ ተስፋችሁ ፡ እንድትረዳችሁ ፡
እናምናለንና ፡ በማይረባ ፡ በማይጠቅም ፡ ነገር ፡ እንመካለን ፡ አንጂ ።
ወፌድፋደ ፡ ንሜህረክሙ ።
ከአራት ፡ ወንጌል ፡ እንድትበልጥ ፡ እናስተምራችኋለን ፡ እንድም ፡ ከቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ ይልቅ ፡ በምትኩ ፡
ገንዘብ ፡ የምትመኩበትን ፡ ምክንያት ፡ እንነግራችኋለን ።

፲፮ ፡ ወእሜሃ ፡ የዐቢ ፡ ምስሌሁ ፡ እምማንን ።
ፈድፋደ ፡ ንሜህረክሙ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ የቢጽ ፡ ሐሳዊስ ፡ ነገር ፡ ይቆይና ፡ መጠናችን ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡
ይታወቃል ፡ (አለ ፡) በጸጋ ፡ መጣመራችን ። ትምህርት ፡ የዋሃን ፡ ይትአወቅ ፡ በገብ ፡ እለ ፡ የኃልፉ ፡
እንዲል ፡ (ብሎ ፡) እንድም ፡ በዘኢይበቍዐ ፡ በጻማ ፡ ነኪር ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ የቢጽ ፡ ሐሳዊስ ፡ ነገር ፡
ይቆይና ፡ መጠናችን ፡ ያንጊዜ ፡ ይታወቃል ፤ (አለ) ድመይ ፡ ፈውሬ ፡ ድመይ ፡ ፈውስ ፤ ምውት ፡ አንስቴ ፡
ሙት ፡ አንሳ ፤ ጋኔን ፡ አውጥቼ ፡ ጋኔን ፡ አውጣ ፡ ስለው ። እንድም ፡ ትዕቢት ፡ ሕገ ፡ ሥርዓትክሙ ፡ ብሎ ፡
ነበርና ፡ የቢጽ ፡ ሐሳዊስ ፡ ነገር ፡ ይቆይና ፡ መጠናችን ፡ ያንጊዜ ፡ ይታወቃል ፡ (አለ ፡) እስኩ ፡ እግዚእ ፡
ኅምስ ፡ መካልየ ፡ ወሀብኩኒ ፡ ወናሁ ፡ ኅምስ ፡ መካልይ ፡ ዲቤሆን ፡ ዘረባሕኩ ፡ ብለን ፡ ስናበረክታችሁ ።
ወንሕነሰ ፡ ኢንትሜካሕ ፡ በዘኢይደልዎ ፡ ወበዘኢይደሉ ።
እኛስ ፡ በማይገባ ፡ ነገር ፡ አንመካም ።

፲፯ ፡ ወዘሰ ፡ ይትሜካሕ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ለይትመካሕ ፡ (ኤር ፡ ፱ ፡ ፳፫ ፡ ፩ቆሮ ፡ ፩ ፡ ፴፩ ።)
ዘሰ ፡ ይትሜካሕ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ለይትመካሕ ፡ ብሎ ፡ እንመካለን ፡ እንጂ ፡ እንድም ፡ የሚመካ ፡
በእግዚአብሔር ፡ ይመካ ።

፲፰ ፡ ወአኮ ፡ ዘለሊሁ ፡ ዘርእሶ ፡ ንዕደ ፡ ኅሩየ ፡ ይከውን ።
ራሱን ፡ ብቻ ፡ ያከበረ ። እንድም ፡ ራሱን ፡ ያከበረ ፡ ብቻ ፡ ብቻ ፡ ራሱን ፡ ያከበረ ፡ ደግ ፡ የሚባል ፡
አይደለምና ።
አኮኑ ፡ ዘእግዚአብሔር ፡ ንዕዶ ፡ ከመ ።
እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ያከበረው ፡ እንድም ፡ እግዚአብሔር ፡ ያከበረው ፡ ብቻ ፡ ደግ ፡ ይባላል ፡ እንጂ ።

## ምዕራፍ ፲፩ ።

፩ ፡ ወርቱዕሰ ፡ ትትዐገሠኒ ፡ ኅዳጠ ፡ ከመ ፡ እንብብ ፡ ከዕበድየ ፡ አንሰ ፡ ትትዔገሡኒ ።
አገባብስ ፡ ዝም ፡ ብላችሁኝ ፡ በስንፍናዬ ፡ ጥቂት ፡ እመካ ፡ ዘንድ ፡ ልትታገሡኝ ፡ ይገባል ፤ ታገሡኝ
ሁኝ ፡ በስንፍናዬ ፡ ጥቂት ፡ እመካ ፡ ዘንድ ፡ ዝም ፡ ልትሉኝ ፡ ይገባል ።
(ሐተታ) ፡ መመካት ፡ ይገባል ፡ ብለው ፡ ሥርዓት ፡ አድርገው ፡ እንዳይዙብኝ ፡ በዕበድየ ፡ አለ ።

፪ ፡ እስመ ፡ እቀንዕ ፡ ለክሙ ፡ ቅንዓተ ፡ እግዚአብሔር ።
መንፈሳዊ ፡ ቅንዓት ፡ እቀናላችኋለሁና ።
እስመ ፡ ፈኀርኩክሙ ፡ ለአሐዱ ፡ ምት ፡ ድንግል ፡ ወንጹሕ ፡ ክርስቶስ ። (ኤፌ ፡ ፭ ፡ ፳፯ ፡ ፳፯ ።)
ድንግል ፡ ንጹሕ ፡ ለሚኾን ፡ ላንድ ፡ ለሰማያዊ ፡ መርዓዊ ፡ ለክርስቶስ ፡ ስላጨኋችሁ ፡ (ሐተታ ፡)
(ድንግል ፡) ከተፈልጦ ፤ (ንጹሕ ፡) ከተድኅሮ ። እንድም ፡ (ድንግል ፡) ከተፈልጦ ፡ ከተድኅሮ ፡ (ንጹሕ ፡)
ካለመመለክ ፡ ካለመስገድ ፡ ነው ። ከመ ፡ እቅርብክሙ ፡ ኀቤሁ ።
ከሱ ፡ ጋራ ፡ አዋሕዳችሁ ፡ ዘንድ ፡ ስለአጨኋችሁ ።

፫ ፡ ወባሕቱ ፡ እፈርህ ፡ የጊ ፡ ከመ ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ አስሐታ ፡ ለሔዋን ፡ በጕሕሉት ፡ እንዳዒ ፡ ለእመ ፡ ይማ
ስን ፡ ልብክሙ ፡ እምየውሀቱ ፡ ወንጽሑ ፡ ለክርስቶስ ፡ (ዘፍጥ ፡ ፫ ፡ ፬ ፡ ፲፫ ።)
ነገር ፡ ግን ፡ በጕሕሉት ፡ ሔዋንን ፤ እንዳሳተ ፡ እንደ ፡ አርዌ ፡ ምድር ። እንድም ፡ አርዌ ፡ ምድር ፡ እን
ዳሳታት ፡ እንደ ፡ ሔዋን ፤ ልቡናችሁ ፡ ከክርስቶስ ፡ ከንጹሕ ፤ ከየውሀቱ ፡ ወጥቶ ፡ በኃጢአት ፡ ይለወጥን ፡
እንጃ ፡ ብዬ ፡ እፈራለሁ ።

www.ethiopianorthodox.org

፱ ፡ ሶበሰ ፡ ኮነ ፡ ዘይመጽእ ፡ ኀቤክሙ ።
　　በመምህርነት ፡ ወደናንት ፡ የመጣ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ።
ጸውዐክሙ ፡ ኀበ ፡ ካልእ ፡ ኢየሱስ ፡ ዘኢሰበክነ ፡ ለክሙ ።
　　እኛ ፡ ያላስተማርናችሁ ፡ ሌላ ፡ ኢየሱስም ፡ ኑሮ ፡ ወደዚያ ፡ የጠራችሁ ፡ ቢኾን ።
ወእመቦ ፡ ካልእ ፡ መንፈስ ፡ ዘትነሥኡ ፡ ዘኢነሣእክሙ ።
　　ከኛ ፡ ያልተቀበላችሁት ፡ ልጅነት ፡ ኑሮ ፡ ወደዚያ ፡ የጠራችሁ ፡ ቢኾን ። ወእመኒ ፡ ካልእ ፡ ትምህርት ፡ ዘኢተመህርክሙ ።
　　ከኛ ፡ ያልተማራችሁት ፡ ትምህርት ፡ ኑሮ ፡ ወደዚያ ፡ የጠራችሁ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ።
ርቱዕ ፡ ትጽንሑ ፡ ሎቱ ። (ገላትያ ፡ ፩ ፡ ፱ ።)
　　ያው ፡ ቅሉ ፡ ቢኾን ፡ መምህሮቻችን ፡ ይምጡ ፡ ብላችሁ ፡ ልትጠብቁን ፡ ይገባል ፤ ይገባ ፡ ነበር ።

፲ ፡ ወባሕቱ ፡ እትሐዘብ ፡ አልቦ ፡ ዘአሕጸጽኩክሙ ፡ እምዘ ፡ ባዕዳን ፡ ሐዋርያት ። (ም፡ ፲፪ ፡ ፲፩፡፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ፡ ፲ ። (ገላትያ ፡ ፪ ፡ ፯ ፡ ፱ ።)
　　ነገር ፡ ግን ፡ ሌሎች ፡ ሐዋርያት ፡ ካስተማሩት ፡ ትምህርት ፡ ከሠሩት ፡ ትሩፋት ፡ ካደረጉት ፡ ተአምራት ፡ ያስቀረሁባችሁ ፡ እንደሌለ ፡ አውቃለሁ ።
　　እንዘ ፡ ለባዕዳን ፡ ሐዋርያት ። ሐዋርያት ፡ ለሌሎች ፡ ካስተማሩት ።
　　ሐዋርያት ፡ ለሌሎች ፡ ካስተማሩት ፡ ትምህርት ፡ ካደረጉት ፡ ተአምራት ፡ ከሠሩት ፡ ትሩፋት ፡ ያስቀረሁባችሁ ፡ እንደሌለ ፡ አውቃለሁ ።

፲፩ ፡ ወእመኒ ፡ ዐብድ ፡ አነ ፡ በቃልየ ፡ አኮኬ ፡ በልብየ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፪ ፡ ፩ ፡ ፪ ፡ ፲፫ ።)
　　በቃሌ ፡ ሰነፍ ፡ ብኾን ፡ በልቤ ፡ አይደለም ፡ (አለ ፡) በመመካቱም ፡ እንደ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ ብኾን ፡ ይገባል ፡ ብዬ ፡ አይደለም ።
ወባሕቱ ፡ እከሥት ፡ ለክሙ ፡ ዙሉ ፡ ውስተ ፡ ዙሉ ። (ኤፌ ፡ ፫ ፡ ፩ ።)
　　ኹሉን ፡ በኹሉ ፡ እገልጥላችኋለሁ ፡ እንጂ ፤ እከሥት ፡ ለክሙ ፡ እገልጥላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፲፪ ፡ ወሚመ ፡ አበስኩኑ ፡ እንጋ ፡ ዘአሕመምኩ ፡ ርእስየ ፡ በዙሉ ፡ ከመ ፡ አንትሙ ፡ ትትለዓሉ ።
　　ወይስ ፡ እናንት ፡ ልዕልና ፡ ነፍስን ፡ ታገኙ ፡ ዘንድ ፡ በውስጥ ፡ በአፍአ ፡ መከራ ፡ የተቀበልሁ ፡ በደልሁን ።
እስመ ፡ በከንቱ ፡ መሀርኩክሙ ፡ ትምህርተ ፡ እግዚአብሔር ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፲፪ ፡ ፲፰ ።)
　　የክርስቶስ ፡ ትምህርት ፡ ወንጌልን ፡ በከንቱ ፡ አስተምሬያችኋለሁና ፡ (አለ ፡) በጸጋ ፡ ዘነሣእክሙ ፡ በጸጋ ፡ ሀቡ ፡ በከንቱ ፡ ዘነሣእክሙ ፡ በከንቱ ፡ ሀቡ ፡ ባለው ፡ ዋጋ ፡ ባለመብላት ።

፲፫ ፡ ወባዕደሰ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቀማኩ ፡ ወነሣእኩ ፡ ለሲሳይየ ።
　　　ከሌሎቹ ፡ ምእመናን ፡ ግን ፡ የዕለት ፡ እራት ፡ ያህል ፡ ነሣሁ ።
ከመ ፡ እትለአክሙ ። (ፊል ፡ ፬ ፡ ፲፩ ።)
　　　　እናንተን ፡ አስተምር ፡ ዘንድ ።

፲፬ ፡ ወእመሂ ፡ ሀለውኩ ፡ ኀቤክሙ ፡ ኢተሰቁቁ ፡ ንዋየክሙ ።
　　ከናንተም ፡ ዘንድ ፡ በነበርሁ ፡ ጊዜ ፡ ለከብታችሁ ፡ አልሳሳሁም ።
እንዘሂ ፡ እጼነስ ።
　　ባይቸግርህ ፡ እንጂ ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ ሲቸግረኝ ።
ወኀበሂ ፡ ኢያእከልኩ ፡ ሰለጡ ፡ ሊተ ፡ አኀዊነ ፡ በጺሆሙ ፡ እመቄዶንያ ።
　　ባላበቃም ፡ ከመቄዶንያ ፡ መጥተው ፡ ወንድሞቻችን ፡ ግዳጄን ፡ ፈጸሙልኝ ።
ወበዙሉ ፡ ተዐቀብኩ ፡ ከመ ፡ ኢያከብድ ፡ ላዕሌክሙ ። (ም ፡ ፲፪ ፡ ፲፫ ።)
　　እናንተን ፡ እንዳላስቸግር ፡ በውስጥ ፡ በአፍአ ፡ ዋጋ ፡ ከመብላት ፡ ተከለከልሁ ።
　　አንድም ፡ በናንት ፡ ሥርዓት ፡ እንዳላጸና ።
ወእትዐቀብሂ ።
　　ከዚህን ፡ ቀደም ፡ ብቻ ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ እንግዲህም ፡ እከለከላለሁ ።
፲፭ ፡ እስመ ፡ ጽድቁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ይሄሉ ፡ ምስሌየ ።
　　የክርስቶስ ፡ ትእዛዝ ፡ በኔ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራልና ፡ (አለ) ፡ በጸጋ ፡ ዘነሣእክሙ ፡ በጸጋ ፡ ሀቡ ፡ በከንቱ ፡ ዘነሣእክሙ ፡ በከንቱ ፡ ሀቡ ፡ ያለው ፡ በኔ ፡ ጸንቶ ፡ ይኖራልና ።

ወኢተዐጽወተኒ ፡ ዛቲ ፡ ፍሥሓየ ፡ በደወለ ፡ አካይያ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፲፭ ። )
　　በአካይያ ፡ አውራጃም ፡ ሳለሁ ፡ አስተምሮ ፡ ዋጋ ፡ አለመቀበል ፡ አልተከለከለችብኝም ።

www.ethiopianorthodox.org

በእንተ ፡ ምንት ።
ስለምን ፡ ነው ።

፲፩ ፡ እስመሁ ፡ እንጋ ፡ ኢያፈቅረክሙኑ ።
እልወዳችሁምናት ፤ እልወዳችሁምና ፡ ነውን ።
እንከሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያአምር ፡ ዘንተ ።
እንኪያስ ፡ እንድወዳችሁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ።

፲፪ ፡ ወባሕቱ ፡ ዘኒ ፡ ገበርኩ ።
ነገር ፡ ግን ፡ ከዚሀ ፡ ቀደም ፡ ዋጋ ፡ አለመብላቴ ።
ወዘኒ ፡ እገብር ።
እንግዲህም ፡ ወዲህ ፡ ዋጋ ፡ አልበላም ፡ ማለቴ ።
ከመ ፡ እክልአሙ ፡ ምክንያተ ፡ ለእለ ፡ ይፈቅዱ ፡ ምክንያተ ።
ምክንያት ፡ የሚሹ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያንን ፡ ምክንያት ፡ እሳጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ነው ።
ከመ ፡ ኢይርከቡ ፡ እሙንቱሂ ፡ በዘይትሜከሑ ፡ ከማነ ፡ (፩ ፡ ቆር ፡ ፱ ፡ ፲፪ ።)
እነሱም ፡ እንደኛ ፡ በሚመኩ ፡ ገንዘብ ፡ የሚመኩበት ፡ ምክንያት ፡ እንዳያገኙ ።

፲፫ ፡ እስመ ፡ ሀለዉ ፡ ሐሳውያን ፡ ገበርተ ፡ ዐመፃ ፡ እለ ፡ ይትሜየኑ ።
የሚተነኰሉ ፡ ዓመፅን ፡ የሚሠሩ ፡ ሐሰተኞች ፡ አሉና ፡ (አለ ፡ ) አስተምረናል ፡ ብለው ፡ ዋጋ ፡ የሚቀበሉ ፡ ቢጽ ሐሳውያን ፡ አሉና ።
ወይትሜሰሉ ፡ ሐዋርያተ ፡ ክርስቶስ ፡ (ም ፡ ፪ ፡ ፲፯ ፡ ፊልጵ ፡ ፫ ፡ ፪ ።)
ክርስቶስ ፡ የሾማቸው ፡ ሐዋርያትን ፡ እንመስላለን ፡ የሚሉ ። እንድም ፡ ክርስቶስ ፡ የሾመን ፡ ሐዋርያት ፡ ነን ፡ የሚሉ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ አሉና ።

፲፬ ፡ ወዝኒ ፡ አኮ ፡ ለአንክሮ ።
ይህም ፡ ድንቅ ፡ አይደለም ።
እስመ ፡ ሰሊሁ ፡ ሰይጣን ፡ ይትሜሰል ፡ ከመ ፡ መልአከ ፡ ብርሃን ።
እሱ ፡ ቅሉ ፡ ሰይጣን ፤ መልአከ ፡ ብርሃን ፡ ክርስቶስን ፡ እመስላለሁ ፡ ብሏልና ።

፲፭ ፡ ወዝኒ ፡ ኢኮነ ፡ ዐቢይ ።
ይህም ፡ ድንቅ ፡ አይደለም ።
ለእመ ፡ ይትሜሰሉ ፡ መላእክቲሁኒ ፡ ከመ ፡ መላእክተ ፡ ጽድቅ ።
አለቃው ፤ አለቃውን ፡ እመስላለሁ ፡ ቢል ፡ ሠራዊቱም ፤ ሠራዊቱን ፡ እንመስላለን ፡ ቢሉ ።
ወደኃሪቶሙሰ ፡ በከመ ፡ ምግባሮሙ ።
ፍጻሜያቸው ፡ ግን ፡ እንደሥራቸው ፡ ነው ፡ (አለ) ፡ በሥራቸው ፡ ይጠፋሉ ፡

፲፮ ፡ ወካዕበ ፡ እብል ፡ አልቦ ፡ ዘይሬስየኒ ፡ ከመ ፡ ዐብድ ።
ዳግመኛም ፡ እንደ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ የሚያደርገኝ ፡ ሰው ፡ አይኑር ፡ እላለሁ ፡
ወእመ ፡ አኮሰ ፡ ከመ ፡ ዐብድኒ ፡ ተወከፉኒ ፡ ቃልየ ።
እንደ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳዊም ፡ ካልሆነሁ ፡ ተቀበሉኝ ።
ከመ ፡ እትመካሕ ፡ እነሂ ፡ ኅዳጠ ፡ (ም ፡ ፲፪ ፡ ፮ ።)
እኔም ፡ ጥቂት ፡ እመካ ፡ ዘንድ ።

፲፯ ፡ ወዝኒ ፡ አኮ ፡ ዘመንገለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘእነግር ።
ይህም ፡ የምመካው ፡ ትምክሕት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተገኘ ፡ አይደለም ፡ (አለ ፡ ) ይገባል ፡ ብዬ ፡ አይደለም ።
ዳዕሙ ፡ ከመ ፡ ዐብድ ፡ እዘነግዕ ፡ በእንተ ፡ ዛቲ ፡ ትምክሕትየ ።
እንደ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ ባሉ ፡ እግብርት ፡ ጽኑዓን ፡ ንሕነ ፡ ያለውን ፡ ዘንግቼ ፡ በመዘንጋት ፡ እመካለሁ ፡ እንጂ ፡ (አልቦ ፡ ዘይሬስየኒ ፡ ከመ ፡ ዐብድ ፡ በእንተ ፡ ዛቲ ፡ ትምክሕትየ ። ) በዚች ፡ በመመካቴ ፡ እንደ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ የሚያደርገኝ ፡ ሰው ፡ አይኑር ፡ እላለሁ ።

፲፰ ፡ እስመ ፡ ብዙኃን ፡ እለ ፡ ይትሜከሑ ፡ በሕግ ፡ ዘሥጋ ።
በሥጋዊ ፡ ሥርዓት ፡ የሚመኩ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ፡ (አለ ፡ ) በጾመና ፡ በደመና ፡ እነሱ ፡ ባላደረጉት ፡ ሙሴ ፡ ባደረገው ።

www.ethiopianorthodox.org

[illegible]
[illegible]

፲፱ ፡ [illegible] ፡ [illegible] ፡ አጽምእትሙ ፡ ለዐብዳን ፡ እንዘ ፡ ነባብያን ፡ አንትሙ ፡
(ነባብያን ፡ ) እግዚአብሔር ፡ አባታችን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማይ ፡ ርስታችን ፡ ብላችሁ ፡ የምትመኩ ፡
ስትኾኑ ፤
አንድም ፡ ጠቢባን ፡ ይላል ፤ በአካል ፡ ምስት ፡ በባሕርይ ፡ በህልውና ፡ አንድ ፡ ብላችሁ ፡ የምታምኑ ፡
ስትኾኑ ። የቢጽ ፡ ሐሳውያንስ ፡ ነገር ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛችሁ ፡ ከኾነ ፡ እኔም ፡ እመካለሁ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡
እሱ ፡ እያጸናው ፡ በተቀበለው ፡ መከራ ፡ ሲመካ ፡ አምልቶ ፡ አስፍቶ ፡ ይጽፋል ።

፳ ፡ እስመ ፡ ትትዔገሥዎሙ ፡ ለእለ ፡ ይትዔገሉክሙ ።
ከብታችሁን ፡ የሚቀሟችሁ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያንን ።
ወለእለሂ ፡ የሀይዱክሙ ።
ከብታችሁን ፡ የሚቀሟችሁን ፡ (በምክንያት ፡ እንበለ ፡ ምክንያት ፡ ሲል ፡ ይደጋግማል ። )
ወለእለሂ ፡ ይትቤልፁክሙ ።
መበያ ፡ የሚያደርጓችሁን ።
ወለእለሂ ፡ ይትዔበዩ ፡ ላዕሌክሙ ።
የሚታበዩባችሁን ፡ ዝም ፡ ብላችኋቸዋልና ።
ወለዘሂ ፡ ይጸፍዐክሙ ፡ ገጸክሙ ።
ፃጸ ፡ ልቡናችሁን ፡ እየጸፉ ፡ ወደ ፡ አሪት ፡ የሚመልሳችሁን ፡ ዝም ፡ ብላችሁታልና ።

፳፩ ፡ እብል ፡ ዘንተ ፡ ከመ ፡ ዘያስተሐቅር ።
ይህንም ፡ እንደሚንቅ ፡ እንደሚያቃልል ፡ ሰው ፡ እናገራለሁ ። አንድም ፡ እንደ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ እናገራለሁ ።
ከመ ፡ ሕሙማን ፡ ንሕነ ፡ ለከሙ ።
እኛ ፡ ሰናንት ፡ አንደ ፡ ጥቂ ፡ ነን ፤ እኛን ፡ አንደ ፡ ጥቂ ፡ ብዬ ።
እብል ፡ አነሂ ፡ በዕበድየ ፡ አልቦ ፡ ዘይትነበል ፡ ላዕሌየ ።
በስንፍናዬ ፡ የሚሠለጥንብኝ ፡ ሰው ፡ አይኑር ፡ እላለሁ ።
ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ ዘአነ ፡ አትነበል ፡ ላዕሌሁ ።
እኔ ፡ ብሠለጥንበት ፡ እንጂ ።

፳፪ ፡ እመኒ ፡ ዕብራውያን ፡ እሙንቱ ፡ አነሂ ፡ ከማሆሙ ።
እነዚያም ፡ ዐዳውያን ፡ ፈለግ ፡ ነን ፡ ቢሉ ፡ እኔም ፡ እንደነሱ ፡ ዐዳዊ ፡ ፈለግ ፡ ነኝ ።
ወእመሂ ፡ እስራኤላውያን ፡ እሙንቱ ፡ አነሂ ፡ ከማሆሙ ።
ሕዝበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነን ፡ ቢሉ ፡ እኔም ፡ እንደነሱ ፡ ሕዝበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነኝ ።
ወእመሂ ፡ ዘርዐ ፡ አብርሃም ፡ እሙንቱ ። (ፊልጵ ፡ ፫ ፡ ፭ ።)
የአብርሃም ፡ ልጆች ፡ ነን ፡ ቢሉ ፡
አነሂ ፡ ከማሆሙ ።
እኔም ፡ እንደነሱ ፡ የአብርሃም ፡ ልጅ ፡ ነኝ ።

፳፫ ፡ እመኒ ፡ ላእኩ ፡ ለክርስቶስ ፡ እሙንቱ ።
የክርስቶስ ፡ አገልጋዮች ፡ ነን ፡ ቢሉ ።
እኮሁ ፡ አዘነግዕ ፡ ለርእስየ ።
ግን ፡ ያውቅላቸዋል ፤ (አኮኑ ፡ ይላል ፡ ) እኔማ ፡ ስንቱና ፡ እዘነጋው ፡ የለምን ።
[illegible]ማኒ ፡ አፈድፈድኩ ።
[illegible] ፡ ጊዜ ፡ ደከምሁ ።
ወበተቀሥፎኒ ፡ አፈድፈድኩ ።
ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተገረፍሁ ።
ወበተሞቅሖኒ ፡ አብዛኅኩ ።
ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ታሰርሁ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወለሞትኒ ፡ ብዙኀ ፡ ተደለውኩ ። (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፲፭ ።)
ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ለሞት ፡ የሚያበቃ ፡ መከራ ፡ ተቀበልሁ ።

፳፬ ፡ ኀምሰ ፡ ቀሠፉኒ ፡ አይሁድ ፡በበአርብዓ ፡ ዘእንበለ ፡ አሐቲ ። (ዘዳግ ፡ ፳፭ ፡ ፫ ።)
አንዲት ፡ ስትቀር ፡ አርባ ፡ አርባ ፤ አምስት ፡ ጊዜ ፡ ገረፉኝ ፤ ካርባ ፡ ወጥቶ ፡ የገረፈ ፡ እንደኾነ ፡ ሕግ ፤ አኀሠርኮ ፡ ትላለችና ፡ አሪት ፤ አንድም ፡ አንድ ፡ ሳትቀር ፡ ፭ ፡ ጊዜ ፡ አርብዓ ፡ አርብዓ ፡ ገረፉኝ ።

፳፭ ፡ ሥልሰ ፡ ዘበጡኒ ፡ በአብትር ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፯ ፡ ፳፪ ።)
መላልሰው ፡ በብትር ፡ ደበደቡኝ ፡ (አለ ፡ ) ሦስት ፡ ቀን ፡ እንደ ፡ ዳጉሳ ፡ ውለውበታል ።
ምዕረ ፡ ወገሩኒ ፡ በአእባን ። (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፲፬ ፡ ፲፱ ።)
አንድ ፡ ጊዜ ፡ በድንጊያ ፡ ወገሩኝ ፡ (አለ ፡ ) ቤት ፡ የሚያህል ፡ ደንጊያ ፡ ጭነውበታል ።
ሥልሰ ፡ ሰኰየት ፡ ሐመርየ ።
መርከቤ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ተንከራተተች ፡ ይኸውም ፡ በግብረ ፡ ሐዋርያት ፡ ታውቋል ።
ቤትኩ ፡ ወወፀልኩ ፡ እንዘ ፡ እጸብት ፡ ውስተ ፡ ዕመቀ ፡ ባሕር ።
ሦስት ፡ ቀን ፡ በጥልቅ ፡ ባሕር ፡ ሰዋኝ ፡ ውዬ ፡ ሰዋኝ ፡ አደርሁ ።
ይህንን፡ ሊቁ ፡ ሳዊሮስ ፡ በአካል ፡ ሦስት ፡ በባሕርይ ፡ በህልውና ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ብዬ ፡ አምኜ ፡ አም ስቱን ፡ አዕማደ ፡ ምሥጢር ፡ ተምሬ ፤ በአብነ ፡ ሃይማኖት ፡ ተወግሬ ፡ ጸሬ ፡ ኃጢአት፡ዘአመ፡ አይሁድና፡ (ይህድናም፡)ይላል ፡ በአይሁዳዊነት ፡ ሳለሁ ፡ የነበርሁበትን ፡ የፈፀናትን ፡ ትብትብ፡ በስመ፡አብ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ውስተ ፡ ነቅዐ ፡ ጥምቀት ፡ አስጠምኩ ፡ ብሎ ፡ ወስዶታል ።

፳፮ ፡ ወበመንገድሂ ፡ ዘልፈ ፡ እትመነደብ ።
በመንገድም ፡ ኹል ፡ ጊዜ ፡ መከራ ፡ እቀበል ፡ ነበር ።
በተከዚኒ ፡ አመንደቡኒ ፡ ፈያት ።
በፈሳሽ ፡ ውኃ ፡ ሽፍቶች ፡ መከራ ፡ አጸኑብኝ ፡ (እንደቆትላት ፡ ያሉ ፡ ናቸው ። )
አመንደቡኒ ፡ አዝማድየ ።
ዘመዶቼ ፡ እስራኤል ፡ መከራ ፡ አጸኑብኝ ።
አመንደቡኒ ፡ አሕዛብ ።
አሕዛብ ፡ መከራ ፡ አጸኑብኝ ።
ተመንደብኩ ፡ በሀገር ።
በከተማ ፡ መከራ ፡ ተቀበልሁ ።
ወተመንደብኩ ፡ በሐቅል ።
በበርሀ ፡ መከራ ፡ ተቀበልሁ ፡ (እንደጣጥራስ ፡ ያሉ ፡ ናቸው ። )
ተመንደብኩ ፡ በባሕር ።
በባሕር ፡ መከራ ፡ ተቀበልሁ ። ሻምቡቅ ፡ የምትባል ፡ ቀላል ፡ ፈጣን ፡ መርከብ ፡ አለች ፤ የባሕር ፡ ወን በዴ ፡ በዚያች ፡ ገሥግሶ ፡ ሔዶ ፡ አደጋ ፡ ይጥላልና ፡ (አንድም ፡ ) ማዕበል ፡ የሚመስል ፡ ልብስ ፡ አለ ፡ ያንን ፡ ለብሶ ፡ ሳይታወቅ ፡ ሳይ ፡ ሳዩን ፡ ሔዶ ፡ አደጋ ፡ ይጥላል ። (አንድም ፡ ) ውኃ ፡ የማያስገባ ፡ ብርሃን ፡ የማይከለክል ፡ ልብስ ፡ አለ ፡ ያንን ፡ ለብሶ ፡ ውስጥ ፡ ለውስጥ ፡ ሔዶ ፡ መርከቡን ፡ ይገለብጠዋል ።
አመንደቡኒ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳውያን ።
ቢጽ ፡ ሐሳውያን ፡ መከራ ፡ አጸኑብኝ ።

፳፯ ፡ በጻማ ። በቀዊም ።
ወበሥራኅ ። በስጊድ ።
ወበትጋሀ ፡ ብዙኀ ። በትጋሀ ፡ ሌሊት ።
በረኃብ ፡ ወበጽምዕ ። በረኃብ ፡ በጽምዕ ።
በጾም ፡ ብዙኅ ።
በብዙ ፡ ጾም ፡ (አለ ፡ ) ሲርብ ፡ መተው ፤ ውሎ ፡ መብላት ፤ ምግብ ፡ አለ ፡ ማሻሻል ፤ ጊዜያት ፡ አለመለዋወጥ ።
በቈር ። በብርድ ።
ወበዕርቃን ፡ (ም ፡ ፮ ፡ ፭ ። )
ዕራቁት ፡ በመኾን ፡ መከራ ፡ ተቀበልሁ ፡ (አለ) ፡ እንዘ ፡ እሑሊ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ብሎ ፡ እንዲያመ ጣው ፡ ጢት ፡ ጢት ፡ ምእመናንን ፡ ለማስተማር ፡ ሲሔድ ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፰ ፡ ዘእንበለ ፡ ብዙኅ ፡ ባዕድ ፡ ዘረከበኒ ፡ ኵሉ ፡ እሚረ ።

ቅሉ ፡ ጊዜ ፡ ከዚህ ፡ ሌላ ፡ ያገኘኝ ፡ መከራ ፡ ብዙ ፡ ነው ። እንዘ ፡ እሔሊ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። (ግብረ ሐዋ ፡ ፳ ፡ ፲፰ ፡ ፲፱ ።)

ምእመናንን ፡ ለማስተማር ፡ ስሔድ ።

፳፱ ፡ መኑ ፡ ዘኢይደዊ ።

(ዘኢይደዊ ፡) ኃጢአት ፡ የማይሠራ ፡ ማነው ።

ወኢየሐምም ፡ አነ ።

እኔ ፡ ግን ፡ አልሠራም ።

እስከዚህስ ፡ አይመከም ፡ ብሎ ፡ (ዘይደዊ ፡ ይላል ።) ኃጢአት ፡ ሠርቶ ፡ እኔ ፡ የማላዝንለት ፡ ማነው ።

ወመኑ ፡ ዘኢይስሕት ።

የማይስት ፡ ማነው ።

ወኢይደነግፅ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፱ ፡ ፳፪ ።)

እኔ ፡ ግን ፡ አልስትም ፡ እስከዚህስ ፡ አይመከም ፡ ብሎ ፡ (ዘይስሕት ፡) ስቶ ፡ እኔ ፡ የማላዝንለት ፡ ማነው ።

፴ ፡ ወእመሰ ፡ ይደሉ ፡ ተመክሖ ።

መመካት ፡ አይገባም ፡ እንጂ ፡ የሚገባስ ፡ ቢኾን ።

አነኒ ፡ እትሜካሕ ፡ በሕማምየ ፡ (ም ፡ ፲፪ ፡ ፱ ።)

እኔ ፡ ይልቅ ፡ በመከራዬ ፡ እመካለሁ ።

፴፩ ፡ የአምር ፡ እግዚአብሔር ፡ አቡሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የባሕርይ ፡ አባቱ ፡ እግዚአብሔር ። አብ ፡ ያውቃል ።

ዘውእቱ ፡ ቡሩክ ፡ ለዓለም ።

ይኸውም ፡ መከራ ፡ ቢቀበሉለት ፡ ክብር ፡ የማይጨመርለት ፡ መከራ ፡ ባይቀበሉለት ፡ ክብር ፡ የማይጐ ልበት ፡ ክቡር ፡ የባሕርይ ፡ አምላክ ፡ ነው ። ከመ ፡ ኢይሔሉ ፡ (ም ፡ ፩ ፡ ፳፭ ።)

(የአምር ፡ ከመ ፡ ኢይሔሉ ፡) ሐሰት ፡ እንዳልናገር ፡ ያውቃል ።

፴፪ ፡ በሀገረ ፡ ደማስቆ ።

ደማስቆ ፡ በሚባል ፡ ሀገር ።

መልአከ ፡ አሕዛብ ።

የአሕዛብ ፡ አለቃ ።

ዘውእቱ ፡ አርስጣስዮስ ።

ይኸውም ፡ አርስጣስዮስ ፡ ነው ።

ንጉሥ ፡ ንጉሥ ፡ የሚኾን ፡ (ንጉሥ ፡ አለው ።)

ንጉሥ ፡ ዘሤሞ ፡ ንጉሥ ፡ ውእቱ ፡ ይላልና ።

ዐቃቤ ፡ ሀገር ።

ሀገር ፡ አሳዳሪ ።

ደማስቆናዊ ፡ ፈቀደ ፡ የአኀዘኒ ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፱ ፡ ፳፬ ።)

የደማስቆ ፡ ሰው ፡ አርስጣስዮስ ፡ ሊይዘኝ ፡ ወደደ ።

፴፫ ፡ ወአውረዱኒ ፡ በሠብሣብ ፡ እንተ ፡ መስኮት ፡ እምዐረፍት ፡ (ግብ ፡ ሐዋ ፡ ፱ ፡ ፳፭ ።)

ወአምሠጥኩ ፡ እምእዴሁ ።

ከጁ ፡ አመለጥሁ ። ተይዞ ፡ አይደለም ፡ ወአምሠጠ ፡ ዳዊት ፡ እምውስተ ፡ ኢሎፍሊ ፡ እንዳለው ፡ ያለኀነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፪

፩ ፡ ወናሁ ፡ ይረትዕ ፡ ሊተ ፡ ተምክሖ ።

እነሆ ፡ መመካት ፡ ይቻለኝ ፡ ነበረ ።

ወባሕቱ ፡ ኢኮነ ፡ ሠናየ ።

ነገር ፡ ግን ፡ አይገባም ።

www.ethiopianorthodox.org

ንግባእ ፡ ካዕበ ።

ወናሁ ፡ ይረትዕ ፡ ሊተ ፡ ተመኪሖ ፡ ወባሕቱ ፡ ኢኮነ ፡ ሠናየ ፡ ብሎ ፡ ነበርና ፡ ንግባዕ ፡ ካዕበ ፡ አለ ፡
ዳግመኛ ፡ ወደትምክሕቱ ፡ እንመለስ ።

ወንዘከር ፡ ራእየ ፡ ዘከሠተ ፡ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር ፡ የገለጠልንን ፡ ራእይ ፡ እንናገር ።

፪ ፡ አእምር ፡ ብእሴ ፡ ምእመነ ፡ በክርስቶስ ፡ እምቅድመ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወአርባዕቱ ፡ ዓመት ።
ካሥራ ፡ አራት ፡ ዓመት ፡ አስቀድሞ ፡ በክርስቶስ ፡ ያመነውን ፡ ሰው ፡ አውቀዋለሁ ።

እመሂ ፡ በሥጋሁ
በሥጋውም ፡ እንደኾነ ።

ወእመሂ ፡ ዘእንበለ ፡ ሥጋሁ ።
በነፍሱም ፡ እንደኾነ ።

እንዳኢ ፡ የአምር ፡ እግዚአብሔር ።
እኔ ፡ አላውቅም ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ።

ወመሠጥዎ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ፡ እስከ ፡ ሣልስ ፡ ሰማይ ።
ያንን ፡ ሰው ፡ እስከ ፡ ሦስተኛው ፡ ሰማይ ፡ አወጡት ።

፫ ፡ ወአእምሮ ፡ ለውእቱ ፡ ብእሲ ።
ያንን ፡ ሰው ፡ አውቀዋለሁ ።

እመሂ ፡ በሥጋሁ ፡ ወእመሂ ፡ ዘእንበለ ፡ ሥጋሁ ።
በሥጋውም ፡ እንደኾነ ፡ በነፍሱም ፡ እንደኾነ ።

እንዳኢ ፡ እግዚአብሔር ፡ የአምር ፡ ( ም ፡ ፲፩ ፡ ፲፩ ።)
እኔ ፡ አላውቅም ፡ እግዚአብሔር ፡ ያውቃል ።

፬ ፡ ወመሠጥዎ ፡ ውስተ ፡ ገነት ።

ወደገነት ፡ አወጡት ፡ (ሐተታ ፡ ) ሣልስ ፡ ሰማይ ፡ ጠፈር ፤ ምጽንዓት ፤ ዓለመ ፡ መላእክት ፡ ገነት ፤ ተመልሶ ፡ ያረፈበት ፡ ነው ፡ ሲያወርዱት ፡ ከገነት ፡ አሳርፈውታል ፡ ምጽንዓትና ፡ ጠፈርስ ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሣልስ ፡ ሰማይ ፡ ዓለመ ፡ መላእክት ። ገነት ፡ ብርሃን ፡ ሲል ፡ ነው ፤ በዓለመ ፡ መላእክት ፡ ኾኖ ፡ ብርሃን ፡ አይቷል ፡ አበዊነሂ ፡ ይሰምይዎ ፡ ለብርሃን ፡ አእምሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ገነተ ፡ እንዲል ። (ዜና ፡ አበ ፡ ) አንድም ፡ ክንጽሐ ፡ ሥጋ ፡ ክንጽሐ ፡ ነፍስ ፡ ክንጽሐ ፡ ልቡና ፡ ደረስሁ ፡ ሲል ፡ ነው ። አንድም ፡ ግዙፋን ፤ ረቂቃን ፤ ፍጥረታትን ፡ አየሁ ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ግዙፋን ፡ ብሔሞት ፤ ሌዋታን ፤ አድማስ ፤ ናጌብ ፤ ረቂቃን ፡ ነፍሳት ፤ ነፋሳት ፤ መላእክት ። አንድም ፡ ሥላሴን ፡ አየሁ ፡ ሲል ፡ ነው ። (ሐተታ ፡ ) ከዚህ ፡ አምቅድመ ፡ ዐሠርቱ ፡ ወአርባዕቱ ፡ ዓመት ፡ አለ ፡ ሲል ፡ ቁር ። አፈ ፡ ወርቅ ፡ አምቅድመ ፡ ፳ ፡ ይላል ፡ እንደምነው ፡ ቢሉ ፡ ጌታ ፡ ባረገ ፡ በስምንት ፡ ዓመት ፡ አምኗል ። ባመነ ፤ በስድስት ፡ ዓመት ፡ ራእዩን ፡ አይቷል ፡ ራእዩን ፡ ባየ ፡ በዐሥራ አራት ፡ ዓመት ፡ ጽፏል ፡ ከዚህ ፡ ራእዩን ፡ ካየበት ፡ ይዞ ፡ ቈጥሮ ፡ ዐሥራ ፡ አራት ፡ አለ ፡ ሊቁ ፡ ካመነበት ፡ ይዞ ፡ ቈጥሮ ፤ አምቅድመ ፡ ፳ ፡ አለ ።

ወሰምዐ ፡ በህየ ፡ ነገረ ፡ ዘኢይትረጐም ፡ ዘኢይከውኖ ፡ ለዕጓለ ፡ እምሕያው ፡ ይንብብ ።

በዓለመ ፡ መላእክት ፡ ኾኖ ፡ የማይመረመር ፡ ነገር ፡ ሰማ ፡ (አለ ፡ ) ሰው ፡ ሊናገረው ፡ የማይቻለው ፤ ምነው ፡ እሱ ፡ ተናግሮት ፡ የለምን ፡ ቢሉ ፤ ራእዩን ፡ ለማስከበር ፤ አንድም ፡ ያልበቃ ፡ ሰው ፡ ሊናገረው ፡ የማይቻለው ፡ ሲል ፡ ነው ።

፭ ፡ በእንተ ፡ ዝንቱኬ ፡ በዘከመዝ ፡ እትሜካሕ ።
ስለዚህ ፡ እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ነገር ፡ እመካለሁ ፡ እንጂ ።

ዐሮእስየሰ ፡ ኢይትሜካሕ ።
በራሴ ፡ ግን ፡ አልመካም ።

ዘእንበለ ፡ በሕማምየ ፡ (ም ፡ ፲፩ ፡ ፴ ። )
በመከራዬ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፮ ፡ ወእመኒ ፡ ፈቀድኩ ፡ እትመካሕ ፡ ኢኮንኩ ፡ አብደ ።
ልመካም ፡ ብወድ ፡ ሐሰት ፡ አልናገርም ።

አስመ ፡ ጽድቀ ፡ እነግር ።
እውነት ፡ እናገራለሁ ፡ እንጂ ። አንድም ፡ እንደ ፡ ቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ አይደለሁም ፡ እውነት ፡ እናገራለሁና ።

www.ethiopianorthodox.org

ወባሕቱ ፡ እምሕክ ፡ ከመ ፡ ኢይትሐዘቡኒ ፡ በዘርአዩኒ ፡ ወበዘሰምዑኒ ፡ ፈድፋደ ፡ (ም ፡ ፲፰ ፡ ፲፭ ፡ ፲፯ ።)

ነገር ፡ ግን ፡ ያዩኝ ፡ የሰሙኝ ፡ ሰዎች ፡ ባዩኝ ፡ በሰሙኝ ፡ ገንዘብ ፡ እንዳይጠረጥሩኝ ፡ ይህን ፡ ሸልጌ ፡ እተ ወዋለሁ ።

፯ ፡ ወበእንተዝ ፡ ከመ ፡ ኢይትዐበይ ፡ በብዙኅ ፡ ራእይ ።

ብዙ ፡ ራእይ ፡ ስለተገለጠልኝስ ፡ እንዳልመካ ።

ተውህበኒ ፡ መልአከ ፡ ሰይጣን ፡ ዘይደጕፀኒ ፡ ሥጋየ ፡ ወይኰርዐኒ ፡ ርእስየ ። ( ኢዮ ፡ ፪ ፡ ፯ ። )

ጐኔን፡ የሚወጋ ፡ ቀጭን ፡ ስጥር ፡ ውጋት ፡ ራሴን ፡ የሚቀጠቅጠኝ ፡ አዳኔት፡ ፍልጠት ፡ ተሰጠኝ ። አን ድም ፡ ሥጋዬን ፡ በጤገን ፡ የሚያበስለኝ ፡ ራሴን ፡ በመዶሻ ፡ የሚቀጠቅጠኝ ፡ አለእስክንድሮስ ፡ ተነሣ ብኝ ። አንድም ፡ ምእመናንን ፡ ከዋሉበት ፡ አላሳድር ፡ካደሩበት ፡ አላውል ፡ እያለ ፡ ክርስቶስን ፡ ዕሩቅ ፡ ብእሲ ፡ ወንጌልን ፡ ዲቃላ ፡ ሕግ ፡ የሚል ፡ ቢጽ ፡ ሐሳዊ ፡ ተነሣብኝ ።

፰ ፡ ወአስቴብቋዕክዎ ፡ ለእግዚእየ ፡ ሠልሰ ፡ በእንቲአሁ ፡ ከመ ፡ ያዕትቶ ፡ እምኔየ ፡ ደዌውን ፡ ከኔ ፡ ያርቀው ፡ ዘንድ ፡ ስለዚህ ፡ ቀኖና ፡ ገብቼ ፡ ሦስት ፡ ጊዜ ፡ ጌታዬን ፡ ማለድሁት ።

፱ ፡ ወይቤለኒ ፡ የአክለከ ፡ ጸጋየ ።

ጸጋዬ ፡ ይበቃሃል ፡ አለኝ ።

ወኃይልሰ ፡ በደዌ ፡ የኀልቅ ።

ኃይለ ፡ ሥጋማ ፡ ምን ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ነው ፡ በደዌ ፡ እንጂ ፡ ያልቃል ፡ (አለ ፡ ) ይደክማል ፡ ሲል ፡ ነው ። አንድም ፡ ኃይለ ፡ ነፍስም ፡ እንጂ ፡ በደዌ ፡ ይፈጸማል ፡ (አለ ፡ ) ይበዛል ፡ ሲል ፡ ነው ፡ ወኃልቀ ፡ ክብሩ ፡ ለያዕቆብ ፡ እንዲል ፡ (ኢሳ ፡ ፲፯ ፡ ፬ ።)

ወሠመርኩ ፡ በሕማምየ ።

መከራ ፡ ልቀበል ፡ ወደድሁ ።

ከመ ፡ ይኅድር ፡ ኃይለ ፡ ክርስቶስ ፡ ላዕሌየ ።

የክርስቶስ ፡ ተአምራቱ ፡ ይደረግልኝ ፡ ዘንድ ።

፲ ፡ ወበእንተ ፡ ዝንቱ ፡ ሠመርኩ ፡ እትመካሕ ፡ በሕማምየ ።

ስለዚህ ፡ በመከራዬ ፡ ልመካ ፡ ወደድሁ ።

ወበተጽዕሎሂ ።

በመሰደብ ።

ወበምንዳቤሂ ።

በጸዋትወ ፡ መከራ ።

ወበተሰዶሂ ።

ሀገር ፡ ጥሎ ፡ በመሰደድ ።

ወበተጸናስሂ ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ።

ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ብሎ ፡ በመራብ ፡ በመጠማት ።

እስመ ፡ ሶበ ፡ እሐምም ፡ ሶቤሃ ፡ እጸንዕ ። (ፊልጵ ፡ ፩ ፡ ፲፫ ።)

አንዱን ፡ መከራ ፡ በተቀበልሁ ፡ ጊዜ ፡ አንዱን ፡ ለመቀበል ፡ እጸናለሁና ፡ እሱ ፡ እያጸናኝ ፡ በተቀበልሁት ፡ መከራ ፡ ልመካ ፡ ወደድሁ ።

፲፩ ፡ ወናሁ ፡ ኮንኩ ፡ አብደ ፡ በተመካሆትየ ፡ በዘአንትሙ ፡ አገበርክሙኒ ።

እናንት ፡ ባገበራችሁኝ ፡ ገንዘብ ፡ እናንት ፡ ስላገበራችሁኝ ፡ በመመካቴ ፡ አላዋቂ ፡ ኾንሁ ።

ወሊተሰ ፡ ርቱዕ ፡ እክበር ፡ በኀቤክሙ ።

እኔንስ ፡ እናንተ ፡ ልታከብሩኝ ፡ ልታመሰግኑኝ ።

ወትኩኑኒ ፡ ሰማዕትየ ።

ልትመሰክሩልኝም ፡ ይገባ ፡ ነበር ።

እስመ ፡ አልቦ ፡ ዘአሕጸጽኩክሙ ፡ እምዘ ፡ ዙሉ ፡ ሐዋርያት ።

መላው ፡ ሐዋርያት ፡ ካስተማሩት ፡ ትምህርት ፡ ከሠሩት ፡ ትሩፋት ፡ ካደረጉት ፡ ተአምራት ፡ ያስቀረሁባ ችሁ ፡ የለምና ። (አንድም ፡ እምዘ ፡ ለዙሉ ፡ ) ሐዋርያት ፡ ለሰው ፡ ኹሉ ፡ ካስተማሩት ፡ ትምህርት ፡ ከሠ ሩት ፡ ትሩፋት ፡ ካደረጉት ፡ ተአምራት ፡ ያስቀረሁባችሁ ፡ የለምና ።

www.ethiopianorthodox.org

ወእመኒ ፡ ከመ ፡ ወኢምንት ፡ አነ ።
እኔም ፡ ተርታ ፡ ብኾን ።

፲፪ ፡ ትእምርተ ፡ ሐዋርያትሰ ፡ ተገብረ ፡ ለክሙ ፡ በኵሉ ፡ ትዕግሥት ።
የሐዋርያት ፡ ትምህርት ፡ ከፍጹም ፡ ትዕግሥት ፡ ጋራ ።
ወበተአምራት ።
ድውይ ፡ ከመፈወስ ፡ ጋራ ።
ወመንክራት ።
ጋኔን ፡ ከማውጣት ፡ ጋራ ።
ወኃይላት ፡ (ም ፡ ፲፭ ፡ ፩ ። )
ሙት ፡ ከማስነሣት ፡ ጋራ ፡ ተደረገላችሁ ። አንድም ፡ ትእምርተ ፡ (ሐዋርያትሰ ፡ ) የሐዋርያነት ፡ ምል
ክትስ ፡ በፍጹም ፡ ትዕግሥት ፡ ድውይ ፡ በመፈወስ ፤ ጋኔን ፡ በማውጣት ፤ ሙት ፡ በማስነሣት ፡ ተደረገላ
ችሁ ።

፲፫ ፡ ወምንትኑ ፡ ዘአሕጸጽኩክሙ ፡ ወዘአኅጣእኩክሙ ፡ እምኵሉ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናት ።
ምእመናን ፡ ከተማሩት ፡ ትምህርት ፡ ካገኙት ፡ ኹሉ ፡ ያስቀረሁባችሁ ፡ ያሳጣኋችሁ ፡ ምንድነው ፡ አለ ፡
የለም ።
ዘእንበለ ፡ ዛቲ ፡ እንተ ፡ ኢመጻእኩ ፡ ኀቤክሙ ፡ አሥርሕክሙ ፡ ( ም ፡ ፲፭ ፡ ፱ ። )
ዕዳዬስ ፡ ይህታ ፡ በሌጌዎን ፡ ልነዳችሁ ፡ በነፋስ ፡ ልሰቅላችሁ ፡ ወደናንተ ፡ ያልመጣሁ ።
ጸግውንያ ፡ ለዛቲ ፡ አበሳየ ።
ዕዳህ ፡ ይህች ፡ ናት ፡ በሉኝ ። አንድም ፡ ለበደሌ ፡ ስርየት ፡ ስጡኝ ።

፲፬ ፡ ናሁ ፡ ሣልስየ ፡ ዝንቱ ፡ አንዘ ፡ እስተዳሉ ፡ እምጽእ ፡ ፀቤክሙ ።
ወደናንተ ፡ አመጣለሁ ፡ ስል ፡ እነሆ ፡ ይህ ፡ ሦስተኛዬ ፡ ነው ።
ወኢተፋጠነኒ ።
ነገር ፡ ግን ፡ አልቀናኝም ፡ (አለ ፡ ) ስንቅ ፡ አላገኘሁም ፡ ሲል ፡ ነው ። እስመ ፡ ኢያክሙ ፡ እፈቅድ ፡
ወእኮ ፡ ንዋየክሙ ።
ገንዘባችሁን ፡ ያይደለ ፡ እናንተን ፡ እወዳለሁና ።
እስመ ፡ ርቱዕ ፡ አበው ፡ ይዝግቡ ፡ ለውሉዶሙ ፡ ወአኮ ፡ ውሉድ ፡ ለአዝማዲሆሙ ፡ (ም ፡ ፲፫ ፡ ፩ ።)
ልጆች ፡ ለናት ፡ ለአባታቸው ፡ ያይደለ ፡ አበው ፡ ለልጆቻቸው ፡ ገንዘብ ፡ መሰብሰብ ፡ የሚገባቸው ፡
ስለኾነ ፡ ከብታችሁን ፡ ያይደለ ፡ እናንተን ፡ እወዳለሁና ።

፲፭ ፡ ወአንሰ ፡ ምክዕቢተ ፡ አስተዋፃእኩ ።
እኔስ ፡ ዕጽፍ ፡ ድርብ ፡ አወጣጣሁ ፡ (አለ ፡ ) ኹለት ፡ ከታብ ፡ መጻፍ ፤ ማስተማር ፡ ዋጋ ፡ አለመብላት ፡
ነው ።
ወእሜጡ ፡ ሥጋየ ፡ በእንተ ፡ ነፍስክሙ ።
ስለናንተ ፡ ሰውነቴን ፡ ለመከራ ፡ አሳልፌ ፡ እሰጣለሁ ፤ ቀን ፡ በትምህርት ፡ ሌት ፡ በስፌት ።
ወእሙኒ ፡ ፈድፋደ ፡ አፍቀርኩክሙ ፡ ርእስየ ፡ አፍቀርኩ ፡ ( ፊልጵ ፡ ፪ ፡ ፲፯ ። )
ፈጽሜም ፡ ብወዳችሁ ፡ ራሴን ፡ መውደዴ ፡ ነው ።

፲፮ ፡ ወአንሰ ፡ ኢያክበድኩ ፡ ላዕሌክሙ ።
እኔስ ፡ ሥርዓት ፡ እላጸናሁባችሁም ፡ ነገር ፡ አላበዛሁባችሁም ። አንድም ፡ አላስቸገርኋችሁም ።
ወባሕቱ ፡ መስተመይነ ፡ ከዊንየ ፡ ነሣእኩክሙ ፡ በጕሕሉት ።
ተተንኩዩ ፡ በጕሕሉት ፡ ገንዘብ ፡ አደረግኋችሁ ፡ (አለ ፡ ) ዋጋ ፡ ያለመብላትን ፡ አሳይቼ ፡ በትምህርት ፡
በሃይማኖት ፡ ገንዘብ ፡ አደረግኋችሁ ፡ እንጂ ፡ (ሐተታ ፡ ) የሚገባ ፡ ትምይንት ፡ የማይገባ ፡ ትምይንት ፤
የሚገባ ፡ ጕሕሉት ፡ የማይገባ ፡ ጕሕሉት ፡ አለ ። የሚገባ ፡ ትምይንት ፡ እንደ ፡ እስራኤል ፡ ነው ፡ ምሕዋረ ፡
ሠሉስ ፡ ዕለት ፡ ሐዊረነ ፡ ንግብእ ፡ ብለው ፡ በውሸት ፡ ምክንያት ፡ የግብጻውያንን ፡ መሣሪያቸውን ፡ ከብ

www.ethiopianorthodox.org

ታቸውን ፡ ዘርፈዋቸው ፡ ገፈዋቸው ፡ ወጥተዋል ፤ ይኸውም ፡ ኹለት ፡ መቶ ፡ አሥራ ፡ አምስት ፡ ዘመን ፡ የተገዙበት ፡ ነውና ፡ ዕዳ ፡ አልሆንባቸውም ።

የማይገባ ፡ ትዕቢት ፡ እንደ ፡ ሳኦል ፡ ነው ፤ ሊገለው ፡ ወዶ ፡ ሳለ ፡ ዳዊት ፡ ወልድየ ፡ ማለት ።

የሚገባ ፡ ትሕትና ፡ እንደ ፡ ሳባ ፤ ታናሹቱን ፡ እሰጥሃለሁ ፡ ብሎ ፡ ታላቂቱን ፡ መስጠት ፤ ታላቅ ፡ ሳሉ ፡ ታናሽ ፡ አያገባምና ።

የማይገባ ፡ ትሕትና ፡ እንደ ፡ ሄሮድስ ፡ ነው ፤ ሊገለው ፡ ወዶ ፡ ሳለ ፡ እሰግድ ፡ ሎቱ ፡ ማለት ።

፲፯ ፡ ቦኑ ፡ እንጋ ፡ ዘፈነውኩ ፡ ኀቤክሙ ።

በውኑ ፡ ይህን ፡ አደርጉልኝ ፡ ብዬ ፡ ወደናንት ፡ ላክሁባችሁን ፤ (ቦኑ ፡ ) የላክሁባችሁ ፡ መላክ ፡ አለን ።

ወቦኑ ፡ ዘተዐገልኩክሙ ።

በውነት ፡ ከብታችሁን ፡ ቀማኋችሁን ፤ (ቦኑ ፡ ) የቀማኋችሁ ፡ መቀማት ፡ አለን ።

፲፰ ፡ ናሁ ፡ አስተብቋዕክዎ ፡ ለቲቶ ።

ወደናንት ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ እነሆ ፡ ቲቶን ፡ ማለድሁት ።

ወፈነውክዎ ፡ ለካልእ ፡ እኁነ ፡ ምስሌሁ ፡ እኁነ ፡ ምስሌሁ ፡

ወንድማችን ፡ ሉቃስንም ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ሰደድሁት ።

ቦኑ ፡ ዘገፍዐክሙ ፡ ቲቶ ።

በውኑ ፡ ቲቶ ፡ በደላችሁን ፡ የበደላችሁ ፤ (ቦኑ ፡ ) መበደል ፡ አለን ።

አኮኑ ፡ በውእቱ ፡ መንፈስ ፡ ዘይረውጽ ፡ በላዕሌሁ ፡ ቦቱ ፡ ሖርነ ፡ አሠረ ፡ ዚአሁ ፡ ተለውነ ።

ቲቶስ ፡ አልበደለንም ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ ቲቶማ ፡ ካልበደላችሁ ፡ እኛስ ፡ በቲቶ ፡ ግብር ፡ ጸንተን ፡ ቲቶ ፡ ተቃኝቶበት ፡ በሚኖር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተቃኝተን ፡ የምንኖር ፡ አይደለምን ።

፲፱ ፡ ትትሔዘቡነሁ ፡ ኮመ ፡ ንሕነ ፡ ንትዋቀሠክሙ ።

እናንተም ፡ አልበደላችሁንም ፡ ትሉኝ ፡ እንደኾነ ፡ እኛማ ፡ ካልበደልናችሁ ፡ እኛ ፡ እናንተን ፡ በደሉን ፡ ብለን ፡ እንድንወቅሳችሁ ፡ ትጠረጥሩኛላችሁን ፡ (በደሉን ፡ ብለው ፡ ይወቅሱናል ፡ ብላችሁ ፡ ትጠረጥሩናላችሁን ። ) ዘሂ ፡ ንነግር ፡ በቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡ ክርስቶስ ፡ ንነግር ፡ (ም ፡ ፲፰ ፡ ፲፯-፲፰።)

ይህንም ፡ የምንናገረውን ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡ ባወቀው ፡ የክርስቶስን ፡ ነገር ፡ ለማስተማር ፡ እንናገራለን ።

ወዙሉሰ ፡ እኀዊነ ፡ ከመ ፡ ትትሐነጹ ።

ይህ ፡ ኹሉ ፡ ግን ፡ ወንድሞቻችን ፡ እናንት ፡ ሕንጸ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትኾኑ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

፳ ፡ ወባሕቱ ፡ እፈርህ ፡ ለእመቦ ፡ ከመ ፡ እመ ፡ መጻእኩ ፡ ወኢረከብኩክሙ ፡ በከመ ፡ እፈቅድ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ወደናንት ፡ በመጣሁ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ እንደምወደው ፡ ኾናችሁ ፡ ባላገኛችሁ ።

ወእነሂ ፡ እከውነክሙ ፡ በከመ ፡ ዘኢትፈቅዱ ፡ (ም ፡ ፲ ፡ ፪ ።)

እኔም ፡ እናንት ፡ እንደማትወዱት ፡ እኾንባችኋለሁ ፡ ብዬ ፡ እፈራላችኋለሁ ።

ወዮጊ ፡ ይከውን ፡ ውስቴትክሙ ፡ ተዝኀሮ ።

ወይም ፡ እንጂ ፡ በውስጣችሁ ፡ ተዝኀሮ ፡ ይኾን ፡ ይኾናል ፡ (እስ ፡ ) አነ ፡ ዘጳውሎስ ፤ ወአነ ፡ ዘአጵሎስ ፡ ወአነ ፡ ዘኬፋ ፡ ትሉ ፡ ይኾናል ።

ወተቃንዖ ።

በህብት ፡ ትቃኑ ፡ ይኾናል ።

ወተምዕዖ ።

መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አድሮባችሁ ፡ ሳለ ፡ ገቢረ ፡ ተአምራት ፡ ባይሰጣችሁ ፡ አላደረብንም ፡ ትሉ ፡ ይኾናል ።

ወተሣልቆ ።

ዓይኑ ፡ በፈረጠ ፤ እጁ ፡ እግሩ ፡ በተቆረጠ ፡ ትዘብቱ ፡ ይኾናል ። አንድም ፡ ትንሣኤ ፡ ሙታን ፡ የለም ፤ ፈርሰን ፡ በስብሰን ፡ እንቀራለን ፤ እያላችሁ ፡ በራሳችሁ ፡ ትዘብቱ ፡ ይኾናል ።

አው ፡ ተሐምዮ ።

ትነቃቀፉ ይሆናል

ወተሀውኮ ።

ሁከት ፡ ሥጋዊ ፡ ትታወኩ ፡ ይኾናል ።

ወእዕብዮ ፡ ልብ ፡ (፩ ፡ ቆሮ ፡ ፬ ፡ ፮ ።)

www.ethiopianorthodox.org

ልቡናችሁን ፡ ታሳብዩ ፡ ይኾናል ። (የላይኛውን ፡ አነ ፡ ዘጳውሎስ ፡ ወአነ ፡ ዘአጵሎስ ፤ ወአነ ፡ ዘኬፋ፤ ያሉ ፡ እንደሆነ ፤ ይህን ፡ መኑ ፡ የሐተተከ ፡ የላይኛውን ፡ መኑ ፡ የሐትተከ ፡ ያሉ ፡ እንደኾነ ፡ ይህን ፡ ወም ስለ ፡ ዝኒ ፡ ዓዲ ፡ ዕቡያን ፡ ባለው ፡ ትታበዩ ፡ ይኾናል ። )

፳፩ ፡ የጊ ፤ ካዕበ ፡ መጺእየ ፡ ኀቤከሙ ፡ የሐምመኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንቲአከሙ ፡

ወይም ፡ ዳግመኛ ፡ ወደናንተ ፡ በመጣሁ ፡ ጊዜ ፡ በናንተ ፡ እግዚአብሔር ። ያሳዝነኝ ፡ ይኾናል ።

ወእላሕዎሙ ፡ ለብዙኃን ፡ እለ ፡ አበሱ ፡ ወኢነስሑ ፡ በእንተ ፡ ኀሣሮሙ ፤ ወምርዓቶሙ ፡ ወዝሙቶሙ ፡ ዘገ ብሩ ፡ ( ም ፡ ፪ ፡ ፩ና ፡ ፲፫ ፡ ፪ ። )

ስለሥሩት ፡ ዝሙት ፤ ድርዓት ፤ ኃሣር ፤ በድለው ፡ ንስሓ ፡ ላልገቡት ፡ እዝንላቸው ፡ ይኾናል ፤ አላሕዎሙ ፡ ይላል ። በድለው ፡ ንስሓ ፡ ያልገቡትን ፡ አሳዝናቸው ፡ ይኾናል ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

### ክፍል ፡ ፲፩ ።

፩ ፡ ወናሁ ፡ ሣልስየ ፡ ዝንቱ ፡ እንዘ ፡ እመጽእ ፡ ኀቤከሙ ።

ወደናንተ ፡ ስመጣ ፡ እነሆ ፡ ይህ ፡ ሦስተኛዬ ፡ ነው ።

አኮኑ ፡ በአፈ ፡ ክልኤቱ ፡ ወሠለስቱ ፡ ስማዕት ፡ ይቀውም ፡ ኵሉ ፡ ነገር ፡ ( ዘዳግም ፡ ፲፱ ፡ ፲፭ ። )

ነገር ፡ ኹሉ ፡ በኹለት ፡ በሦስት ፡ ምስክር ፡ የሚቀረጥ ፡ አይደለምን ።

፪ ፡ ወአቅደምኩ ፡ ነጊረ ፡ እምትካት ።

በጥንተ ፡ ስብከት ፡ አስቀድሜ ፡ ነገርኋችሁ ።

እቀድም ፡ ወእነግር ፡ ዓዲ ።

ዳግመኛ ፡ አስቀድሜ ፡ ነገርኋችሁ ፡ (አለ ፡ ) ጢሞቴዎስ ፡ ከታብ ፡ ይዞ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ (እቀድም፡ ከቲቶ ። )

በከመ ፡ አቤለከሙ ፡ እንዘ ፡ ሀሎኩ ፡ በቀዳሚ ።

በጥንተ ፡ ስብከት ፡ ከናንት ፡ ዘንድ ፡ ሳለሁ ፡ እንደነገርኋችሁ ።

ከማሁ ፡ እንዘ ፡ ኢሀሎኩ ፡ በሣልስ ፡ እነግር ።

በሌለሁበትም ፡ ጊዜ ፡ በሦስተኛው ፡ እነግራችኋለሁ ፡ (አለ ፡ ) ቲቶ ፡ ከታብ ፡ ይዞ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ።

እንድም ፡ ወአቅደምኩ ፡ ነጊረ ፡ እምትካት ።

አስቀድሜ ፡ ነገርኋችሁ ፡ (አለ ፡ ) ጢሞቴዎስ ፡ ከታብ ፡ ይዞ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ። አቀድም ፡ ወእነግር ፡ ዓዲ ፡ በከመ ፡ አቤለከሙ ፡ እንዘ ፡ ሀሎኩ ፡ በቀዳሚ ፡ ከማሁ ፡ እንዘ ፡ ኢሀሎኩ ፡ በሣልስ ፡ እነግር ። (አቀድም ፡ ዓዲ ፡ በሣልስ ፡ እነግር ፡ ) ከናንት ፡ ዘንድ ፡ ሳለሁ ፡ በጥንተ ፡ ስብከት ፡ እንደነገርኋችሁ ፡ በሌለሁበትም ፡ ጊዜ ፡ ኹለተኛ ፡ በሦስተኛ ፡ እነግራችኋለሁ ፡ (አለ ፡ ) ቲቶ ፡ ከታብ ፡ ይዞ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ። (ኹለተኛነቱ ፡ ለጢሞቴዎስ ፡ ሦስተኛነቱ ፡ ለጥንተ ፡ ስብከት ። ).

ለእለ ፡ አበሱ ፡ ቀዲሙ ።

በድለው ፡ ንስሓ ፡ ለገቡ ።

ወለባዕዳንኒ ።

በድለው ፡ ንስሓ ፡ ላልገቡት ፡ እነግር ።

ከመ ፡ እምከመ ፡ መጻእኩ ፡ ኢይምሕክ ፡ እንከ ፡ ካዕበ ።

ወደናንት ፡ በመጣሁ ፡ ጊዜ ፡ ዳግመኛ ፡ እንዳላዝን ፡ (አለ) ፡ ሥራ ፡ እንዳልሠራ ፡ በነፍስ ፡ እንዳልለቅ ሳችሁ ፡ በሌጌዎን ፡ እንዳልነፃችሁ ።

፫ ፡ እስመ ፡ ተንሥሁ ፡ መከራሁ ፡ ለክርስቶስ ፡ ዘይነብብ ፡ በላዕሌየ ።

በኔ ፡ አድሮ ፡ የሚናገረውን ፡ መከራ ፡ ልትቀበሉ ፡ ትወዳላችሁና ፡ እምከመ ፡ መጻእኩ ፡ ኢይምሕክ ። ውእቱ ፡ እልቦ ፡ ዘይስእኖ ፡ በኀቤኪሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ ኵሉ ፡ ዘይትከሀሎ ፡ ኹሉ ፡ ይቻለዋል ፡ እንጂ ፡ በናንተ ፡ ዘንድ ፡ ምንም ፡ የሚሳነው ፡ የሌለ ፡

፬ ፡ እስመ ፡ ዘተሰቅለ ፡ በድካም ፡ ሕያው ፡ ውእቱ ፡ በኃይለ ፡ እግዚአብሔር ። (ፊልጵ ፡ ፪ ፡ ፯ ፡ ፰ ።)

ደከሞ ፡ በመስቀል ፡ መከራ ፡ የተቀበለ ፡ እሱ ፡ (በእግዚአብሔር ፡ ኃይል) ፡ በእግዚአብሔርነቱ ፡ ኃይል ፡ ሕያው ፡ ነውና ፡ ዘእንበለ ፡ ዳዕሙ ፡ ኵሉ ፡ ይትከሀሎ ፡ ውእቱ ፡ አልቦ ፡ ዘይስእኖ ፡ ባለው ።

www.ethiopianorthodox.org

ወንሕነኒ ፡ ንደክም ፡ ምስሌሁ ።

እኛም ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ እንደሱ ፡ በመከራው ፡ እንደክማለንና ።

ወነሐዩ ፡ ምስሌሁ ፡ በኀይለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በእንቲአከሙ ።

እሱ ፡ ሕያው ፡ እንደኾነ ፡ እኛም ፡ እናንተን ፡ ስለማስተማር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ሕያዋን ፡ ኾነን እንኖራለንና ። ትንሣኤው ፡ መከራው ፡ አይምሕክ ፡ ሳለው ።

፭ ፡ ወርእሰከሙ ፡ አመክሩ ፡ ለእመ ፡ ሀለውከሙ ፡ በሃይማኖት ።

እንዲህም ፡ ከኾነ ፡ በሃይማኖት ፡ ጸንታችሁም ፡ እንደኾነ ፡ አልጸናችሁም ፡ እንደኾነ ፡ ራሳችሁን ፡ መርምሩ ።

ወርእስከሙ ፡ ሕቱ ፡ (፩ ቆሮ ፡ ፲፩ ፡ ፳፰ ፡)

ራሳችሁን ፡ መርምሩ ፡ (አለ) ፡ በነፍስ ፡ በሥጋ ፡ ሲል ፡ ይደጋግማል ።

ለእመቦ ፡ ዘኢተእምሩ ፡ ለሊከሙ ፡ ወኢትጤይቁ ፡ ከመ ፡ ሀሎ ፡ ክርስቶስ ፡ ምስሌከሙ ።

ክርስቶስ ፡ አድሮባችሁ ፡ እንዳለ ፡ የማታውቁ ፡ የማትረዱ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ራሳችሁን ፡ መርምሩ ።

አንድም ፡ ክርስቶስ ፡ ያላደረበት ፡ ሰው ፡ ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ እንዳለ ፡ የማታውቁ ፡ የማትረዱ ፡ እንደኾነ ፡ ራሳችሁን ፡ መርምሩ ።

ወለእመሰ ፡ ኢኮነ ፡ ከመዝ ፡ ምኑናን ፡ አንትሙ ።

እንዲህ ፡ ግን ፡ ካልኾነ ፡ (አለ) ፡ መርምራችሁ ፡ ካላወቃችሁ ፡ ተርታዎች ፡ ናችሁ ።

፮ ፡ ወእትአመን ፡ አንሰ ፡ ታእምሩ ፡ ከመ ፡ ኢኮነ ፡ ምኑናነ ፡ ንሕነኒ ።

እኛ ፡ ግን ፡ ክርስቶስ ፡ አድሮብኝ ፡ እንዳለ ፡ እንድናውቅ ፡ ልታውቁ ፡ እወዳለሁ ። አንድም ፡ ክርስ ቶስ ፡ ያላደረበት ፡ ሰው ፡ ከናንተ ፡ ዘንድ ፡ እንዳለ ፡ እንድናውቅ ፡ ልታውቁ ፡ እወዳለሁ ።

፯ ፡ ወንጼሊ ፡ ኀበ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ኢይግበር ፡ እኩየ ፡ ላዕሌከሙ ፡ ወኢምንተኒ ።

በናንት ፡ ምንምን ፡ ክፉ ፡ ሥራ ፡ እንዳይሠራ ፡ (አለ) ፡ በነፍስ ፡ እንዳይሰቅላችሁ ። በሌጌዎን ፡ እንዳይነ ጸችሁ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንጸልያለን ።

ወአኮሰ ፡ ከመ ፡ ንሕነ ፡ ኅሩያነ ፡ ንኩን ።

መጸለያችንም ፡ እኛ ፡ ደጋግ ፡ ለመባል ፡ አይደለም ።

አላ ፡ ዳዕሙ ፡ ከመ ፡ አንትሙ ፡ ሠናየ ፡ ትግበሩ ።

እናንት ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ ትሠሩ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

ወን ሕነሰ ፡ ከመ ፡ ምኑናን ።

እኛስ ፡ ተርታዎችም ፡ ብንባል ፡ ግድ ፡ የለንም ።

፰ ፡ እስመ ፡ ኢንክል ፡ ወፂአ ፡ እምጽድቅ ።

ከሃይማኖት ፡ ከወንጌል ፡ አንወጣምና ።

ዘእን ፲ለ ፡ ዳዕሙ ፡ በጽድቅ ።

በሃይማኖት ፡ ወንጌል ፡ ጸንተን ፡ እንኖራለን ፡ እንጂ ።

፱ ፡ ወእትፌሣሕ ፡ ሶበ ፡ ንሕነ ፡ ነሐምም ።

መከራም ፡ በተቀበልን ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ይለኛል ።

ከመ ፡ አንትሙ ፡ ትጽንዑ ፡ ወትትፌሥሑ ።

እናንት ፡ ደስ ፡ ብሏችሁ ፡ በመከራው ፡ ትጸኑ ፡ ዘንድ ።

፲ ፡ ወዝውእቱ ፡ ጸሎትነ ።

የምንጸልየውም ፡ ጸሎት ፡ ይህ ፡ ነው ።

ከመ ፡ አንትሙ ፡ ታርትዑ ።

እናንት ፡ ርእስ ፡ ልቡናችሁን ፡ የቀና ፡ ታደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ነው ።

፲፩ ፡ ወበእንተዝ ፡ ዘንተ ፡ እጽሕፍ ፡ ለከሙ ፡ እንዘ ፡ ኢሀለውኩ ፡ ኀቤከሙ ።

ጻሐፍኩ ፡ ሲል ፡ ነው ። ስለዚህ ፡ ከናንት ፡ ዘንድ ፡ ሳልኖር ፡ ይኽነን ፡ ጻፍሁላችሁ ።

ከመ ፡ አመ ፡ መጻእኩ ፡ ምቱረ ፡ ኢይግበር ፡ በላዕሌከሙ ።

ወደናንት ፡ በመጣሁ ፡ ጊዜ ፡ ቍርጥ ፡ ሥራ ፡ እንዳልሠራ ፡ (እለ ፡) በነፋስ ፡ እንዳልሰቅላችሁ ፡ በሌጌዎን ፡ እንዳልነጻችሁ ።

www.ethiopianorthodox.org

ከመ ፡ ዘሥልጣን ፡ በ ።
ሥልጣን ፡ ያለኝ ፡ እንደመኾኔ ፤ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ እንደ እግዚአብሔር ።
ዘወሀበኒ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሐኒጽ ፡ ወአኮ ፡ ለንሢት ፡ (ም ፡ ፲ ፡ ፲፩ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ፰ ።)
ለማፍረስ ፡ ያይደለ ፡ እናንተን ፡ ለማነጽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባሠለጠነኝ ፡ ገንዘብ ፡ ኢይግበር ፡ እኩዩ ላለው ።

፲፩ ፡ ተፈሥሑ ፡ እንከሰ ፡ አኀዊነ ፡ (ፊልጵ ፡ ፬ ፡ ፬ ።)
ወንድሞቻችን ፡ እንግዲህስ ፡ ወዲህ ፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡
እጥብዑ ።
መከራውን ፡ ለመቀበል ፡ ጨክኑ ።
ወተዓገሡ ።
መከራውን ፡ ታገሡ ።
ወተሰነአዉ ።
በፍቅር ፡ አንድ ፡ ኹኑ ።
ወአምላከ ፡ ሰላም ፡ ወፍቅር ፡ የሀሉ ፡ ምስሌክሙ ፡ (ሮሜ ፡ ፲፭ ፡ ፴፫ ።)
የፍቅር ፡ የአንድነት ፡ ባለቤት ፡ እግዚአብሔር ፡ አድሮባችሁ ፡ ይኑር ።

፲፪ ፡ ተአምኁ ፡ በበይናቲክሙ ፡ በአምኃ ፡ ቅድሳት ።
ከይሁዳ ፡ ከዲያብሎስ ፡ ከኤሳው ፡ በተለየ ፡ ሰላምታ ፡ እርስ ፡ በርሳችሁ ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ ተባባሉ ።
አምኁክሙ ፡ ኵሎሙ ፡ ቅዱሳን ። (፩ ፡ ቆር ፡ ፲፮ ፡ ፳ ።
ምእመናን ፡ ኹሉ ፡ ቸር ፡ አላችሁን ፡ ይሏችኋል ።

፲፫ ፡ ጸጋሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
የጌታችን ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸጋው ።
ወፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ።
የእግዚአብሔርም ፡ ፍቅሩ ።
ወሱታፌ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሀሉ ፡ ምስለ ፡ ኵልክሙ ።
የመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ አንድነቱ ፡ በናንተ ፡ ጸንቶ ፡ ይኑር ፡

አ ሜ ን ።

በውነት ።

ተፈጸመት ፡ መልእክት ፡ ዳግሚት ፡ ኀበ ፡ ሰብእ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ወተጽሕፈት ፡ በፊልጵስዩስ ፡ ዘመቄዶንያ ፡
ወተፈነወት ፡ በእደ ፡ ቲቶ ፡ ወሉቃስ ።
የመቄዶንያ ፡ መዲና ፡ በምትኾን ፡ በፊልጵስዩስ ፡ የተጻፈች ፡ በቲቶና ፡ በሉቃስ ፡ እጅ ፡ ከጳውሎስ ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡ የተላከች ፡ ኹለተኛዪቱ ፡ ክታብ ፡ ደረሰች ፡ ተፈጸመች ።
ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ።
እነሣስቶ ፡ ላስጀመረን ፡ አስጀምሮ ፡ ላስጨረሰን ፡ ጌታ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።

www.ethiopianorthodox.org